# አዲስ ዘመን

አፕድ

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 016 መስከረም 16 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ዓባይን መነሻ ያደረገው የግብፅ አካሄድ - ለሠላም ወይስ ቀጣናውን ለማተራመስ?



**አዲሱ ገረመው**

**ዜና ትንታኔ**

ግብፅ ኢትዮጵያን ከጎረቤት ሀገራት የማግለል እሳቤዋን ተግባራዊ ለማድረግ ከሶማሊያና ከኤርትራ ጋር ከምታደርጋቸው ግንኙነቶች ባሻገር በቅርቡ ሠላም አስከባሪ በማስመሰል ወታደሮቿን ወደ ደቡብ ሱዳን ለማሠማራት ማቀዷን ይፋ ማድረጓ ይታወቃል። የግብፅ እንቅስቃሴ ለሠላም አስተዋፅዖ ማድረግ ወይስ ኢትዮጵያን ለመክበብ እና ምሥራቅ አፍሪካን ለማተራመስ ?

ኢትዮጵያ የዓባይ ግድብ የሀገራዊ ልማት ስትራቴጂዋ ቁልፍ አካል መሆኑን በተደጋጋሚ ለዓለም አቀፉ ማኀበረሰብ ስታሳውቅ በግድቡ ምክንያት በታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንደማያደርስ ማስተማመኛ በመስጠት ጭምር እንደሆነ በርካቶች ዘግበውታል።

ዘ ኒውዮርክ ታይምስ እኤአ በ2020 ይዞት በወጣው ዘገባ እንዳመላከተውም፤ የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ትልቅ የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት ረገድ ትልቅ ተስፋን የሰነቀችበት መሆኑን ይጠቅሳል። እንግሊዛዊው የፖለቲካ ተንታኝ አሌክስ ደ ዋል ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ግድቡ ለኢትዮጵያ የመልማት መብትን የሚያረጋግጥ ነው ማለታቸው አይዘነጋም።

ዓባይን መነሻ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








## የሩዝ ልማት የመሬት ሽፋን ወደ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር አድጓል

ገጽ 2

## “ደብተር ስላላገኘን በትምህርታችን ላይ ተፅዕኖ ፈጥሮብናል”

- የአዲስ ከተማና የዳግማዊ ምኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች

## “በአንድ ሳምንት ውስጥ ደብተሮች ለተማሪዎች ይሰራጫሉ”

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ

ገጽ 4

# መስከረምና ቱሪዝም

**ሄለን ወንድምነው**

**ዜና ሐተታ**

ወርሐ መስከረም ለኢትዮጵያውያን ልዩ ትርጉም አለው። የክረምቱ ዝናብ አልፎ አበቦች የሚያብቡበትና ወንዞች የሚጎድሉበት ወር ነው። ከዚህ አልፎም በክረምት ዝናብ የተለያየ ቤተሰብ የሚገናኙበትና የሚጠያየቁበት ነው። አሮጌው ዘመን ተሰናብቶ አዲሱ ዘመን የሚተካውም በዚሁ ወር ነው።

በወርሐ መስከረም በርከት ያሉ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው የአደባባይ በዓላት ይከበራሉ። የዘመን መለወጫ፣ ደመራ፣ ኢሬቻ፣ መሳላ፣ መሽቃሮ፣ ያሆዴ ከሚከበሩት በዓላት ጥቂቶቹ ናቸው። በዓላቱ የኢትዮጵያውያን ባሕል፣ ወግ፣ እሴት፣ ማንነትና አንድነት ለሌሎች የዓለም ሀገራት አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው።

በወርሐ መስከረም የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት የኢትዮጵያን አንድነት ለማጠናከርና የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ ምን ፋይዳ አላቸው? ብለን ላነሳቸው ጥያቄዎች የዘርፉ ምሑራን ምላሽ ሰጥተዋል።

መስከረምና ... ወደ ገጽ 3 ዞሯል








# የሩዝ ልማት የመሬት ሽፋን ወደ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር አድጓል

**ሳሙኤል ወንድሰን**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሁለት ዓመታት በተሠራው ሥራ የሩዝ ልማት የመሬት ሽፋንን ከ180 ሺህ ሄክታር ወደ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ማሳደግ መቻሉን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ኢሳያስ ለማ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ሩዝ እንደሀገር በተለየ ትኩረት እየተሠራባቸው ካሉ ሰብሎች ውስጥ አንዱ ነው። ከስንዴ ቀጥሎ ባለፉት ሁለት ዓመታት የሩዝ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጠንካራ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል። በዚህም የሩዝ ልማት የመሬት ሽፋንን ከ180 ሺህ ሄክታር ወደ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ማሳደግ ተችሏል።

ቀደም ሲል ሩዝ በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር አካባቢ፣ በኦሮሚያ ክልል እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ጉራፈርዳ አካባቢ እንደሚመረት የገለጹት አቶ ኢሳያስ፤ የዚህም የመሬት ሽፋን 180 ሺህ ሄክታር ያህል እንደነበር ተናግረዋል። ይህም እንደሀገር ካለው ፍላጎትና አቅም አንፃር በምርትም በመሬት ሽፋንም ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

ከ180 ሺህ ሄክታሩ ሰባ በመቶ የሚሆነው በአማራ ክልል ብቻ ይመረት እንደነበር አንስተው፤ አሁን ላይ ሁሉም ክልሎች ልዩ ትኩረት (ኢኒሼቲቭ) በማድረግ ተግባራዊ እያደረጉት መሆኑን የገለጹት አቶ ኢሳያስ፤ በዚህም ባለፉት ሁለት ዓመታት በተሠራው ሥራ የሩዝ ምርት የመሬት ሽፋንን ከ180 ሺህ ሄክታር ወደ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ማሳደግ ተችሏል ብለዋል።

ሩዝን በማምረት የአካባቢው አርሶ አደሮች ተጠቃሚ በመሆናቸው ደስተኛ ናቸው። በተለይ ከዚህ በፊት ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሬቶች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ የደስታቸው ሌላኛው ምንጭ መሆኑን የተናገሩት አቶ ኢሳያስ፤ መሬቶቹ ውሃ አዘል በመሆናቸው ለሩዝ ሰብል ምቹ እንደሆኑ ገልጸዋል።

በዘንድሮው የምርት ዘመን ዓመት አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬትን በሩዝ ሰብል መሸፈን መቻሉ ትልቅ እምርታ መሆኑን የተናገሩት አቶ ኢሳያስ፤ ሩዝ ከሌሎች ሰብሎች የተለየ አሰባሰብ አለው። ለዚህም የሚያግዙ መሣሪያዎች ለአርሶ አደር የማሟላት ሥራዎች እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ሌላው የሩዝ ልማት በሶማሌ ክልል ጎዴ አካባቢ፣ ሸበሌ ዞን፣ ሸንሌ እና ሌሎች አካባቢዎች ላይ የተጀመረ ሲሆን ይህም 500 ሄክታር መሬት ላይ ተግባራዊ ተደርጓል ያሉት አቶ ኢሳያስ፤ በክልሉ ያለው የሩዝ ሰብል ሽፋን ሦስት ሺህ ሄክታር መሬት እስኪደርስ ድረስ እየተደረገ ያለው ርብርብ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

በሶማሌና በአፋር ክልል የመስኖ ሩዝ ለማምረት እንዲሁም በሶማሌ ክልል ሁለተኛ ዙር ሩዝን ለማምረት ዝግጅት እየተከናወነ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ኢሳያስ፤ የሩዝ ምርትን በሀገር ውስጥ የመተካት እቅድን ከማሳካት አንፃር ባለፉት ሁለት ዓመታት የተሰራው ሥራ አመርቂ መሆኑን ገልጸዋል።

በዚህም የሩዝ ሰብል የመሬት ሽፋን አድጓል። ከዚህ በፊት ጥቅም ላይ ያልዋሉ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ተችሏል ያሉት አቶ ኢሳያስ፤ ከውጭ የሚገባውን የሩዝ ምርትን ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ለመተካት እየተሠራ ነው ብለዋል።

# የአደባባይ በዓላት ለቱሪስት ፍሰት መጨመር ያላቸውን አስተዋፅዖ አሟጦ መጠቀም ይገባል

**ውብሸት ሰንደቁ**



አዲስ አበባ፡- የአደባባይ በዓላት ለቱሪስት ፍሰት መጨመር ያላቸውን አስተዋፅዖ አሟጦ መጠቀም ይገባል ሲል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

የመስቀል ደመራ በዓል ሲምፖዚዬም "በኀብራዊ ብርሃኑ ዓለምን የሚጣራ፤ መስቀል የአንድነታችን ደመራ" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሕል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሃፍታይ ገብረእግዚአብሔር እንደገለጹት፤ የአደባባይ በዓላት ለቱሪስት ፍሰት መጨመር ከፍተኛ አስተዋፅዖ አላቸው። በዓላቱን ለቱሪዝም ዘርፍ ያላቸውን ዕድል አሟጦ መጠቀም ይገባል።

በመስከረም ወር ከሚከበሩ የአደባባይ በዓላት የመስቀል በዓል አንዱ መሆኑን አንስተው፤ በዓሉ የቱሪዝም መስሕብ እንዲሆን የበለጠ መሥራት እንደሚገባ ገልጸዋል።

በዓላቱን ለማክበር ከተለያዩ የዓለም ጫፎች የሚመጡ ጎብኚዎችን በዓላቱ በተመዘገቡበት ልዕልና ልክ አድርገን ማሳየት ይገባናል ብለውም፤ ይህም መዲናዋ እየሠራቻቸው ከምትገኘው የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን የማልማት ሥራ ጋር ሲደመር ቱሪዝምን ለማሳደግ እንደሚረዳ ተናግረዋል።

በየዓመቱ ቢሮው በዓሉን የሚዘክሩ ሁነቶችን እንደሚያዘጋጅ አንስተው፤ ይህን የምናደርገው በዓለም አቀፍ ቅርስነት የተመዘገበው በዓሉ ያለውን ዕሴቶች እና የነበረውን ልዕልና በአግባቡ ይዞ እንዲዘልቅ ለማስቻል ነው ብለዋል።

በዓሉ ከሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ባሻገር እንደየአካባቢው የሚለያዩ የአለባበስ እና የአጊያጌጥ ባሕሎች እንዳለው ጠቅሰው፤ እነዚህ ባሕሎች ሳይበረዙ ከትውልድ ትውልድ እንዲሸጋገሩ መሥራት እንደሚገባ ተናግረዋል።

በዓሎቻችን የአንድነት እና የፍቅር እንጂ የመጠላላት ምንጭ እንዳይሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊሠሩ ይገባል ያሉት ኃላፊው፤ ለዚህ በተለይም የሃይማኖት አባቶች ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው ሲሉ ገልጸዋል።

አዲስ አበባ ከአፍሪካ ቀዳሚ የቱሪስት መዳረሻ ለመሆን ደፋ ቀና እያለች መሆኑን በማንሳት፤ እነዚህ የአደባባይ በዓላት ቱሪዝሙን በመደገፍ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ እና የከተማዋን ገፅታ የሚቀይሩ ናቸው ብለዋል።

በቢሮው የኪነጥበብ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሠርፀ ፍሬስብሃት በበኩላቸው የሰው ልጅ ሕይወትን ልዩ ትርጉም ከሰጠባቸው መንገዶች አንዱ በዓል ነው ብለው፤ ነገር ግን በዓላትን ስለፈለግናቸው ብቻ ልንፈጥራቸው አንችልም። በዓላቱ እንዲፈጠሩ የሚያደርጉ አመክንዮዎች አሉ ብለዋል።

በተለይም በአደባባይ በዓልነት ከሚከበሩ ሃይማኖታዊ እና ባሕላዊ ይዘት ካላቸው በዓላት አንዱ መስቀል መሆኑን በመጥቀስ፤ በዓሉ የሚከበርበት ጊዜ ተከታታይ የአደባባይ በዓላት የሚከበሩበት በመሆኑ ለቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው አመላክተዋል።


ሀገራችን ኢትዮጵያ 13 ቅርሶቿን በዓለም ቅርስነት አስመዝግባለች ያሉት ደግሞ በቢሮው የባሕል ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አስፋው ኩማ ናቸው።

ከተመዘገቡት ውስጥ አምስት ያህሉ የማይዳሰሱ ናቸው ያሉት አቶ አስፋው፤ የመስቀል በዓልም በዓለም ቅርስነት ከተመዘገቡት አንዱ መሆኑን አስታውቀዋል።


በዓሉ ለዘመናት ሃይማኖታዊ ትውፊቱን እና ባሕላዊ ወጉን ጠብቆ እየተከበረ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በቱሪዝም መስሕብነቱ ለኢኮኖሚ ጉልህ አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል ብለዋል።

ከዚህ በተሻለ መልኩ የገቢ ምንጭ እንዲሆን እና በዓለም እንዲታወቅ ቢሮው ሰፊ ሥራ እየሠራ እንደሚገኝም አብራርተዋል።

# የአብሮነት እሴት ነፀብራቅ



አቶ አደም አብደላ



አቶ ታለግን ተማም



አቶ ሞገስ ባልቻ

**ሳሙኤል ወንድሰን**

**ዜና ሐተታ**

ጠዋት 12 ሰዓት በመስቀል አደባባይ የእስልምና፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እና የሌላ እምነት ተከታዮች የጋራ ዓላማ ይዘው ተሰብስበዋል። ዓላማውም በዓለም ቅርስነት የተመዘገበውን የመስቀል ደመራ በዓል የማክበሪያ ሥፍራን ለማፅዳት ያለመ ነው።

በዚህ ተወዳጅ ሥፍራ ላይ የተለያዩ እምነት ተከታዮች መጥረጊያ እና የፅዳት ዕቃዎች ይዘው በአንድነት አካባቢውን እያፀዱ ነው። ትብብራቸው እና አንድነታቸው በተግባራቸው ጎልቶ ይታያል። አቶ አደም አብደላ በፅዳት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ከተሳተፉ የእስልምና እምነት ተከታዮች አንዱ ናቸው።

አቶ አደም አብደላ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ በክርስትና እምነት ተከተዮች ለሚከበረው የመስቀል በዓል ድምቀት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠርና የእምነቱ ተከታዮች በዓሉን በደስታ እንዲያከብሩ የአጋርነት ሚናቸውን ለመወጣት የማክበሪያ ሥፍራውን እያፀዱ መሆኑን ነው የተናገሩት።

በዓሉ የሚከበርበትን ስፍራ በማፅዳት የበኩላቸውን ተሳትፎ እያደረጉ መሆኑን የገለጹት አቶ አደም አብደላ፤ ከክርስትና እምነት ተከታዮች ጋር ያለንን የአብሮነትና የመቻቻል ባሕል አጠናክረን ለመቀጠል በዓሉ የሚከበርበትን ስፍራ አፅድተን ለበዓሉ ዝግጁ አድርገናል ብለዋል።

የሁሉም እምነት ተከታዮች በኅብረት ጠንክረን በመሥራት ድህነትን ከሀገራችን ማጥፋት ይጠበቅብናል ያሉት አቶ አደም አብደላ፤ በሀገሪቱ የሚከበሩ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ በዓላትን በሠላም፣ በፍቅርና በአንድነት የማክበር ልማድን ማስቀጠል እንደሚገባ ነው የተናገሩት።

የመስቀል በዓል የሚከበርበትን ስፍራ በማፅዳት የእስልምና እምነት ተከታዮች ያሳዩት አኩሪ ተግባር የአብሮነት እሴታችን ነፀብራቅ ነው ያሉት አቶ አደም አብደላ፤ የመስቀል ደመራ በዓል ከኢትዮጵያም አልፎ የዓለም ቅርስ በመሆኑ ለጋራ ሀብታችን በጋራ ልንቆም ይገባል ነው ያሉት።

አቶ ታለግን ተማም በበኩላቸው፤ "እኛ የእስልምና እምነት ተከታዮች ያፀዳነው የክርስትና እምነት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በዓል መሆኑን በመረዳት ነው። ይህ በጎ ተግባር ዘመን ተሻጋሪ የአንድነትና የአብሮነት ፅናት ማሳያ በመሆኑ ሊጠበቅና ሊጠናከር ይገባል ይላሉ።

የተካሄደው የፅዳት ዘመቻ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘመን የዘለቀ ኅብረትና አንድነት መገለጫ ነው ያሉት አቶ ታለግን ተማም፤ በዚህም አዲስ አበባ የተለያዩ እምነት ተከታዮችና ብሔር ብሔረሰቦች መዲና የመሆኗን እውነታ ለትውልድ ለማስተማር በተግባር አጋርነታችንን እና ወንድማማችነታችንን አሳይተናል ነው ያሉት።

የፅዳት ዘመቻ መርሐ ግብሩን ያስጀመሩት የከተማ አስተዳደሩ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ኃላፊ አቶ ሞገስ ባልቻ፤ "እኛ ኢትዮጵያውያን አንድነታችን የጥንካሬያችን መሠረት፣ መከባበራችን የአብሮ መኖራችን ምስጢርና መለያችን ሆኖ ዘመናትን ተሻግረናል። ትውልዱም ይህንን ድንቅ ጥበብና ምስጢር ይዞ እንዲቀጥል እንሠራለን "ብለዋል።

የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ መምህር የማነ ዘመንፈስ ቅዱስ በበኩላቸው የመስቀል በዓልን የምናከብረው በመስቀሉ የተሠራልንን ድንቅ ተዓምር ለመግለጽ ነው። ቤተክርስቲያኗ በመስቀሉ የምታስተምረው ሠላምን ነው። ይህንን ሠላም በትብብር ማፅናት የሁላችንም ኃላፊነት መሆኑን ይገልጻሉ።

የአዲስ አበባ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ ዋና ፀሐፊ መጋቢ ታምራት አበጋዝ የመስቀል በዓል ከሃይማኖት መገለጫነቱ ባሻገር በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በቅርስነት የተመዘገበ በመሆኑ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ኩራት መሆኑን ጠቅሰዋል።

በዓሉ እሴቱን በጠበቀ መልኩ ሲከበር ኢትዮጵያውያውያንን በዓለም አደባባይ በማንገሥ አንድነታችንን ያጠናክራልና በልዩ ትኩረት ልናከብረው ይገባል ሲሉ ይናገራሉ።

በዓሎቻችን የሁሉም ኢትዮጵያዊ ድምቀቶች፣ ኩራቶች እንዲሁም ኅብረብሔራዊ አንድነታችንን የምናጎለብትበት በመሆናቸው የሚከበሩበትን ስፍራዎች በጋራ በማፅዳትና በማስዋብ አብሮነታችን የመቻቻልና የመተሳሰብ በባሕላችን ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት በመርሐግብሩ ላይ ተገልጿል።



# በዞኑ ከመኸር እርሻ ከሰባት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

## - ከ150 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በዘር ተሸፍኗል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በ2016/17 የምርት ዘመን ከመኸር እርሻ ከሰባት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚጠበቅ የሀድያ ዞን ግብርና መምሪያ አስታወቀ። 150 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በዘር መሸፈኑም ተመላክቷል።

የዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ ሀብታሙ ታደሰ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ በመኸር እርሻ ሰብል ልማት ዘርፍ 149 ሺህ 828 ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዶ ከ150 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት መሸፈን ተችሏል። ከዚህም ከሰባት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል።

በዘር ከተሸፈኑት ሰብሎች መካከልም ስንዴ፣ ጤፍ፣ ገብስና ባቄላ እንደሚገኙበት ጠቅሰው፤ በዞኑ በ344 ቀበሌዎች በ2 ሺህ 153 ክላስተሮች ከ51 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በስንዴ፣ በጤፍና በገብስ ዘር የተሸፈነ መሆኑን ተናግረዋል።

በክላስተር ልማቱ 74 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች እየተሳተፉ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ አሁን ላይ ሥራው በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ዞን ምርትና ምርታማነትን ለአደጋ ሊያጋልጥ የሚችል የበሽታና የአየር ሁኔታ አለመኖሩን አውስተው፤ የግብርና ባለሙያዎች በሁሉም ቀበሌዎች ተመድበው የሰብል ጥበቃና የአረም ቁጥጥር ሥራ እየሠሩ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

አርሶ አደሩ ምርት በሚሰበስብበት ወቅት ለብክነት እንዳይዳረግ ፍላጎታቸውን መሠረት ባደረገ ሁኔታ በኮምባይነር በመታገዝ ምርቱን ለመሰብሰብ ታቅዶ እየተሠራ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

በራስ አቅም ራስን በመቻል ተረጂነትን ለማስቀረት በአርሶ አደሮች ላይ የአመለካከት ለውጥ በማምጣት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑንም አስረድተዋል።

በመኸር የታቀደውን ምርት ለማግኘት ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ እስከ እንክብካቤውና ድህረ ምርት ድረስ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ኃላፊው እንደገለጹት፤ የተለያዩ የዕፅዋት በሽታ መከላከያ ዘዴዎችን ለአርሶ አደሮች የማስተዋወቅ ሥራ ተከናውኗል።

ከስንዴ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ዋግና የተለያዩ በሽታዎች በምርታማነቱ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቀድሞ የመከላከል ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

የግብርና ግብዓቶችን በወቅቱ ለአርሶ አደሮች ተደራሽ በማድረግ የተቀናጀ የመኸር ወቅት ግብርና በታቀደው ልክ ለማሳካት በቅንጅት እየተሠራ እንደሚገኝ ሀብታሙ (ዶ/ር) አመላክተዋል።

# ታሪክ መስካሪው አዳራሽ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

"ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለአፍሪካውያን ሕዝብ የወደፊት እድገት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ከአሳባቸው አንቅተው መርቀው የመሠረቱትን ይህን ሕንጻ ጥር 29 ቀን 1953 ዓ.ም የአፍሪካ አዳራሽ ብለው ሰየሙት" የሚል ጽሑፍ በአዳራሹ ግድግዳ ላይ ሰፍሮ ይገኛል።

ከ62 ዓመታት በፊት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ አዳራሹን መርቀው በከፈቱበት ወቅት" የአፍሪካ አዳራሽ ብለን የሰየምነው ይህ ሕንጻ የአፍሪካ ሕዝቦች ወደተከበረው ዓላማቸው እንዲደርሱ የሚረዳና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ መጀመሪያውን የሚይዝ በመሆኑ መንፈስን የሚያነቃቃ ቋሚ መታሰቢያ ሆኖ ይኖራል" ሲሉ ያደረጉት ትንቢታዊ ንግግር እውን ሆኗል።

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ማክሰኞ ጥር 30 ቀን 1953 ዓ.ም ይዞት በወጣው የቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ንግግር "በውስጡ የሚገኙ የስብሰባ አዳራሾችና የጽሕፈት ቤቶች የአፍሪካውያንን ዓላማና ምኞት ከፍጻሜው ለማድረስ ዓይነተኛ ግባቸውና ተግባራቸው አድርገው የሚደክሙ ወንዶችና ሴቶች የሚሠሩባቸው ይሆናሉ" ባሉት መሠረት፣ ዛሬም የአፍሪካ ብርቅዬ ልጆች ለአፍሪካ ጥቅም የሚደክሙበት ስፍራ ሆኖ በአዲስ ገጽታ ፈክቷል።

ሕንጻው እ.አ.አ 1963 ሠላሳ ሁለት የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች በመምከር የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን የመሠረቱበት ታሪካዊ አዳራሽ ነው። በዘመናት ውስጥ በርካታ ስብሰባዎችንና የአፍሪካ መሪዎችን ውሳኔዎች አስተናግዷል።

ስለአፍሪካ አዳራሽ ሲነሳ አብረው የሚነሱት በዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በአዳራሹ መስኮቶች ላይ የተሳሉት የመስታወት ስዕሎች የአፍሪካን የትናንት ጭቆና እና መጻኢ ተስፋ አመላካች መሆናቸው ይነገራል።

ይህ ታሪካዊ ሕንፃ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በኋላ በመንግሥታቱ ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ ታሪካዊ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ ዘመኑን የዋጀ ገጽታ እንዲላበስ ተደርጎ ጥገና እና ዕድሳት ተከናውኖለት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። ዕድሳቱም በ2017 ዓ.ም ጥቅምት ወር አጋማሽ እንደሚመረቅ ተጠቁሟል።

በተመድ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የአፍሪካ አዳራሽ አስተዳደር የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አንቶንዮ ባእዮ እንደሚገልጹት፤ እድሳቱ ከ61 ዓመታት በላይ የቆየውን አዳራሽ ታሪካዊ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ ዘመኑን የዋጀ ገጽታ እንዲላበስ እያስቻለው ይገኛል። በተለይም የአፍሪካን



የአፍሪካ አዳራሽ አሁናዊ ገጽታ

ታሪካዊ አመጣጥ፣ አሕጉሪቱ አሁን ያለችበትን እና የወደፊት ሁኔታዋን የሚያሳይ እንዲሆን ተደርጓል።

አዲሱ የሕንጻው ዲዛይን ዘላቂ፣ ማራኪ እና ጎብኚዎችን የሚስብ ሆኖ የተቀረጸ ሲሆን ብዛት ያለው የሕንፃው ክፍል በአዲስ መልክ ዕድሳት የተደረገለት ነው። የተሠራው የዕድሳት ሥራም ሕንጻውን የማደስ ብቻ ሳይሆን የማዘመን ተግባርንም እንደሚያጠቃልል የሚጠቁሙት አንቶንዮ ባእዮ፤ ዕድሳቱ የአወቃቀርና ቴክኖሎጂ ማዘመን፣ የተሻለና ምቹ አገልግሎት ያለው፣ ቅርሶችን የጠበቀ እና ሌሎች ታሪካዊ ይዘቶችን ያጎላ ሆኖ መከናወኑ የፕሮጀክቱ ትልቅ ስኬት እንደሆነ ነው የሚያነሱት።

ለእድሳት ሥራው 57 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ በጀት እንደወጣ፤ ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ ብቃት ያላቸው ሥራ ተቋራጮች (ኮንትራክተሮች) ዕድሳቱን በልዩ ትኩረት እያከናወኑት እንደሚገኙና ዕድሳቱ ከአፍሪካ ታሪክ እና ትዝታ ጋር የተያያዘ መሆኑንንም አንቶንዮ ባእዮ ይገልጻሉ።

ከሕንፃው ዲዛይን በስተጀርባ ካሉት ዋና ዋና መርሆዎች ውስጥ አንዱ የአፍሪካን ታሪክ ባከበረ መልኩ ዕድሳቱን ማከናወን ነው። የዕድሳት ሥራው ዓላማ ሕንጻውን ወደነበረበት በመመለስ አዳራሹን የላቀ የድምፅ ስርጭትና ፈጣን ትርጉም በሚሰጥ ቴክኖሎጂዎች መቀየር እንደሆነ አንቶንዮ ባእዮ ያስረዳሉ።

እድሳቱ በሥነ ሕንፃ፣ በባሕልና ታሪካዊ እሴትን በጠበቀ መልኩ እየተከናወነ ሲሆን፤ በጄኔቫና በኒውዮርክ ከሚገኙ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጋር ተመሳሳይነት እንዲኖረው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል ሲሉም ያብራራሉ።

የአፍሪካ አዳራሽ ፕሮጀክት የሲቪል እና አርክቴክቸራል ሥራዎች ሱፐርቫይዘር ኢንጂነር ጌታቸው አርዓያ በበኩላቸው፤ ሕንጻው በራሱ ቅርስ ነው። በውስጡ የእንጨት፣ የኪነጥበብና ሌሎችም ሥራዎች ይገኙበታል። ከዚህ ውስጥም የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የጥበብ ሥራ አንዱ ሲሆን ዕድሳቱም ይህንን ለማስጠበቅ ትልቅ ሚና አለው ይላሉ።

እንደ ኢንጂነር ጌታቸው ገለጻ፤ እድሳቱ አራት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት። እነዚህም የሕንጻውን መዋቅራዊ ደኅንነት በማረጋገጥ ለቀጣይ ተጨማሪ ዓመታት እንዲቀጥል ማድረግ፤ የኮንፈረንስ ሥርዓቱን ማዘመን፤ የሕንጻውን ቅርስነት ማስጠበቅ እና ሕንጻው ለማኅበረሰቡ ዕይታ ክፍት እንዲሆን ማስቻል ናቸው።

አዳራሹ ፓን አፍሪካኒዝም ተቋማዊ ቅርጽ የያዘበት ቦታ መሆኑንና አፍሪካውያን በጉዳዮቻቸው ዙሪያ የመከሩበት የመጀመሪያው ስፍራ እንደሆነ የሚገልጹት ኢንጂነር ጌታቸው፤ ዕድሳቱ የአዳራሹን የሥነ-ሕንፃ ውበት ወደነበረበት መመለስ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ አንድነት እና የእድገት ምልክት የሆነውን ቦታ ዘመናዊ እንዲሆን ማስቻል ነው ይላሉ።

የዕድሳቱ አካል የሆነውና በመቋቋም ላይ የሚገኘው ቋሚ የኤግዚቢሽን ማዕከል ከሕንጻው ታሪክ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ሚና ምን እንደሚመስል በቋሚነት የሚታይበትና የአፍሪካ የፖለቲካ ታሪክ የሚገለጽበት ክፍልን ጨምሮ በተመድ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ታሪክን የሚያሳዩ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች እንዳሉት ኢንጂነር ጌታቸው ያወሳሉ።

ኢንጂነር ጌታቸው እንደሚገልጹት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በመቋቋም ላይ ለሚገኘው ቋሚ የኤግዚቢሽን ማዕከል ለተሸከርካሪ ማቆሚያ የሚሆን ተጨማሪ መሬት ሰጥቷል። እንዲሁም ማሊ፣ ሲዊዘርላንድ፣ ፖርቹጋል እና ኔዘርላንድ ለግንባታው የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል።

# መስከረምና ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዐቢይ ንጉሴ ይባላሉ። በቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት የቱሪዝም አሠልጣኝ መምህር ናቸው። በኢትዮጵያ የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት የሀገሪቱን ባሕል ለሌሎች ሀገራት ለማስተዋወቅና ለተተኪ ለትውልድ ለማስተላለፍ፣ ለኢኮኖሚያዊ እድገት፣ የማኅበረሰብን አንድነት ለማጠናከርና ቱሪስቶችን ለመሳብ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ ሲሉ ያስረዳሉ።

በኢትዮጵያ የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት አካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ ሳይሆን፤ ባሕልን፣ ማንነትን፣ እሴትን፣ ትውፊትን፣ አንድነትንና እምነትንና አጠናክሮ ለትውልድ በሚያሻግር መልኩ ነው። በመሆኑም የበዓላቱን እሴትና ትውፊት በጠበቀ መልኩ አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል ሲሉ ያብራራሉ።

የአደባባይ በዓላትን ለመታደም ለሚመጡ እንግዶች በዓሉ በሚከበርባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ተጨማሪ የቱሪስት መዳረሻዎችን ማስጎብኘት ይገባል። በዚህ ደግሞ ተጨማሪ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን ማስተዋወቅ እና የቱሪስት የቆይታ ጊዜን በማራዘም ለአካባቢው ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት ይቻላል ይላሉ።

ኢትዮጵያ እምቅ የቱሪዝም ሀብት አላት የሚሉት አሠልጣኙ፤ እነዚህን የቱሪዝም ሀብቶች ለማስተዋወቅ በአደባባይ የሚከበሩ በዓላት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ በመሆኑ በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ ያስረዳሉ።

የቱሪዝም ጋዜጠኛው ሄኖክ ስዩም በበኩሉ፤ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚከበሩት የአደባባይ በዓላት የኢትዮጵያውያን ሃይማኖት፣ ባሕል እና ትውፊት በስፋት የሚንፀባረቁበት በመሆኑ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች መሳብና ማቆየት የሚችሉ ናቸው ይላል።

ይህም ለቱሪዝም እድገትና ለአካባቢው ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ ሚና ያለው በመሆኑ፤ ሁሉም በዓላቶች በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገቡና እንዲታወቁ ማድረግ እንደሚገባ ይገልጻል።

የአደባባይ በዓላቱ በሚከበሩበት አካባቢዎች የበዓሉ ተሳታፊዎች የሚደምቁባቸውን አልባሳት፣ ጌጣጌጥ እና የአካባቢውን ባሕላዊ ምግቦች አዘጋጅቶ ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ መሆንና ማስተዋወቅ እንደሚገባም ይናገራል።

በኢትዮጵያ የአደባባይ በዓላትን ወቅቱን ጠብቆ ከማክበር ባለፈ፣ ባሕላዊ እሴቱን ለማጎለበት፣ በቅርስነት ለመጠበቅ፣ ለሌሎች ሀገራት ለማስተዋወቅና ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በትኩረት ሊሠሩ ይገባል ይላል።

የአደባባይ በዓላት ከቱሪዝም ዕድገት በተጨማሪም ለኪነጥበብ እድገትና ለከያኒዎች መፈጠር ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክት ይናገራል።

በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት ማኅበረሰብን ከማኅበረሰብ ለማገናኘት፣ ባሕልን ለማስተዋወቅ፣ አብሮነትን ለማሳደግ፣ በጎ እሴቶችን ለተተኪ ትውልድ ለማስተላለፍ ጉልህ ሚና አላቸው የሚሉት ደግሞ በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የባሕል ጥናት መምህርና የአዲስ ዓለማየሁ የባሕል ጥናት ተቋም ዳይሬክተር መስፍን ፈቃዴ (ዶ/ር) ናቸው።

የአደባባይ በዓላት የአንድን ማኅበረሰብ ምንነት፣ ባሕል፣ ታሪክና አመጋገብ ለሌላው አጉልተው ያሳያሉ። የበላይና የበታች ሳይኖር እርስ በእርስ ተከባብረውና ተዋደው እንዲኖሩም ያስችላል ሲሉ ይናገራሉ።

መስፍን (ዶ/ር) እንደሚሉት፣ የአደባባይ በዓላት ሲከበሩ የሀገር በቀል አልባሳትንና ጌጣጌጦችን በማድረግ ሊሆን ይገባል። ከሀገሪቱ ባሕል ውጪ ያሉ አልባሳትና ጌጣጌጦች ኢትዮጵያን ሊገልጹና ሊያስተዋውቁ ስለማይችሉ ሁሉም እንደ እድሜ ደረጃቸው የአካባቢያቸውን የባሕል አልባሳት በመልበስ ማክበር ይገባል።

ሌሎች ሀገራት ከኢትዮጵያ ጋር በባሕል፣ በኢኮኖሚ፣ በቱሪዝም፣ በፖለቲካውና ፍልስፍና ሊተሳሰሩ የሚችሉት እኛ እኛን ሆነን ስንቀርብ ነው ይላሉ።

አንድ ማኅበረሰብ ከባሕል ወጣ ማለት ዓሣ ከባሕር ወጣ እንደማለት ነው የሚሉት መስፍን (ዶ/ር)፤ ዓሣ በባሕር ውስጥ ሕልውናው እንደሚጠበቀው ሁሉ ሀገርም በባሕል ሲደገፍ ሕልውናው ይቆያል። ባሕል የሀገር ሕልውና እና የማኅበረሰብ መንፈሳዊና ቁሳዊ መገለጫ በመሆኑ እሴቱን ጠብቆ ለትውልድ ማሻገር ይገባል ሲሉ ያመላክታሉ።

በራሱ ባሕል የሚኮራ ትውልድን ለማፍራት መንግሥት፣ ወላጆችና መምህራን ድርሻቸው ከፍተኛ ነው የሚሉት መስፍን (ዶ/ር)፤ ወላጆች ለልጆቻቸው በሀገሪቱ የሚከበሩ የሃይማኖታዊና ባሕላዊ በዓላትን አንድምታ በቤታቸው ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል።

መንግሥትም የበዓላቱን ትርጉም በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በማካተት ልጆች በትምህርት ቤት እንዲማሩት በማድረግ ከሀገሪቱ ባሕል፣ እምነት፣ ወግና ሥርዓት ጋር የሚጻረሩ መጤ ባሕልን መከላከል ይቻላል ይላሉ።

አንድምታቸው በቃል ብቻ እየተነገረ ያለ ባሕልና ታሪኮችን በጽሑፍና በምስል በማደራጀት የውጭው ማኅበረሰብ በሚያውቁት ቋንቋ ተርጉሞ በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን በማቅረብ ቱሪስቶችን መሳብ ይቻላል ሲሉ ያስረዳሉ።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ስለሺ ግርማ በበኩላቸው፤ በመስከረም ወር የሚከበሩ የተለያዩ በዓላት ለቱሪዝም ገቢ ዕድገት ያላቸውን ሰፊ ጠቀሜታ በመረዳትና ከክልሎች ጋር በመነጋገር ሚኒስቴሩ የተለያዩ የጉብኝት ጥቅሎችን አዘጋጅቶ እያስተዋወቀ ይገኛል ይላሉ።

በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የቱሪስት መስሕቦችን በመለየትና በማስተዋወቅና የገቢ ምንጭ ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የተጠናከረ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ እንደሚገባ ያስረዳሉ።

በመስከረም ወር የሚከበሩ በዓላቶች ከሃይማኖታዊና ባሕላዊ ትውፊት ባለፈ ቱሪዝሙንና ኢኮኖሚውን ለማነቃቃት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያላቸው ናቸው። በዓላቱን ለመታደም የሚመጡ እንግዶችን በሚሄዱበት አካባቢ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥልጠና መሰጠቱን ይናገራሉ።

በዓላቱ በሚከበሩበት ወቅት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎችን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ዜጎች በልዩ ሁኔታ ማስጎብኘት እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

# “ደብተር ስላላገኘን በትምህርታችን ላይ ተፅዕኖ ፈጥሮብናል”

*- የአዲስ ከተማና የዳግማዊ ምኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች*

# “በአንድ ሳምንት ውስጥ ደብተሮች ለተማሪዎች ይሰራጫሉ”

*- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ*

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የ2017 ዓ.ም የትምህርት መርሐግብር መስከረም 6 ቀን 2017 ዓ.ም የተጀመረ ቢሆንም እስካሁን የደብተር አቅርቦት ስላልደረሳቸው በትምህርታቸው ላይ ተፅዕኖ እንደፈጠረባቸው በአዲስ አበባ ከተማ የሚማሩ ተማሪዎች ገለጹ። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ በበኩሉ ከዛሬ ጀምሮ በአንድ ሳምንት ውስጥ 9 ሚሊዮን 125 ሺህ በላይ ደብተሮችን ለተማሪዎች አሰራጭቶ ለማጠናቀቅ መታቀዱን አስታውቋል።



የአዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ተማሪ ሕሊና ደምሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸችው፤ የ2017 ዓ.ም የትምህርት ዘመን መርሐግብር መስከረም 6 ቀን የተጀመረ ቢሆንም እስካሁን የመማሪያ ደብተር አልተሰጠንም።

በዚህም በየትምህርት አይነቱ በየቀኑ ስለሚጻፍ ደብተር ከሌለ ወደኋላ የሚያስቀር መሆኑን ተናግራ፤ ከማጥናት ይልቅ ያለፉትን ማስታወሻ በመገልበጥ ጊዜ ማባከኑ ትምህርቷ ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥርባት መሆኑንም ጠቅሳለች።

ደብተር ስላልተሰጠን ካለፈው ዓመት በተረፈ ደብተር እየተማርኩ ነው የምትለው ሌላዋ የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነጃት ጌድዮን፤ ዘንድሮ 12 የትምህርት አይነት እየተማረች ቢሆንም በአንድ ደብተር ላይ 3 የትምህርት አይነት ማስታወሻ ለመገልበጥ መገደዷን ተናግራለች።

በመንግሥት እየቀረበው ያለው የደብተር እና የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) አቅርቦት መግዛት ለማይችሉ ወላጆች ችግር የሚያቀል መሆኑን ጠቅሳ፤ በወቅቱ ተደራሽ አለመሆኑ ተማሪው ላይ ከሚያሳድረው ተፅዕኖ ባለፈ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወላጆች ለድጋሚ ወጪ ይዳርጋል ስትል ተናግራለች።

የአዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ እንዳልካቸው ደጀኔም፤ የ2017 የትምህርት ዘመን መርሐግብር መስከረም 6 ቀን 2017 ዓ.ም የተጀመረ ቢሆንም የተማሪዎች ግብዓት ከማሟላት አንጻር የተወሰኑ እጥረቶች አሉ ብለዋል።

ይህንንም ለመቅረፍ ትምህርት ቤቱ አምና ከተረፈው የደብተር ግብዓት ለተወሰኑ ተማሪዎች የተሰጠ ቢሆንም በቂ አይደለም። ተማሪዎች አዲስ ደብተር ባይገዙም አምና በተረፈው እንዲማሩ የተደረገ ሲሆን፤ በሂደት ይሟላል የሚል እምነት እንዳላቸው አብራርተዋል።

ደብተር አቅርቦት መዘግየት ተማሪዎች ማስታወሻ ለመያዝ ከመቸገራቸውም በላይ በዘገየ ቁጥር መማር ማስተማሩን በማወክ የተወሰነ እንቅፋት ስለሚፈጥር ቀደም ብሎ መቅረብ አለበት ብለዋል።

በመንግሥት የሚደረገው የትምህርት አቅርቦት ድጋፍ ለመማር ማስተማሩ ብቻ ሳይሆን ለወላጆች ኢኮኖሚያዊ ጫናም ለማቃለልና የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ግብዓት ወሳኝ ነው ያሉት ርዕሰ መምህሩ፤ በተለይም በዝግጅት ምዕራፉ ላይ ቀደም ተብሎ የመማሪያ ግብዓትን ቢመጡ ዝግጅቱን ሙሉ ያደርገዋል ብለዋል።

የዳግማዊ ምኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ በላይ ወልደጻዲቅ በበኩላቸው፤ ትምህርት በተጀመረበት ዕለት ለተገኙ ደብተር እና ዩኒፎርም የታደለ ቢሆንም ከግማሽ በላይ ተማሪዎች አላደረሳቸውም።

የተሰጣቸው ተማሪዎች በየክፍል ደረጃቸው በሚማሩት የትምህርት አይነት ልክ የተሰጣቸው ሲሆን ግብዓቱ ሲገባ አንድ ደርዘን ከአንድ ስኩየር ደብተር ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል።

የትምህርት ግብዓት በተለይም ለተማሪዎች የትምህርት ክትትልና ማስታወሻ ለመያዝ ወሳኝ የሆነው ደብተር በትምህርታቸው ላይ ተፅዕኖ እንዳይፈጥርና በቁሳቁስ እጥረት ምክንያት ከትምህርት ገበታ እንዳይሰናከሉ ትምህርቱ ከመግፋቱ በፊት መቅረብ አለበት ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ የግብዓት አቅርቦት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ምነወር ኑረዲን ለኢፕድ በሰጡት ምላሽ፤ የተማሪዎች የትምህርት ግብዓት በተለይም የደብተር አቅርቦት የግዢ ሂደት ቀደም ብሎ የተጀመረ ቢሆንም በአሠራር ሂደት ላይ በተፈጠሩ ተግዳሮቶች ምክንያት የተወሰነ መዘግየት እንደነበር ገልጸዋል።

ኤጀንሲው በከተማዋ እና በከተማዋ ዙሪያ ባሉ አካባቢዎች የደንብ ልብስ እና የደብተር አቅርቦት የሚያካሄድ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዘንድሮ የትምህርት ዘመንም በአጠቃላይ ለአንድ ሚሊዮን ሠላሳ አራት ሺህ በላይ ተማሪዎች የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) እና ደብተር የሚቀርብ መሆኑን ገልጸዋል።

በዚህም በመጀመሪያ ዙር ደብተር ስርጭት 739 ሺህ ደብተር የቀረበ ቢሆንም በቂ አለመሆኑን አስታውቀው፤ ከዛሬ ጀምሮ በአንድ ሳምንት ውስጥ 9 ሚሊዮን 125 ሺህ በላይ ደብተሮችን ለተማሪዎች አሰራጭቶ ለማጠናቀቅ መታቀዱን ገልጸዋል።

አቶ ምነወር እንደገለጹት፤ በዚህ የተማሪዎች የትምህርት ግብዓት ማሟላት ተግባርም ትልቅ በጀት የሚጠይቅና በጊዜ እና ግብዓት አቅርቦት ሂደት የመንግሥትን አሠራርና ሂደት በተከተለ መልኩ ይካሄዳል።

በሂደቱ ላይ የግብዓት አቅራቢ፣ የመንግሥት ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች ብሎም ሰፊ ቁጥር ያለው የተማሪዎችን ጨምሮ በርካታ ተዋንያን የሚሳተፉበት በመሆኑ በርካታ ተግዳሮቶች ያጋጥማሉ ብለዋል።

በመሆኑም ከተማ አስተዳደሩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የምርቶቹን ብዛትና ጥራት ለማረጋገጥ እና ችግሮችን ለመቅረፍ የተለያዩ የአሠራር ማሻሻያዎች እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ኤጀንሲው በዚህ ዓመት የታየውን ችግሮችና መልካም ጎኖች በትኩረት በመለየት በሚቀጥለው የተሻለ አሠራር በመፍጠር ትምህርት ግብዓት አቅርቦቱን ከትምህርቱ እኩል ለማቅረብ ይሠራል።

በዚህ ትውልድን ለመገንባት ዋነኛ ዘርፍ በሆነው ትምህርት ላይ ተሳታፊ የሆኑ አካላት የሚጠበቅባቸውን ሚና እና ኃላፊነት መወጣት እንደሚገባ አቶ ምነወር ተናግረዋል።

# ዓባይን መነሻ ያደረገው ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ይህ የኢትዮጵያ የልማት ፍላጎት ግን የግብፅን ፍራቻ ከፍ እንዳደረገው ይጠቀሳል። ካይሮ የኢትዮጵያን ኃያልነት በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ለግብፅ ታሪካዊ የበላይነት ፈተና ሊሆን እንደሚችል ታያለች። እኤአ በ2020 በአልጀዚራ በኩል የወጣ ዘገባ የግብፅ ባለሥልጣናት፤ ኢትዮጵያ በዓባይ ግድብ የቀጣናውን የኃይል ሚዛን ልትቀይር ትችላለች በሚል ስጋት የኢትዮጵያን “መነሳት” በከፍተኛ ስጋት ይመለከቱታል” ብሏል።

ኢትዮጵያ ፕሮጀክቱን ወደፊት ስትገፋ፣ ግብፅ በድብቅ እርምጃዎችን በመውሰድ የተለያዩ ተፅዕኖ በማሳደር ተፎካካሪዋን ለማተራመስና ሠላም ለመንሳት ጥረት እንደምታደርግም ተመላክቷል። በቅርቡ ከሶማሊያ እና ከኤርትራ ጋር እያደረገች ካለው ግንኙነት ባሻገር ኢትዮጵያን የመክበብ አዝማሚያ በሚታይበት መልኩ በደቡብ ሱዳን ሠላም አስከባሪዎችን ለመላክ ማሰቧ የተለየ አንድምታ እንዲኖረው አድርጓል። የግብፅ አሉታዊ እንቅስቃሴዎች ለአካባቢው አለመረጋጋት አስተዋፅዖ እንደሚያደርጉም ባለሙያዎች ይናገራሉ።

የቦሮ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የውጭና ዓለም አቀፍ ዘርፍ ኃላፊ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባል የሆኑት መብራቱ ዓለሙ (ዶ/ር) እንደሚያብራሩት፤ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና አሁን ላይ አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል። የዓባይ ግድብ ግንባታ እየተጠናቀቀ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ “ዓባይ የእኛ ነው” በሚል ትርክት ግብፅ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረገች ትገኛለች። የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕር በር ጉዳይን በሚመለከት ከሶማሌላንድ ጋር ያደረገውን ስምምነት አስመልክቶ አሉታዊ ጎን በመያዝ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ግንኙነት እየፈጠረች ነው። አጠቃላይ ቀጣናው ላይ ችግር እንዲፈጠር ፍላጎቷን በጉልህ እያሳየች ነው።

ይህ የግብፅ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ ሠላማዊ ሀገር እንዳትሆንና አንድነቷን እንዳትጠብቅ እንዲሁም ሌሎች የልማት ሥራዎችን እንዳትሠራ የሚካሄድ ሩጫ እንደሆነ ይጠቅሳሉ። “የዓባይ ግድብ ግንባታ ከተከናወነ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ አቅም ያላት ሀገር ትሆናለች” የሚል ስጋት ውስጥ መሆናቸውንም አንስተዋል። በዚህም የኢትዮጵያ ተሰሚነቷ እያደገ እንዳይመጣ ጫና ለመፍጠርና እድገቷንም ለማስተጓጎል ብዙ ርቀቶችን እየተጓዙ ይገኛሉ ነው ያሉት።

ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያን በተለያዩ መንገዶች ለመክበብ ሙከራዎችን ከማድረግ ባሻገር ሀገር ውስጥ የሚስተዋሉትን ግጭቶች ጭምር የማባባስ ሥራ እንደምትሠራ ጠቅሰዋል። በዚህ ምክንያት በአሁን ወቅት በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ያለው የፖለቲካ ትኩሳት እየጎላ መምጣቱን አመላክተዋል። ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላትን ዲፕሎማሲ ይበልጥ ልታጠናክር እንደሚገባም ይመክራሉ።

መብራቱ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፤ ግብፅ በኢትዮጵያ የተጀመሩ የለውጥ ሥራዎችን በማደናቀፍ ዘላቂ ልማት እንዳይኖር ግጭት እንዲነሳሳና ርስ በርስ ችግሮች ተነስተው ሀገሪቷ ተረጋግታ የልማት ፕሮጀክቶችን እንዳትሠራ የመግታት እንቅስቃሴ ነው እያደረገች ያለችው።

ከዓባይ ወንዝ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የነበሩ ጥንታዊ ስምምነቶችን በመያዝ ጫና ለመፍጠር እየተንቀሳቀሰች ነው። ከዚህ አኳያም ኢትዮጵያም ከዚህ ቀደም ስታከናውናቸው የነበሩ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን አጠናክራ በልዩ ትኩረት መሥራት እንደሚገባም ነው ያስገነዘቡት።

ዘ ኢኮኖሚስት እኤአ በ2021 ይዞት በወጣው ዘገባ በግብፅ እና በኢትዮጵያ መካከል ያለው የዓባይ ውሃ ውዝግብና ግብፅ የምትከተለው ስትራቴጂ እያደገ የመጣውን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለመግታት ተፅዕኖ እንዳለው ተገልጿል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢትዮጵያ በዓባይ ግድብ ፕሮጀክት ሉዓላዊነቷን እና ቀጣናዊ መሪነቷን ለማስከበር ቆርጣ መነሳቷን እና በአንጻሩ የግብፅ እንቅስቃሴ ወደ ግጭት ሊያመራ የሚችል አዝማሚያ ያለው መሆኑ ተመላክቷል። የዚህ ግጭት ውጤት ለምሥራቅ አፍሪካ መረጋጋት እና የወደፊት እድገት ትልቅ መዘዝ እንዳለውም ነው በወቅቱ የተገለጸው።

የኖርዌይ እውቅ የታሪክ ምሑር ተርጄ ቴቬት እኤአ በ2019 በአልሞኒተር ላይ እንዳስታወቁት፤ በግብፅና በኢትዮጵያ መካከል ያለው የዓባይ ወንዝ ውዝግብ መነሻው በቅኝ ግዛት ዘመን የተደረጉ ስምምነቶችን ተከትሎ ነው ይላሉ። እነዚህ የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነቶች ግብፅ በዓባይ ወንዝ ላይ ያላትን የበላይነት ያጎናፀፉ ሲሆን በተለይም የወንዙን ውሃ አብዛኛውን የምታበረክተውን የላይኛው ተፋሰስ ሀገር የኢትዮጵያን ጥቅም ችላ ያለ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ እነዚህን ያረጁ ስምምነቶች ፍትሐዊ ያልሆኑ እና የዘመናዊ እውነታዎችን እንደማይወክሉ በመቁጠር ስትቃወማቸው መኖሯንና ግብፅም ይህንኑ መነሻ በማድረግ ኢትዮጵያ ላይ ጫናዎችን ለመፍጠር የተለያዩ ሙከራዎችን ስታደርግ መቆየቷን አንስተዋል።

ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ተንታኙ አቶ ሙሳ ሼኮ በበኩላቸው፤ ግብፅ በኢትዮጵያ የውስጥና የቀጣናዊ ጉዳዮች በተለይም በዓባይ ተፋሰስና በአፍሪካ ቀንድ ጉዳይ ላይ የፈጸመችው የረጅም ጊዜ ጣልቃ ገብነት እንቅስቃሴዋ ሰፋ ያለ ጂኦፖለቲካዊ አንድምታ እንዳለው ይገልጻሉ። የግብፅ በኢትዮጵያን ዙሪያ የመሸከርከሯ ሁኔታ ለራሷ ለግብፅ የሚበጅ እንዳልሆነም ይጠቅሳሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ ታሪክና ረጅም የዲፕሎማሲ ገድል ያለው፤ በጦርነትም ሆነ በዲፕሎማሲ የማሸነፍ ልምድ ያለው ነው በማለት፤ ግብፅ በአሁን ወቅት እየሠራች ያለው ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን መላ አፍሪካውያንን የሚያስቆጣ መሆኑን ተናግረዋል። ግብፅ በሶማሊያ እያደረገች ባለው እንቅስቃሴ ኢንቨስት አድርጋ ከነደፈቻቸው ቡድኖች ውጪ ሌሎቹ እየተቃወሟት ስለመሆኑም አንስተዋል።

ግብጽ አፍሪካ ውስጥ ትሁን እንጂ ጀርባዋን ለአፍሪካውያን ከሰጠች 50 ዓመታት ተቆጥረዋል። ሁሉም እንቅስቃሴዋ ከአፍሪካ ተቃራኒ የሆነ፤ ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ የሚለውን የአፍሪካውያንን አቋም የምትጻረር ናት። ይህ ሁሉ ተደምሮ ሰሞኑን በኢትዮጵያ ዙሪያ እያደረገች ያለው ተገቢ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች የዓለም አቀፍም ሆነ የአፍሪካውያንን ድጋፍ የሚያሳጣት መሆኑ አመላክተዋል።

የተፈጠረው አጋጣሚ ወደ ሶማሊያ ይውሰዳት እንጂ ተልዕኳቸውን የሚያስፈጽሙት ኤርትራን በማዕከላዊ ሥፍራነት በመጠቀም እንደሆነም አቶ ሙሳ አብራርተዋል። ይህም ባለፉት 33 ዓመታት ውስጥ የተንጸባረቀ ነው ብለዋል። ከዚህም ባሻገር በሌሎች ጎረቤት ሀገራት የምታደርገው እንቅስቃሴ ዓላማው ኢትዮጵያን ለማተራመስ እንደሆነ ተናግረዋል።

አቶ ሙሳ፤ “የግብፅ ተግባራዊ እንቅስቃሴና ፕሮፓጋንዳ ሌሎች ሀገራትንም እስከመጠቀም ሊደርስ ይችላል። ራሳቸውን ኃያል በማስመሰል አንዱ ሞቃዲሾ፣ ሌላው ደግሞ አስመራ ሊቆም ይችላል። ነገር ግን ኢትዮጵያ ባላት የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ልምድ ፈተናዎችን ትሻገራለች” ነው ያሉት።

በኒውዮርክ እየተካሄደ ከሚገኘው 79ኛው የተ.መ.ድ ጠቅላላ ጉባዔ ጎን ለጎን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ ከአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳይ ረዳት ሚኒስትር ሞሊ ፊ ጋር የጋራ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያይተዋል።

አምባሳደር ታዬ ለረዳት ሚኒስትሯ በአፍሪካ ቀንድ ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ገለጻ ባደረጉበት ወቅት ኢትዮጵያ በቀጣናው ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት እንዲሰፍን እያደረገች ያለውን ጥረት ትኩረት ሰጥተው አንስተዋል።

ሚኒስትሩ ሶማሊያን በተመለከተ ሞሊ ፊ ጋር በነበራቸው ውይይት ኢትዮጵያ ሽብርተኞችን በመዋጋት ረገድ በምታደርገው የተጠናከረ ጥረት ዙሪያ ገለጻ ያደረጉ ሲሆን ከድህረ አትሚስ በኋላ የሚኖረው የኃይል ሥምሪት ተግባራዊ ከመደረጉ አስቀድሞ የስምሪቱ ማዕቀፍ በጥንቃቄ መሠራት እንዳለበት ነው የተናገሩት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመስቀል ደመራ በዓል በሠላም እንዲከበር ሁሉም የሚጠበቅበትን ይወጣ!

የመስቀል ደመራ በዓል በኢትዮጵያ በርካታ ሕዝብ ታድሞባቸው ከሚከናወኑ የአደባባይ በዓላት መካከል አንዱ ነው። በየዓመቱ መስከረም 16 ቀን ከሰዓት በኋላ ጀምሮ በተለያዩ ሃይማኖታዊ ዝግጅት የሚከበረው የመስቀል ደመራ በዓል በሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓቶች ደምቆና ተውቦ ነው።

በበዓሉ ላይ በሊቃውንቱ መካከል የተዘጋጁ ያሬዳዊ ዝማሬዎች፣ የሰንበት ትምህርት ቤት መዘምራን መዝሙሮች፣ በንግሥት እሌኒ የተቀበረውን መስቀል ፈልጎ የማግኘትና የማስወጣት ሙሉ ትርዒት ለበዓሉ ታዳሚዎች ይቀርባል። በመሆኑም ይሄን በርካታ ሕዝብ የሚገኝበትን ሥነሥርዓቱን ሊያየው ለሚጓጓው ሃይማኖታዊ በዓሉ እሴቱን ጠብቆ በሠላም እንዲከበር ማድረግ ከእምነቱ ተከታዮች ብቻ ሳይሆን ከመላው ሕዝብ የሚጠበቅ ነው።

የመስቀል ደመራ በዓል የመከባበር፣ የመተሳሰብ፣ አብሮ የመብላት በጋራ የመደሰት የአደባባይ በዓል ነው። በመሆኑ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎች በዓሉን ለመታደም የደመራው ሥነሥርዓት ወደሚካሄድበት የመስቀል አደባባይ ያመራሉ። የበዓሉ ታዳሚዎች ሴቶች፣ ሕጻናት፣ አረጋውያንን ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ቱሪስቶች ናቸው ።

የመስቀል ደመራ በዓል ሃይማኖታዊ በዓል ከመሆኑ ባሻገር እንደ ሀገርም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሳይንስ፣ የትምህርትና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) በዓለም ቅርስነት ተመዝግቦ ይገኛል። ከውጪ ሀገር በራሳቸውም ሆነ ጥሪ ተደርጎላቸው በዓሉን ለማክበር የሚመጡ ቱሪስቶች በርካታ ናቸው። በመሆኑም የሀገራችንን ገጽታ የሚያጠፋ የሠላም መደፍረስ እንዳይከሰት አስቀድሞ የጥንቃቄ ሥራ መሥራት አለበት።

የመስቀል ደመራ ሃይማኖታዊ እሴቱንና ሥርዓቱን ጠብቆ እንዲከበር ማድረግ ያስፈልጋል። በአዲስ አበባ በተለይ በመስቀል አደባባይ በሚካሄደው ሃይማኖታዊ ሥነሥርዓት ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ከሀገር ውስጥና ከውጪ ስለሚመጣ ታዳሚው በዓሉን አክብሮ በሠላም እንዲመለስ ማድረግ ይገባል።

የሰንበት ትምህርት ቤቶችና በየአካባቢው ያሉ ወጣቶችም መንግሥት ከሚያሰማራቸው የፀጥታ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ለመሥራትና ሠላምን ለማስከበር ዝግጅት እያደረጉ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ሃይማኖታዊ በዓል ላይ ካለምንም ችግር በዓሉ በድምቀት እንዲከበር ማድረግ ያለበት ደግሞ እያንዳንዱ ታዳሚ ነው።

በእጁ ስለታም ነገሮችን ባለመያዝ፣ ተቀጣጣይ የሆኑ ነገሮችን ባለመጠቀም፣ እንደ ርችት ያሉ ሕዝብን የሚያውኩና ሠላምን የሚያደፈርሱ አይነት ድምፆች እንዳይኖሩ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ ይገባል። የሠላምና የፀጥታ ኃይሎችም ተገቢውን ፍተሻ በማድረግ እንዲሁም አስፈላጊው የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎችን በመሥራት በዓሉ በሠላም እንዲከበር በዓል አክባሪውም ሕዝብ በሠላም ወደ ቤቱ እንዲመለስ በጋራ መሥራት አስፈላጊ ነው።

የመስቀል ደመራ በዓል ሃይማኖታዊ በዓል በመሆኑም ታዳሚዎችም ሆኑ ሌሎች ከሃይማኖታዊ ሥርዓት ያልወጣ፣ የማንንም እምነት፣ ሃይማኖት እና ብሔር በማይነካ መልኩ በፍቅርና በመተሳሰብ በዓሉ እንዲከበር ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ፀብና ግጭትን ሊቀሰቅሱ ከሚችሉ ነገሮች መቆጠብ ይገባል።

ኢትዮጵያውያን ሁልጊዜም እንደሚባለው ሃይማኖተኛ ሕዝብ ነው። ሃይማኖተኛ ሕዝብ ደግሞ ችግር ቢያጋጥመው እንኳን ችግሩን በትዕግስትና በጥበብ ያልፋል። አሁንም በበዓሉ አከባበር ወቅት ወይም በመንገድ ላይ ምንም ዓይነት ችግሮች እንዳያጋጥም አድርጐ መሥራት፤ እንዲሁም ችግሮች ሲያጋጥሙም በሠላማዊ መንገድ ችግሮችን መፍታት፣ ከዚያም ከፍ ያለ ነገር ሲያጋጥም ለፀጥታ ኃይሎች በማሳወቅና በመጠቆም የዜግነት ግዴታችንን መወጣት አለብን።

በዓሉ በሠላምና በደስታ እንዲጠናቀቅ ሁሉም ዜጋ ሰላም ከሚያደፈርሱ ተግባራት ራሱን መቆጠብ፤ ተፈጥረው ሲያጋጥሙ የችግሩ አካል ሳይሆን የመፍትሔው አካል በመሆን በግንባር ቀደምትነት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። መልካም የመስቀል በዓል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በዓሉን በኃላፊነት መንፈስ እናክብር

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

መስከረም በኢትዮጵያውያን ዘንድ አቆጣጠር አዲስ ዓመት «አሃዱ» ብሎ ቁጥር የሚጀምርበት ነው። ክረምት እና በጋ ከፍተኛ ሽኩቻ ውስጥ፤ የክረምቱ ጭቃ ጥለኸኝ አትሂድ! እያለ የኋሊት የሚጎትተው፤ ፀደይ ደግሞ እባክህ ወደ እኔ ናልኝ! የሚልበት፤ ሃይማኖታዊ እና ባሕላዊ ትርጉም እና እሴት ያላቸው በዓላት የሚበዙበት ወር ነው።

መስከረም የክረምቱን መውጣት ተከትሎ ምድሪቱ ከቆላ እስከ ደጋ ልምላሜ የሚላበስበት፤ አንገቱን ደፍቶ የከረመ የቁጠማ ሣር የክረምቱን ማለፍ የሚያረጋግጠው፤ ከአጎነበሰበት ቀና ብሎ ‹ወፌ ቆመች› እንደሚል ሕፃን ለመቆም የሚውተረተረው በመስከረም ወር ነው።

የወፎች ኅብረ ዝማሬ ደመቅ የሚልበት፤ ሰፈራቸውን ትተው የተሰደዱ የአዕዋፋት ዝርያዎች ወደ ቀያቸው ተመልሰው ሥነ-ምሕዳሩን ውበት የሚያላብሱበት፣ በማለዳ ጫጫታቸው የተኛን ፍጡር የሚቀሰቅሱበት ወቅት ነው መስከረም።

በእኔ አተያይ እንደ እንቁጣጣሽ የተጨበጨለት የተዘፈነለት፤ እንደመስቀልም የተደመረለት በዓል አይገኝም። መስከረም ነገረ ብዙ፤ ሐሳበ ብዙ ነው፤ መልከ ብዙም ነው። ከዚህም ባሻገር በዚህ ወር ያለፈውን ዓመት ረስቶ በአዲስ ተተክቶ ሌላ ሕይወት ለመጀመር ሰዎች ደፋ ቀና የሚሉበት ነው። በርካታ በዓላትም የሚከበሩበት ነው። በዚህ ወር ከሚከበሩ በዓላት ታዲያ ከእንቁጣጣሽ ተከትሎ የበርካቶች መድመቂያ በዓል መስቀል ነው። መስቀል በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል በተለያዩ ሃይማኖታዊ እና ባሕላዊ ትውፊቶችን በማስታከክ ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንዱ ነው።

የታሪክና የሃይማኖት ድርሳናት እንደሚያመለክቱት፤ የመስቀል በዓል ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን (327 ዓ.ም) ጀምሮ ይከበራል። በዓሉ ሃይማኖታዊ ትውፊት የተላበሰ ሲሆን፤ በዘመኑ የነበረችው ንግሥት እሌኒ እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል አስቆፍራ ካስወጣችበት ጊዜ ጀምሮ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ሃይማኖታዊ ይዘት ተላብሶ ይከበራል።

ንግሥቲቱ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ‹‹ቂራቆስ›› በተባሉ አባት ጠቋሚነት ለማግኘት ደመራ አስደምራ ፍለጋ የጀመረችው መስከረም 17 ቀን እንደሆነ የክርስትና ሃይማኖት ድርሳናት ያስረዳሉ። ንግሥት እሌኒ የሃይማኖት አባቶችን አሰባስባ በፀሎት እንዲረዷት ጠይቃ፤ ከደመራው በሚወጣው ጢስ ጠቋሚነት መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ አግኝታለች። መስቀሉም ከወራት ቁፋሮ በኋላ መጋቢት 10 ቀን ወጥቷል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መስከረም 16 ቀን ‹ደመራ› እና መስከረም 17 ቀን ‹የመስቀል በዓል› እየተባለ ይከበራል።

ከአራተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ እንደሚከበር የሚነገርለት ይህ በዓል በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) የማይዳሰሱ ቅርሶች መዝገብ ላይ በዓለም ቅርስነት በኢትዮጵያ ሥም እንዲመዘገብ ተደርጓል።

የመስቀል በዓል ሃይማኖታዊ ይዘቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በየአካባቢው እንደ ማኅበረሰቡ ባሕልና ወግም ይከበራል። በተለይም ደግሞ በሀገሪቱ ደቡባዊ ክፍል ከሃይማኖታዊ ይዘቱ በተለየ ትርጉም ሰጥተው ያከብሩታል። ይህ በዓል በአንዳንድ አካባቢዎችም የዘመን መለወጫ ተደርጎም ይወሰዳል። የመስቀል በዓል በዘመናት መካከል ነባር ትውፊቶቹን ጠብቆ የዘለቀ ደማቅ በዓል ነው። መስቀል በዓል እንደ ዘመን መለወጫ ከመታየቱም በተጨማሪ የተጣሉ ሰዎች የሚታረቁበት ወሳኝ ወቅት ሲሆን ማኅበራዊ እሴትን በማጠናከርና ሠላምን በመስበክ ትልቅ ሚና አለው።

ንግስት ዕለኒ መስቀሉን ለማግኘት ብዙ የለፉች በኋላም የተሳካላት ስለመሆኑ ይነገራል። እንግዲህ ብዙ የተለፋበት ፆም ፀሎት የተደረገለት ሂደት ውስጥ ያለፈ በመሆኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ ያለበትም በዚሁ ጠንካራና ያልተበረዘ ዓውድ መሆን አለበት። በዓሉ ውበት እንዲኖረው የኅብኒዎችንም ቀልብ እንዲይዝ እና ከሃይማኖታዊ ይዘቱም በዘለለ ምጣኔ ሃብታዊ ጠቀሜታ እንዲኖረው ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል።

መስቀሉን ለማግኘት የተከማቸውን ክምር አፈር ለማስወገድ ብዙ ቁፋሮ ተካሂዷል፤ ረጅም ጊዜም ወስዷል። ይህ የሚያሳየው አንድ ነገር ለማግኘት ዕምነት፤ ፅናት እና ትዕግስት የሚፈልግ መሆኑ ነው። በአጭሩ መስቀል በዓል የምንፈልገውን ለማግኘት የማንፈልገውን የምናስወግድበት ሂደት የምንረዳበት ነው።

> **መስቀሉን ለማግኘት የተከማቸውን ክምር አፈር ለማስወገድ ብዙ ቁፋሮ ተካሂዷል፤ ረጅም ጊዜም ወስዷል፡፡ ይህ የሚያሳየው አንድ ነገር ለማግኘት ዕምነት፤ ፅናት እና ትዕግስት የሚፈልግ መሆኑ ነው። በአጭሩ መስቀል በዓል የምንፈልገውን ለማግኘት የማንፈልገውን የምናስወግድበት ሂደት የምንረዳበት ነው**

እኛም በዓሉን ስናከብር፤ እንደ ሀገር ሊጠቀሙን የሚችሉ ግን በርካታ ውጣ ውረዶችና የሚጠይቁ ጉዳዮች መኖራቸውን በመረዳት፤ ለዚህ መከባበር፣ መተባበር እንደሚያስፈልጉን በማጤን ሊሆን ይገባል። መስቀሉን ለማግኘት የማይፈለገውንና ለዓመታት የተከመረውን ቆሻሻ ማስወገድ ግድ እንዳለ ሁሉ፤ እኛም የምንፈልገውን እስክናገኝ ድረስ የምንፈልገው ነገር የተሸፈነበትን ቆሻሻ ማስወገድ ይጠበቅብናል። መስቀሉን ለማግኘት ሲባል በነበረው ቁፋሮም በርካታ የእምነቱ ተከታዮች የተሳተፉ ሲሆን፤ ከፍተኛ ልፋትና ፀሎት የታከለበት ነው። በመሆኑም የምንፈልገውን ለማግኘት ብዙ የተጋን፤ ነገም የምንተጋ መሆናችንን ማስመስከር አለብን።

የደመራ ወይንም መስቀል በዓል በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) የማይዳሰሱ ቅርሶች መዝገብ ላይ በመላው ኢትዮጵያ ስም በዓለም ቅርስነት መመዝገቡ፤ ከክርስትና እምነት ተከታዮች ባለፈ፤ ለሌሎች እምነት ተከታዮች የብሔራዊ ኩራት ምንጭ ነው። መስቀል በዓል ከመንፈሳዊ በዓልነት ባለፈ የሕዝቦች አንድነትና መተሳሰር የሚጠናከርበት፣ ተስፋ እና ቀጣይ ዕቅድ የሚነደፍበት ወቅት ነው። በመሆኑም መስቀልን የመንፈሳዊ ይዘት ብቻ ሳይሆን ሥነልቦናዊ ትስስር የሚጠናከርበት በመሆኑ አብሮነታዊነትን ለማጉላት ፋይዳው ላቅ ያለ ነው።

በዓሉ ብሔራዊ ክብራችንን፤ የመዋደዳችንና የመከባበራችን ዓርማ፣ ብሔራዊ አንድነታችንን፤ ለሠላም እና ለአብሮነት ያለንን ማኅበረሰባዊ ማንነት በአደባባይ የምናስመሰክርበት መልካም አጋጣሚ በመሆኑ ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ ልናከብረው ይገባል። ይህንን ማድረግ ደግሞ የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ነው። መልካም በዓል።

## ወቅታዊ

# የደመራ በዓል መንፈሳዊና ባሕላዊ እሴቶች

ራስወርቅ ሙሉጌታ

**የኢትዮጵያ የመስቀል በዓል አከባበር በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ የትምህርትና ባሕል ማዕከል በዓለም ቅርስነት ተመዝግቧል። ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ካስመዘገበቻቸው ዓለም አቀፍ ቅርሶች በተጨማሪ የመስቀል ደመራ ባሕላዊ ክብረ በዓል አስረኛውና የመጀመሪያው የማይዳሰስና የማይጨበጥ (ሕሊናዊ) ቅርስ በመሆን ለመመዝገብም በቅቷል። የደመራ በዓል መስከረም አስራ ስድስት ቀን በመስቀል ዋዜማ የሚከበር ሲሆን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ በታላቅ ናፍቆትና አክብሮት ከሚከበሩ በዓላት መካከልም አንዱ ነው።**

**የደመራ በዓል እንደ መሆኑ በመላው ሀገሪቱ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ከሀይማኖታዊ ስርዓት ባለፈ የተለያዩ ባሕላዊ ክንዋኔዎችም የሚፈጸሙበት ነው። የደመራ የአደባባይ በዓል እንደመሆኑ ሁሉ በርካታ ሀይማኖታዊና ባሕላዊ ክንዋኔዎች የሚካሄዱበትም ነው። እኛም ለዛሬው ዝግጅታችን የደመራ በዓል መንፈሳዊና ባሕላዊ እሴቶች ምን ይመስላሉ ስንል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅና የብዙኃን መገናኛ ቴሌቪዥን መርሐ ግብር አዘጋጅ ከሆኑት መጋቤ ምስጢር ሣህሉ አድማሱ ቆይታ አድርገናል። እንደሚከተለውም አቅርበነዋል።**



**አዲስ ዘመን ፡ ደመራ ምን ማለት ነው ታሪካዊ አመጣጡስ እንዴት ነው ?**

**መጋቢ ምስጢር ሣህሉ ፤** ደመራ የሚለው ቃል ደመረ፣ ጨመረ፣ አንድ አደረገ፣ አዋሀደ ከሚለው የግእዝ ቃል የተወሰደ መሠረታዊ ቃል ሲሆን መሰብሰብን፤ መከመርን፤ መጨመርን ያመለክታል። ጥንታውያን አባቶች ሕዝባዊ አንድነትን ለመግለጽ፣ ብሔራዊ ኅብረትን ለመስበክ የተጠቀሙበት ትውፊታዊ ቃል ነው። ኢትዮጵያዊ አንድነት ኦርቶዶክሳዊ ኅብረት እጅግ ተዳክሞ በነበረበት ወቅት ሕዝባዊ ስሜትን ብሔራዊ ፍቅርን ሃይማኖታዊ እሴትን ለማጠናከር የተጠቀሙበት የመቀስቀሻ ዘዴ እንደሆነ ይነገራል።

የደመራ በዓል ታሪካዊ አመጣጥንም ስንመለከት እንደሚከተለው በታሪክ ተዘግቦ እናገኛለን። እየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከወደቀበት መርገም ያድነው ዘንድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በሰላሳ ሶስት ዓመቱ በራሱ ፈቃድ በመስቀል ላይ ተሰቀለ። ከፍተኛ ወንጀል የሠሩ ሰዎች ብቻ ይሰቀሉበት የነበረው መስቀል ከጌታ ስቅለት በኋላ የመዳን ምልክት ሆነ። ዳሩ ግን ጌታ የተሰቀለበት መስቀል ተአምራትን በማድረጉ የታወኩ አይሁድ መስቀሉን ከሰዎች እይታ ለመሠወር በመወሰን ጉድጓድ ቆፍረው ቀበሩት። መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ለ300 ዓመታት ያህል የቆሻሻ መጣያና ማከማቻም አደርገውት ቆይተዋል።

ከዚህ በኋላ ግን የታላቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት እሌኒ ከቁስጥንጥንያ የዛሬዋ (ኢስታንቡል) ተነሥታ የጌታችን የመድኃኒችን የእየሱስ ክርስቶስን መስቀል ከተቀበረበት ለማውጣት ወደ እየሩሳሌም ሔደች። እየሩሳሌም በደረሰች ጊዜ የጌታችን የመድኃኒታችን መስቀል ተአምራትን እንዳያደርግ አይሁድ በምቀኝነት ጉድጓድ ቆፍረው ቀብረውት ነበርና የተቀበረበትን ቦታ የሚያሳያት አጥታ በመፈለግ ብዙ ጊዜ አሳለፈች። በኋላ ግን አንድ ኪራኮስ የሚባል አረጋዊ አካባቢውን ነግሯት ደመራ አስደምራ ዕጣን አጢሳ ወደ ፈጣሪዋ ብትማፀን የዕጣኑ ጢስ ወደ ሰማይ ከወጣ በኋላ መንበረ ጸባዖት ደርሶ ተመልሶ መስቀሉ የተቀበረበትን ስፍራ (ጎልጎታ) እንዳመላከታት ተገልጿል።

እርሷም በምልክቱ መሠረት መስከረም አስራ ሰባት ቀን ቁፋሮው እንዲጀመር አዘዘች። ሰባት ወር ያህል ከተቆፈረ በኋላ መጋቢት አስር ቀን የጌታችን እየሱስ ክርስቶስን ክቡር መስቀል አገኘች፤ ከእርሱ መስቀል ጋር ሁለት ወንበዴዎች የተሰቀሉበትን መስቀልም አብራ አግኝታው ስለነበር የጌታችንን መስቀል ለይታ ያወቀችበት መንገድ ግን ድውያንን በመፈወሱ፣ አንካሳ በማበርታቱ፣ ጎባጣን በማቅናቱ፣ ሽባን በመተርተሩ፣ የዕውራንንም ዐይን በማብራቱ ነው። ስለዚህም በየዓመቱ የመስቀልን በዓል ስናከብር ደመራ የምንደምረውና የምናበራው ንግሥት ዕሌኒን አብነት በማድረግ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡ የደመራ በዓል ማክበር መቼ ተጀመረ ?**

**መጋቢ ምስጢር ሣህሉ፤** ንግሥት ዕሌኒ መስቀሉን ባገኘች ጊዜ የደስታዋን መልዕክት ለልጇ እንዲደርሰው ለማድረግ እንዳሁኑ ዘመን ስልክና ሬድዮ ስላልነበር በዚያን ጊዜ መልዕክትን ሩቅ ሥፍራ ለማስተላለፍ ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት መንገድ ነበር። ይህም በየተራራው ቃፊሮችን (መልእክተኞችን) መድበው መልዕክቱን ከሚተላለፍበት አቅራቢያ ተራራ ላይ ችቦ በማብራት ከርሱ በኋላ ተራራ ላይ ላለው መልዕክተኛ ምልክትን በማሳየት ነው። ቀጣዩም መልዕክተኛ ችቦን እያበራ፣ ለሌላኛው መልዕክተኛ በማሳየት መልዕክቱ መድረስ የሚገባው ቦታ እንዲደርስ በዚህ መልኩ ያስተላልፉ ነበር።

ንግሥት ዕሌኒም ይህንን ዘዴ በመጠቀም የመስቀሉ መገኘት ወሬ (የምሥራች ዜና) ቁስጥንጥንያ እንዲደርስ አደርጋለች። ልጇ ቆስጠንጢኖስም መልዕክቱ እንደደረሰው ወደ እየሩሳሌም ሂዶ እናቱን አግኝቶ ብዙ ስጦታ አበርክቶላታል። እርስዋም የቤተክርስቲያኑም መሠረት ወዲያው እንዲጣል ያደረገች ሲሆን የደመራ ማብራት ሥርዓትም ከዚህ ግዜ አንስቶ ሲያያዝ የመጣና ዛሬ የደረሰ ነው።

**አዲስ ዘመን፤ የደመራ በዓል ከሃይማኖታዊ ስርዓቶች ባለፈ በየአካባቢው የተለያዩ ባሕላዊ ክንዋኔዎች አሉት እነዚህን ቢያብራሩልን ?**

**መጋቢ ምስጢር ሣህሉ፤** የመስቀል በዓል ሃይማኖታዊ በዓል ቢሆንም ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ባህሎቻቸውን እና እሴቶቻቸውን በማሳየት የሚያከብሩት በዓል ነው። የውኃ በዓል ከሚባሉት ውስጥ በዓለ ጥምቀትና ቃና ዘገሊላ ተጠቃሽ ሲሆኑ፤ በዓለ እሳት ከሚበሉት ውስጥ ደግሞ ደብረ ታቦርና የደመራ በዓል ተጠቃሽ ናቸው። በዋናነት ሀይማኖታዊ ስርዓቱ ሲታይ በመስከረም አሥራ ስድስት ቀን በዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ለመስቀል መታሰቢያ ሰው ሁሉ በየመንደሩ በየቀበሌው ቀጠን ያለ ርጥብ አጠናን ይዞ ዕንጨትን እየሰበሰቡ መደመርና በማቃጠል ነው። ይህም ሆኖ እንደ ጎንደር ፤ አክሱምና ላሊበላ ባሉ አካቢዎች ደመራ የማብራት ስነስርዓቱ የሚከናወነው በአስራ ሰባት ነው።

አዲስ አበባም የመስቀል ደመራ በዓል በደምቀት ከሚከበርባቸው ቦታዎች አንዷ ናት። በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ የሚከበረውን የደመራ በዓል ለማክበር የሚታደሙት የሀይማኖቱ ተከታዮች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎችም ናቸው። በዓሉ በሚከበርብት ወቅትም ከፓትርያርኩ ጀምሮ በርካታ የሀይማኖት አባቶች የሚገኙ ሲሆን ከየአድባራቱ የሚመጡ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችና ሌሎች ዘማሪዎችም የሚታደሙበት ይሆናል። ከየቤተክርስቲያናቱ ከሚመጡት አገልጋዮች በተጨማሪም በርካታ የእምነቱ ተከታዮችም በተመሳሳይ ሀይማኖታዊ ስርዓቶችን ይታደሙበታል።

በተለመደው አካሄድ በዓሉ በሚከበርበት ቦታ የሚገኙ ምእመኖችም ሆኑ የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ከሌላው ግዜ በተለየ የሚለብሷቸው አልባሳት አሉ። ከቅርብ ግዜ ወዲህ ደግሞ በየሰፈሩ ያሉ ወጣቶች የተለያዩ ሀይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ተመሳሳይ ልብሶችን በማዘጋጀት በመስቀል አደባባይ የሚታደሙ ሲሆን የሚያሰሟቸው ዝማሬዎችና ምስጋናዎችም አሉ። የደመራ በዓል በዋናነት በመስቀል አደባባይ የሚከበር ቢሆንም በየሰፈሩና በየቤቱም ችቦ በማዘጋጀት ደመራ ተደርጎ ይበራል።

በዓሉ በገጠራማው የሀገራችን ክፍል ከሀይማኖታዊ ስርዓትነቱም ባለፈ የጥሩ ነገር ጅማሮ እየተደረገም ይወሰዳል። የመስቀል ደመራ በዓል የሚከበርበት የመስከረም ወር ጨለማ የሚባለው ክረምት አልፎ የብርሃን ወቅት የሆነው የሚጀምርበት ነው። በዚህም የወንዝ ሙላትን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ለወራት ሳይገናኙ የከረሙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በማገናኘቱ ረገድ የመስቀል በዓል የራሱ አዎንታዊ ሚና አለው። በዚህም የተነሳ በዓሉ ለበርካቶች የተነፋፈቀ የሚገናኙበት፤ ቤተሰብ የሚሰባሰብበት በመሆን ለብዙዎች የደስታ ምንጭም ነው።

**በደመራ በዓል በሚደረጉ ሀይማኖታዊ ትምህርቶች በሚከናወኑ ምስጋናዎች ሁሉ ሰላም የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑንና የሰላምን አስፈላጊነት ለሰው ልጆች ሁሉ የሚታወጅበትም ይሆናል**

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የደመራ በዓል ለበርካታ ሰዎች የገቢ ምንጭ በመሆንም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው በዓል ነው። በከተሞች ለደመራ በዓል እንደ ሌሎች አውደ አመቶች ሁሉ አዲስ ልብስ መልበስ የተለመደ በመሆኑ ከልብስ ሽያጭ ጀምሮ በየአካባቢው የደሩ ገበያዎችን ማየት የተለመደ ትእይንት ነው። በገጠርም እንደ አካባቢው ባሕል የደመራን በዓል ታሳቢ በማድረግ የሚዘረጉ ገበያዎች ያሉ ሲሆን ለደመራ በዓል ተብለው የሚቀርቡ ምርቶችም አሉ።

**አዲስ ዘመን፤ በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች ያለው የደመራ በዓል አከባበር ምን ይመስላል ?**

**መጋቢ ምስጢር ሣህሉ፤** የደመራና የመስቀል በዓል በሁሉም አካባቢዎች የሚከበር ቢሆንም በደቡብ የሀገራችን ክፍል በተለየ ድምቀትና ባሕላዊ ሁነት ይከበራል። በደቡብ የመስቀል በዓል ከሃይማኖታዊ ገፅታው በተጨማሪ በተለያዩ ባሕላዊና ማኅበራዊ እሴቶች ታጅቦ ይከበራል። የበዓሉ አከባበር እንደ አካባቢው ይለያያል። በጉራጌ፣ በከንባታ እና በዶርዜ የመስቀል በአል ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይከበራል።

ለምሳሌ የመስቀል በዓል በቤተ ጉራጌ ከወትሮው የተለየ ቦታ አለው። በሥራ ምክንያት ተለያይተው የቆዩ ቤተሰቦች የሚገናኙበት ብቻም ሳይሆን በጋራ እየበሉና እየጠጡ የሚያከብሩት በዓል ነው። ለምሳሌ በቤተ ጉራጌ የመስቀልን በዓል ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ እንስሳትም ጭምር ያከብሩታል። ለወትሮው ወደ ግጦሽ ሜዳ ወጥተው የዕለት ጉርሳቸውን ያገኙ የነበሩ የቀንድም ሆኑ የጋማ ከብቶች ታጭዶ በተዘጋጀላቸው መኖ ከቤት ሳይወጡ በዓሉን እንዲያሳልፉ ይደረጋሉ። በቤተ ጉራጌ የመስቀል በዓል ለአንድ ቀን ብቻ ተከብሮ የሚያልፍ አይደለም።

በጉራጌ ብሔረሰብ ተወዳጅ የሆነው የመስቀል በዓል በቀናት ተከፋፍሎ የሚከበር በዓል ነው።

በቤተ ጉራጌ የመስቀል በዓል ከመስከረም አስራ ሁለት እስከ ጥቅምት አምስት ቀን ይከበራል። በእነዚህ ግዜያትም ከሕፃናት ጀምሮ ወጣቶች እና አዛውንቱ የብሔረሰቡን ባሕላዊ ምግብ ክትፎና ሌሎችን በመመገብ፣ በጭፈራና በፈንጠዝያ ያከብራሉ።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# የደመራ በዓል መንፈሳዊና...

ከገጽ 6 የዞረ

እያንዳንዱ ቀናትም የየራሳቸው ሥያሜና ባሕላዊ ክዋኔዎች አሏቸው። በዚህም መሰረት መስከረም አስራ ሶስት ቀን «ወሬት የኽና » ይባላል። ይህም ማለት በብሔረሰቡ ቋንቋ እንቅልፍ ከልካዩ ቀን የሚል ትርጓሜን የያዘ ሲሆን ለዚህም በምክንያትነት የጉራጌ ሴቶች ለበዓሉ ዝግጅት ለማድረግ የሚጓጉበት ቀን ከመሆኑ ጋር በተያያዘ እንደሆነ ይነገራል። በዚህ ቀን ለበዓሉ ለመመገቢያነት የሚያገለግሉ ባሕላዊ ቁሳቁሶች ለዓመት ከተሰቀሉበት ቦታ ወርደው በጥንቃቄ ተጣጥበው ዝግጁ ይሆናሉ። የፅዳት ተግባሩ ከአጥንት የተሰሩ ባሕላዊ የመመገቢያ ማንኪያዎች፣ ከሸክላ የተሰሩ ጣባዎች እና ሌሎችንም ይጨምራል። በተጨማሪ ቤቶች ከአፈር በተዘጋጁ ቀለማት ያሸበርቃሉ፤ አዳዲስ የኬሻ ጅባዎች ተነጥፎባቸው ለበዓሉ ዝግጁ ይሆናሉ። ይኸው ቀን በሶዶ ክስታኔ ጉራጌዎች «የወልቀነ» ወይም የሴቶች ቀን በመባል ይታወቃል።

መስከረም አስራ አራት ቀን «ደንጌሳት» ይባላል። ይህ ቀን ልጆች እና ሕፃናት ደመራ ደምረው ባሕላዊ ጭፈራዎቻቸውን የሚጫወቱበት ነው። «ደንጌሳት» ወይም የልጆች ደመራ/እሳት የሚል ትርጓሜን የያዘ ሲሆን ልጆች ቀኑን በተለያዩ ባሕላዊ ዘፈኖች ለቀኑ ስላበቃቸው ፈጣሪያቸውን ያመሰግኑታል።

ከደመራው በኋላም ሴቶች የጎመን ክትፎ በማዘጋጀት በእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ውክልና በተዘጋጀ ጣባ በማድረግ ለምግብነት ያዘጋጃሉ። ባለትዳር የሆኑ የቤተ ጉራጌ አባላት በአንድ ጣባ የጎመን ክትፎው ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል። ተምሳሌትነቱም የትዳር አጋሮች አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው ተብሎ ስለሚታመን የሚፈፀም ነው።

መስከረም አስራ አምስት «ወኸመያ» በቤተ ጉራጌ ዋናው የመስቀል በዓል የሚከበርበት ቀን ነው። «ወኸመያ» ወይም ዓመት በዓል የሚል ትርጉም አለው። በዚህ ቀን በሁሉም የብሔረሰቡ አካባቢዎች የእርድ ቀን ነው። በዕለቱም የሚታረደው በሬም ሆነ ወይፈን ሽማግሌዎች ፊት ቀርቦ ስለ ሃገር ሰላም እንዲሁም ስለ በዓሉ መልካሙን የመመኘት ምርቃት የሚወርድበት ነው። የቤተሰቡ አባላትም በእያንዳንዱ ምርቃት መጨረሻ ላይ ሶስት ጊዜ “ኬር ይሁን” በማለት ምርቃቱን ይቀበላሉ። ‘ኬር ይሁን’ ትርጉሙ ሰላም ይሁን እንደማለት ነው።

በተመሳሰይ በተለያዩ አካባቢዎችም የሚከወኑ ባሕላዊ ስርዓቶች አሉ። እነዚህን ስርዓቶች በሙሉ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር አለ። በዓሉ ሁሉም ስለሰላም የሚመክሩበት ;ሁሉም ስለሰላም የሚሰባሰቡበትና የሚሰሩበት ነው። አንዳንዶቹ ዝግጅቶች ለወራት የሚደረጉ ናቸው። እንግዲህ በእነዚህ ግዜያት ውስጥ ሁሉ አንዱ ሌላውን እያሰበ እንዴት ሊያስደስተው ሊያስተናግደው እንደሚችል ለፍቅሩ እየተጨነቀ ይቆያል ማለት ነው። ቤተሰብ በዚህ ደረጃ እንደሚዘጋጀው ሁሉ ብዙ ልጆችም ወላጆቻቸውን በዚህ ቀን ደስተኛ ለማድረግ ገንዘብ ከማስቀመጥ ጀምሮ በርካታ ስጦታዎችንም ሲያዘጋጁ ይቆያሉ። በዚህ አይነት በአብዛኛው ከአዲስ አበባ ወደተለያዩ አካባቢዎች የደመራ በዓልን ለማክበር የሚንቀሳቀሱ ሲሆን የደመራና የመስቀል በዓልን ታሳቢ በማድረግ ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ወደኢትዮጵያ የሚመጡትም በርካቶች ናቸው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከቤተሰብ ጀምሮ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው ሰላማዊ ግንኙነት እንዳይላላ ትልቅ ፋይዳ ያላቸው ናቸው።

**አዲስ ዘመን፤ በኢትዮጵያ የሚከበረው የደመራ በዓል በሀገር ገጽታ ግንባታ ረገድ የሚኖረው ፋይዳ እንዴት ይታያል።**

**መጋቢ ምስጢር ሣህሉ፤** የመስቀል ደመራ በዓል በ2006 ዓ.ም በዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት ተመዝግቧል። ይህም በዓሉ ከሀገራችን አልፎ በሌሎች ልዩ ሥፍራ እንዲሰጠው ምክንያት ሆኗል። ከዚህ ግዜ ጀምሮም የበዓሉ አከባበርም በርካታ የውጭ ሃገር ቱሪስቶችን ቀልብ የሳበና የደመራው በዓል በሚከበርበት ወቅት በርካቶቹ ወደ ሀገራችን በመምጣት ታዳሚ መሆን ከጀመሩ ሰነባብተዋል። በበዓሉ የሚታደሙት የውጪ ዜጎች በአንድ ወገን ከየሀገራቸው ይህንን በዓል ለማክበር እቅድ ይዘው የሚታደሙ ሲሆን ፤ ሌሎች ደግሞ የስራ ጉዳይን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። እነዚህ የውጪ ሀገር ዜጎች ለየትኛውም ጉዳይ ተገኝተው ቢሆን እንደ ሀገር የሚያስገኙልን ጠቀሜታ ሰፊ ነው።

እንደሚታወቀው በዓሉ በሚከበርበት ወቅት



**እንደ ደመራ ያሉ ሀይማኖታዊ በዓላት ሲከበሩ በንጹህ ሕሊና ከቂምና ጥላቻ በጸዳ ልቦና ሊሆን እንደሚገባ በተደጋጋሚ ትምህርት ይሰጣል። በተግባርም እንደምናየው በቤተሰብ ውስጥ ተኳርፎ እና ተቀያይሞ የደመራ እሳትን የሚለኩስ አይኖርም**

የሀገር ውስጥም ሆነ የውጪ በርካታ ሚዲያዎች ለዘገባ መገኘታቸው አይቀርም። ነግር ግን የበዓሉን አከባበር አስመልክቶ በእነዚህ የመገናኛ ብዙሀን ከሚተላለፈው ባላነሰ በበዓሉ የታደሙ የውጪ ዜጎች ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በርካታ በጎ ነገሮችን ለዓለም ተደራሽ የሚያደርጉበት እድልም ሰፊ። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በአንዳንድ አካባቢዎች ያሉ ችግሮች እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ ችግሮች የሀገርን ገጽታ የሚያጠለሹና ቀሪው ዓለም ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ያለውን ቀና እሳቤ የሚያበላሹ ናቸው። በተለይም እኛ ኢትዮጵያውያን እንግዳ በመቀበል ረገድ በጣም የሚያኮራ ታሪክ ያለን ሕዝቦች ነን። በየትኛውም ዘመን ቢሆን በኢትዮጵያ የነበሩ ነገስታትም ሆነ ሕዝቦቿ የትኛውንም በሰላም የመጣ እንግዳ አሳፍረው የመለሱበት ግዜ የለም። እንግዳ በመቀበልና በማስተናገድ ረገድ ያለው ታሪካችን ዛሬም ይኸው ነው። ይህንን አስጠብቆ በመቀጠል ረገድ የደመራ በዓል ይህንን የራሱ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

በሌላ በኩል በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም በያሉበት የደመራ በዓልን ሲያከብሩ እንመለከታለን። እነዚህ ሰዎች የትም ሆነው በዓሉን ቢያከብሩ ኢትዮጵያውያን ሆነው ነው። ማለትም የሀገር ባሕል ልብስ ይለብሳሉ። አቅማቸው በፈቀደ በየእለቱ የሀገር ባሕል ምግቦችን ያዘጋጃሉ። የሚያሰሟቸው ዝማሬዎችና ሌሎች ክንዋኔዎችም በሙሉ ሀገርን የሚያሳዩ ይሆናሉ። ባጠቃለይም ሀገራችን ኢትዮጵያ ያላትን ሀገራዊ ማንነትና ተቀባይነት ለቀሪው ዓለም ለማሳወቅ ተደመራ በዓል ዝግጅቶች የየራሳቸው ድርሻ አላቸው።

ሌላው በሀገር ውስጥ የሚከበሩ ሕዝባዊ የአደባባይ በዓላትን ስናነሳ እንደ ሀገር የቱሪዝም እንቅስቃሴ መጠቀሱ አይቀርም። የደመራ በዓልም በርካታ ቱሪስቶችን በመሳብ ለሀገር ገቢ ከሚያስገኙት መካከል አንዱ ነው። በእርግጥ በአሁኑ ወቅት ያለው የውጪ ሀገራት የደመራ በዓል ታዳሚ ቁጥር ሊደረስበት ከሚገባው አንጻር ሲታይ በጣም ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል። ይህንን ለማሳደግ በቅድሚያ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ያሉትን የደመራ አከባበር ለሕዝብ ማስተዋወቅ የሚጠበቅ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን ፤ የደመራ በዓል በሰዎች መካከል ስለሰላም የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው?**

**መጋቢ ምስጢር ሣህሉ፤** እንደ ሀይማኖት አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሰላም አባት ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር እንደተጣሉ እንዲሁም እርስ በእርሳቸውም በኑሮው ሰላምን ማግኘት እንዳልቻሉ ታስተምራለች። ይህ የታጣው ሰላምም የሰላም አለቃ በሆነው በክርስቶስ እንደገና በመስቀሉ ምክንያት እንደተገኘ ታውጃለች።

ሰላም የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎትና የሕልውና መሠረት ነው። ሰላም የሰው ልጆች ሁሉ የጋራ ፍላጎት እንጂ የአንድ ቡድን አመለካከት ወይም ርእዮተ ዓለም አይደለም። ሁሉን የሰው ልጆች ከምናገለግልባቸው ነገሮች አንዱ ሰላምን ለሰው ልጆች ሁሉ መስጠት ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የሰላም መገኛ እየሱስ ክርስቶስን ምሳሌ በማድረግ ለሰው ልጆች ሁሉ ሰላም እንዲሰፍን ትሰራለች። የመስቀል ደመራ በዓል መሠረትም ይህ ነው። ክርስቲያኖች በሙሉ የቤተ ክርስቲያንንም ሆነ የሀገርን ሰላም ለመጠበቅ ኃላፊነታችንን በአግባቡ መወጣት እንደሚጠበቅባቸው ይታመናል። በመሆኑም በደመራ በዓል በሚደረጉ ሀይማኖታዊ ትምህርቶች በሚከናወኑ ምስጋናዎች ሁሉ ሰላም የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑንና የሰላምን አስፈላጊነት ለሰው ልጆች ሁሉ የሚታወጅበትም ይሆናል።

ሌላው ከሰላም ጋር በተያያዘ የሚነሳው ጉዳይ ቤተሰብ ለማኅበረሰብ ብሎም ለሀገር መሰረት እንደሆነ ሁሉ በቤተሰብ ውስጥ የሚጀመር ሰላምም ከሰፈርና አካባቢ አልፎ ለሀገር የሚተርፍ ይሆናል። የደመራ በዓል ሲከበር ከላይ እንደተገለጸው ተራርቀው የኖሩ የቤተሰብ አባላት የሚሰባሰቡበት ስጦታ የሚለዋወጡበት መልካም ምኞት የሚገላለጹበት ነው። እንደ ደመራ ያሉ ሀይማኖታዊ በዓላት ሲከበሩ በንጹህ ሕሊና ከቂምና ጥላቻ በጸዳ ልቦና ሊሆን እንደሚገባ በተደጋጋሚ ትምህርት ይሰጣል። በተግባርም እንደምናየው በቤተሰብ ውስጥ ተኳርፎ እና ተቀያይሞ የደመራ እሳትን የሚለኩስ አይኖርም። በመሆኑም በዓሉ ይቅር ለመባባል የሚያስችልም ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በበርካታ አካባቢዎች ለደመራ በዓል ዝግጅት ሲደረግ ሽማግሌዎች የተቀያየሙ ጎረቤታሞች ወይንም ቤተዘመዶች ካሉ ሰላም እንዲያወርዱ ይጠይቃሉ። የተለመደ ነገር ስለሆነም ብዙ ሰዎች ተቀብለው በይቅርታ አዲስ ግንኙነት የሚጀምሩበት ሁኔታ ይፈጠራል። እነዚህ ነገሮች ሁሉ በሰዎች መካከል የነበሩ ቁርሾዎች እንዲቀሩ ቅይሞች እንዲለዝቡ በማድረግ ሰላምን የሚያበዙ ናቸው።

በሌላ በኩል በተለይም በአዲስ አበባ የደመራ በዓል ሲከበር ከሀይማኖት አባቶችና ከምእመናኑ በተጨማሪ ከፍተኛ የመንግስት አመራሮችና ሌሎች እንግዶችም የሚታደሙ ይሆናል። የእነዚህ እንግዶች መገኘት በዓሉ በኢትየጵያውያን ዘንድ ያለውን ቦታ ተቀባይነት የሚያመላክት ሲሆን እንግዶቹም የሚያስተላልፏቸው መልእክቶች ሰላምን አንድነትንና ልማትን የሚሰብኩ ናቸው። ይህም እንደ ሕዝበ ክርስቲያኑ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር እንደ ሕዝብ ያነበረንን ያለንን ሰላም እንድናጸና የሚጠቅም ነው።

**አዲስ ዘመን ፤ በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ ?**

**መጋቢ ምስጢር ሣህሉ፤** እኛ ኢትዮጵያውያን በርካታ ጥሩ ነገሮች ያሉን ሕዝቦች ነን፤ ከገጠሙን ተግዳሮቶች በላይ ብዙ የደስታና የአሸናፊነት ግዜዎችንም አሳልፈናል። ዛሬም ይህንን የደመራ በዓል ስናከብር ትላንት የነበርንበትን ታላቅነት ለመመለስ በሰላም በመተሳሰብና በፍቅር ሊሆን ይገባል። ይህንን ሰላምና ፍቅር የምንገልጸው ደግሞ እርቀን ሳንሄድ በአካባቢያችን ካሉት ጀምሮ ነው። የተቸገሩን መርዳት፤ ለሰው ልጆች ሁሉ ቀና ማሰብ፤ ከክፉ ስራዎች መጠበቅ፤ በበጎ ተግባራት ተባባሪ መሆን እና ሰላምን መስበክ ከእያንዳንዱ ክርስቲያን የሚጠበቅ ይሆናል።

**አዲስዘመን፤ ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**መጋቢ ምስጢር ሣህሉ፤** እኔም አመሰግናለሁ።

# መስቀል ሃይማኖታዊ የትስስር በዓል

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሸክታብ)**

የመስቀል በዓል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ መንፈሳዊ የአደባባይ በዓላት መካከል አንዱ ነው። መስቀል ኃይላችን፣ መስቀል ቤዛችን፣ መስቀል መመኪያችን በሚል የሃይማኖቱ አስተምህሮ ሥርዓቱ በሚፈቅደው አለባበስና አካሄድ የእምነቱ ተከታይ በተገኘበት በዝማሬና፣ በሌሎች መንፈሳዊ ዝግጅቶች ይከበራል።

የመስቀል በዓል ከመንፈሳዊ ቀለሙ ጎን ለጎን ብዙሀነት የሚታይበት የእርስ በእርስ ጉርብትና የሚንፀባረቅበት በዓልም ጭምር ነው። እንደእምነቱ አስተምህሮ መስቀል የሚከበርበት ዋና ምክንያት የክርስቶስ ግማደ መስቀል በንግስት እሌኒ ዓማካኝነት መገኘቱን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን የበዓሉ ዋና ዓላማ በመስቀሉ ጥልን መሻሩ፣ ፍቅርን ማብሰሩ ዋና ሆኖ ይጠቀሳል።

መስቀል ‹ሰቀለ› ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን መስቀያ ወይም መከራ የሚለውን ትርጉም ይይዛል። መከራ የተባለበት ምክንያትም የጥንት ሮማውያን ወንጀለኞችን በሞት ሲቀጡ በእንጨት ላይ እየሰቀሉ ስለነበር ነው። አይሁድም ከገዢዎቻቸው በወረሱት ልማድ ከጽድቅ በቀር አንዳች በደል የሌለበትን እየሱስ ክርስቶስን ወንጀለኛ በማድረግ በመስቀል ላይ ሰቅለውታል። ይህ ጻድቁን ጌታ የሰቀለ የድህነት መስቀል ብዙዎችን ከህፅያትና ከበደል፣ ከአጋንትና ከለምጽ ሲፈውስ ያዩት አይሁዶች በብስጭት ጉድጓድ ምሰው ይቀብሩታል።

አይሁዶች በዚህ ሳያበቁ በእየሩሳሌም እና በይሁዳ ምድር ያሉ ሕዝቦች ማንኛውንም ጥራጊ መስቀሉን በቀበሩበት ቦታ ላይ እንዲጥሉ ትዕዛዝ በማስተላለፍ የቅዱስ መስቀሉ ስፍራ 200 ዘመናት ያህል የቆሻሻ መጣያ ሆኖ ነበር። የመስቀሉ ፍቅር ያንገበግባት የነበረችው ንግስት እሌኒ ዘውድ በጫነ ልጇ ቆስጠንጥኖስ በኩል የወቅቱ የክርስቲያን ጠላት የነበሩ መክሰምያኖስ እና ድዮቅልጥያኖስ የተባሉ አህዛቦችን በመፋለም በስተመጨረሻ ደመራ ደምራ የጭሱን አቅጣጫ በመከተል መስቀሉ ከተቀበረበት እንዲወጣ ሆኗል።

‹አንቺም በከንቱ አትድከሚ ሰውንም አታድክሚ እንጨት አሰባስበሽ፣ ዕጣን አፍሽበት፣ በእሳትም አያይዢው የዕጣኑ ጢስ ወደላይ ወጥቶ ወደታች ሲመለስ አቅጣጫውን አይተሽ አስቆፍሪ በዚህ ምልክት ታገኛለሽ› በሚል የኪራኮስ ምክር መሰረት ደመራ ደምራ የመስቀሉን ስፍራ ደረሰችበት። ከመስከረም 17 ጀምራ እስከ መጋቢት 10 ድረስ ቀንና ለሊት ለሰባት ወራት ያህል የቆሻሻውን ኮረብታ አስቆፍራ መስቀሉን አገኘች።

በጠላቶች እንደተራ ነገር የትም ተጥሎ ዓመታትን የዘለቀው መስቀል ጊዜው ደርሶ ለብዙዎች የደስታና የመዳን መንገድ ሆነ። መስከረም 16 የሚከበረው የደመራ በዓልም ያን መስቀሉን ከተሰወረበት ለማግኘት የተከፈለውን ዋጋ ለማስታወስ መሆኑን የሀይማኖቱ አስተምህሮ ይገልጻል። ደመራ የሚለው ቃል ‹ደመረ፣ ጨመረ፣ አንድ አደረገ› ከሚለው የግዕዝ ቃል የተመዘዘ ሲሆን አንድነትንና ሕብረትንም ይወክላል።

የመስቀል በዓል በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት (በዩኒስኮ) የተመዘገበ ከሀገር አልፎ ዓለም አቀፍ በዓል ከሆነ ሰነባብቷል። ይህ ማለት መንፈሳዊነቱን ሳይለቅ፣ በሕግና በቀኖና በተደራጀ መልኩ «ኢንታንጀብል» በሚል የቅርስ መዝገብ ላይ ሰፍሯል። የመስቀል በዓል ከስም አጠራሩ ጀምሮ ኢትዮጵያዊነት የተንጸባረቀበት ነው። ደመራ በሚለው የመደመርና የብዙሀነት ሥርወ-ቃል መሰረቱን ሲያቆም የነበረውን ካለውና ከሚመጣው ጋር በማስተሳሰር እንደሆነ አምናለሁ። አንድነትና አብሮነት በራቀን በዚህ ጊዜ የደመራ ጽንሰ ሀሳብ አስታራቂና አግባቢ ሆኖ መምጣቱ ዋጋው ብዙ ነው።

አንድነት ሰባኪ ክብረ በዓላት ሀገር በማቅናትና ትውልድ በመቅረጽ ረገድ ሚናቸው የትዬየሌለ ነው። በፍቅርና በእርስ በርስ ጉርብትና የደረጁ እንደዚህ አይነት መንፈሳዊና የአደባባይ በዓላት ጥሩ መልዕክት በማስተላለፍ ከበጎ ማኅበራዊ እሴቶች ተለይተው የሚታዩ አይደሉም። መንፈሳዊነትን ለብሰው ከማኅበራዊ የተገለሉ ይምሰሉ እንጂ በዋጋቸውና እያደረጉ ባሉት አስተዋጽኦ የሀገር ካስማነታቸው ገዝፎ የሚታይ ነው።

መስቀል በደመራ ጽንሰ ሀሳብ አብሮነትንና ብዙሀነትን ከዋጀ ተለያይተን ለቆምነው ለእኛ መልዕክቱ የገዘፈ ነው። መንፈሳዊ በዓላት ከዝማሬና ከመንፈሳዊ ሥርዓታቸው ጎን ለጎን ሊያስተምሩን የሚገባ ብዙ ነገር አለ። እየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጅ ሲል በመስቀል ላይ ከተሰቀለ፣ ተሰቅሎም ከሞተልን እኛስ ስለሌላው ምንድነው የሚሰማን? እሌኒ ፍቅር አስገድዷት መስቀሉን ከተሰወረበት ካገኘች የእኛስ የቤት ስራ ምንድነው? እና መሰል ጥያቄዎች የመስቀልን ክብረ በዓል እያከበርን አብረን የምንመልሳቸው ናቸው። በጥላቻና በመገፋፋት የፍቅር አምላክ እየሱስን ከሕይወታችን፣ ከቤታችን፣ ከሕይወታችን እናርቀዋለን እንጂ አናቀርበውም።

መስቀል መልካችን ነው፤ ጥንተ ወዛችን። መንፈሳዊ በዓሎቻችን በሥርዐትና በጨዋነት የተባ ኢትዮጵያዊነትን ካስገኙልን በረከቶቻችን መካከል ናቸው። እያከበርናቸው የመጣነው በዚህ መንፈስ ነው። ወደፊትም የምናከብራቸው በዚህ መንገድ ነው። መስቀል ከጽኑ ፍቅር መሃል የፈለቀ ክርስቶሳዊ ዋጋ ነው። ዋጋው በሁላችንም ላይ ተገልጦ ከጥል ወደፍቅር፣ ከክርክር ወደውዳዴ የምንሸጋገርበት ቢሆን ብዙ ትርፍን ያስገኝልናል።

በዓሎቻችን የነበረውን አጥብቀን በፍቅርና በወንድማማችነት ከመቼውም ጊዜ በላይ አንድ የምንሆንባቸው ናቸው። የመስቀሉ ፍቅር በዚህ ካልተተረጎመ በሌላ ቢተረጎም ልክ አይሆንም። መስቀል የፍቅር አደራ ነው ካልን፤ ፍቅራችን ወሰን ሊኖረው አይገባም። ፍቅር የክርስቶስ የእውነት ወዝ ያረፈበት ነው ካልን፤ ወዛችን ወደሌሎች ሊተላለፍ ግድ ይለዋል። መስቀል ሞት የሞተበት፣ ፍቅር የተወለደበት ነው ካልን ፍቅርን አምጦ መውለድ ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል።

የወረስነው ውርሳችን ተከባብሮ አብሮ መኖር ነው። ውርሳችን አብሮ ማክበር፣ አብሮ መሆን ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን በአንዱ በዓል ቤተኛ በመሆን አብሮ በማክበር ጥሩ ሥም ያለን ነን። የእኔ በሌለበት ኢትዮጵያዊነት ከትላንት ወደዛሬ ስንጓዝ ዋስትና ያደረግነው ጽኑ ጉርብትናችንን ነው። በአንድ መርፌና ክር የተጣፍንባቸው በልዩነት ውስጥ የደመቅንባቸው እልፍ ባህሎች እና መንፈሳዊ በዓላት አሉን። ከነዚህ ባሕሎች መሃል መስቀል አንዱ ሆኖ መጥቷል።

ልቦቻችን እንደነጠላዎቻችን ፀዓዳ ለብሰው ፍቅር መስካሪ እንዲሆኑ እና ከእዳ እንዲያወጡን ይገባል። እንደአለባበሳችን፣ እንደዜማችንና እንደመንፈሳዊነታችን ልናስተካክላቸው የሚገቡ የተዘበራረቁ ብዙ ነገሮች አሉ። መስቀል መንፈሳዊነት ከዓለማዊነት ጋር ሳያብር የቄሳርን ለቄሳር የክርስቶስን ለክርስቶስ የምንሰዋበት የመሰዊያ ሥፍራችን ነው። መንፈሳዊ በዓላት የንሰሀ እና የሱባዔ ስፍራ በመሆን የሚያገለግሉንም ናቸው። በደሎቻችንን ተናዘን ለተሀድሶ እንድንበቃ በዚያ በኩል ብዙ መንገዶች ይከፈታሉ።

በመስቀል ስለሀገራችን እንጸልያለን፣ ስለሕዝባችን እንማልዳለን። በመስቀል

> **ከጽድቅ በቀር አንዳች በደል የሌለበትን እየሱስ ክርስቶስን ወንጀለኛ በማድረግ በመስቀል ላይ ሰቅለውታል**

በዝማሬያችን ፈጣሪ ሰላም እንዲሰጠን፣ አብሮነታችንን እንዲያጠነክር እንጠይቀዋለን። የመስቀሉ ፍቅር እንዲህ ባለው ለሁሉ በሚተርፍ ሰላማዊ አካሄድ ካልተገለጠ የጣመ ትርጉም አይኖረውም። በመስቀሉ ስም ክርስቶስን ለብሰን አዲስ ለመሆን በፍቃዱ ስር ማረፍ ይኖርብናል። የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ፆምና ፀሎት የሚፈልግ ነው። መንፈሳዊ በዓላት ደግሞ ለዚህ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ ናቸው። የመስቀል በዓልን ስናስብ እንዳለፈው ጊዜ ስለሀገራችን፣ ስለሕዝባችን፣ ስለትውልዱ በማሰብ መሆኑ የተስፋ ብርሃን የሚፈነጥቅ ነው።

የመስቀል በዓል በየዓመቱ የአዲስ ዓመትን መግባት ተከትሎ የሚከበር የፍቅርና የመተሳሰብ በዓል መሆኑን መናገር ለቀባሪ ማርዳት ነው። እንቁጣጣሽ እንኳን መጣሽ ብለን፣ በመስቀል ወፍ እና በአደይ አበባ ታጅበን የፍቅር መልክ የሆነውን የመስቀል በዓል በመስቀል አደባባይ ማክበር ልዩ ስሜትን የሚጭር ነው።

ብዙሀነት ጌጣችንና አርማችን ሆኖ ከሚቀጥልባቸው የአደባባይ በዓላት መካከል እንደመስቀል ያሉ ጉምቱ ማኅበራዊ ስርዓቶች የሚዳብሩባቸው ክብረ በዓላት አሉ። ከአዲስ ዓመት ወደ ደመራ፣ ከዚያም ወደመስቀልና እሬቻ የምናደርገው ጉዞ የኢትዮጵያዊነትን ቀለም የሚገልጡ ሕብረ ትውፊቶቻችን ናቸው። በቀጣይም በአብሮነት የምናከብራቸው በብሔር ብሔረሰብ አስተሳሰብና ባሕል የደረጁ የዘመን መለወጫ በዓላት ደጃፋችን ስር አድፍጠዋል።

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ መስቀል የላቀ ቦታ አለው። የእምነቱ ራስ የሆነው እየሱስ ክርስቶስ ከሚገለጽባቸውና ከሚከበርባቸው አጋጣሚዎች አንዱ መስቀል ነው። አማኙን ከሚያመልከው አምላኩ ጋር አስተሳስሮና አቆራኝቶ፣ በቅዳሴውና በሰዐታቱ፣ በማህሌቱና በወረቡ መሀል ለምስጋና መሰዊያ የሚቀርብ የእምነት ዋስትና ነው። ከጎለጎታ የራስ ቅል ጀምሮ ዛሬም ድረስ መስቀል እየሳምን፣ እየባረክን፣ እየያዝንና በአንገታችን ላይ በማንጠልጠል እምነታችንን ገልጠናል። ከእንዲህ አይነቱ ታሪካዊ ዳራ በመነሳት የመስቀል በዓል ለኦርቶዶክሳውያን ልዩ ትርጉም አለው።

በመስቀሉ ጥልን ገሎ፣ ሀፅያታችንን ይቅር ብሎ፣ በደላችንንም ሽሮ በሞቱ ታርቆናል ስንል፤ የተሰቀለውን ጌታ ከተሰቀለበት መስቀል ጋር አመሳጥረን ነው። አአትብ ገጽዩ በኩለንታዩ በትምህርተ መስቀል ብለን የምናማትበው ለመስቀል ካለን ፍቅር የተነሳ ነው። ክርስቲያንና መስቀል የአንድ አካል ፊትና ኋላ ናቸው። በልብሰ ተክኖ፣ በካባላንቃ፣ በአስኬማ፣ በድንቅ ዜማ ታጅበን ደመራችንን እንለኩሳለን።

መስቀል ለሰው ልጆች ሁሉ የድህነት ምልክት ሆኖ ይታሰባል። ‹በመስቀሉ ጥልን ገደለ› የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮት ላነሳሁት በኩረ ሐሳብ ምስክር በመሆን የሚያግዝ ነው። የትኛውም ሀይማኖታዊ በዓል ፈጣሪ የሚመሰገንበት፣ ክብሩ የሚገለጥበት መሆኑ ይታወቃል። የመስቀል በዓልም ፈጣሪ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ዳግም ሕይወትን እንደሰጠንና ጥልን በፍቅር እንደሻረ አንዱ ማሳያ ነው። በመሆኑም የመስቀል በዓል የፍቅርና የይቅርታ፣ የእርቅና የጉርብትና ሃይማኖታዊ በዓል ነው ብል ተሳሳትክ አትሉኝም።

‹በመስቀሉ ጥልን ገደለ› የሚለው ኃይለ ቃል የመስቀሉ ኃይል ከተገለፀባቸው ግብር እና ንግግር መካከል ዋነኛው ነው። ይህ እውነት የመስቀል በዓል የክብረ-በዓሉ ዋና ዓላማ ሆኖ ከዘመን ዘመን ሲከበር መጥቷል። በመስቀሉ ጥልን ገደለ ስንል ፍቅርን ሰጠን፣ ከሀፅያት አነጻን፣ ከወደቅንበት አነሳን፣ ከዲያቢሎስ ግዞት ነጻ አወጣን እያልን ነው። በተዘዋዋሪ አንድነትንና ሰብዓዊነትንም እየሰበከን ነው።

ከክርስቶስ ስቅለት በኋላ ዓለም ዳግመኛ ተፈጥራለች። ዓለምን ለማዳን ከተጠበበው ጥበብ በላይ በሞቱ የሰውን ልጅ ያዳነበት ጥበቡ እንደሚበልጥ ቅዱሳን መጽሐፍቶች ይናገራሉ። ስለሆነም የመስቀል በዓል ትርጓሜው በዚህ ሚዛን የሚለካ በዓል ነው። ደመራ ደምረን፣ በችቦ ራስ ላይ እሳት ለኩሰን እሌኒን እንዘክራለን። በማግስቱ መስቀል ኃይላችን ነው ስንል ክብረበዓሉን በደመቀ መልኩ እናከብራለን።

በሚዛናዊነት ካየናቸው፤ ሁሉም መንፈሳዊ በዓላት ከጋራ ማንነት ውስጥ የተፈለቀቁ የጋራችን ናቸው። ለዚህም ነው በክርስቲያንና በሙስሊሙ ሀይማኖታዊ በዓላት ላይ ከምንም በላይ የአብሮነት መንፈስ የሚታየው። የሀይማኖት መቻቻል ምልክት ሆነን በዓለም አደባባይ የምንጠራው ብቻነትን በሻረ የእርስ በእርስ ትቅቅፍ ነው። መስቀልንም ፈጣሪን ባስቀደመ፣ ሰውነትን ባስከተለ መንፈሳዊ ሥርዓት እንደተለመደው በጋራ እናከብረዋለን።

የመስቀል በዓል የአከባበር ሥርዓትና የመንፈሳዊ ትርጓሜው አሁን ላለው ሀገራዊ ሁኔታ መልካም መንፈስን የሚያላብስ ነው ብዬ አስባለሁ። ከአከባበሩ ስንነሳ አንድነትና ራሮት ይታይበታል። ፍቅርን ያነገበ መንፈሳዊ መነሻ አለው። ትርጓሜውን ስናይ ደግሞ በፍቅር ጀምሮ በፍቅር የሚያበቃ እዝነተ ልብ ነው። አሁን ያለንበት ሁኔታ ፍቅር የቀዘቀዘበት፣ ቡዳኔና ጎራ የገዘፈበት፣ እኔነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ያየለበት፣ ጥልና ክርክር፣ ጥላቻና ትርክት የሰፋበት ወቅት ነው። ታዲያ የመስቀል መንፈስ አያስፈልገንም ትላላችሁ? ጥልን በመስቀሉ እንደገደለ እኛም ፍቅርን ከመስቀሉ አምጠን መውለድ ይጠበቅብናል። መልካም በዓል።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የግሉን ዘርፍ ኢኮኖሚያዊ ድርሻ የሚያሳድገው አጋርነት

አንተነህ ቸሬ

በበርካታ የዓለም ሀገራት የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ውስጥ በየጊዜው እያደገ የመጣ ሚናን መጫወት የቻለው ‹‹የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት›› (Public Private Partnership - PPP)፣ ብዙ ሀገራትም መንግሥታዊ አገልግሎቶችን በግሉ ዘርፍ በኩል እንዲያቀርቡ እድል ፈጥሯል። ይህ አጋርነት መንግሥት በራሱ ማቅረብ የሚገባውን አገልግሎት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመቀናጀት እንዲያቀርብ የሚያደርግበትን አሰራር እንዲዘረጋ አስችሏል።

የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት ሁሉንም የምጣኔ ሀብትና የፖለቲካ ጥናት ባለሙያዎች የሚያስማማ ትርጓሜ አልተገኘለትም። የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት እንዲጠናከር ድጋፍ ከሚያደርጉ ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው የዓለም ባንክ (World Bank)፣ የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት ‹‹መንግሥትና የግሉ ዘርፍ በረጅም ጊዜ የውል ስምምነት አገልግሎቶችን ለማቅረብ በትብብር የሚተገብሩት አሰራር›› እንደሆነ ይገልፃል።

የዓለም የገንዘብ ድርጅት (International Monetary Fund - IMF) በበኩሉ፣ የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነትን፣ ‹‹በተለምዶ መንግሥት ያቀርባቸው የነበሩ አገልግሎቶች በግሉ ዘርፍ በኩል እንዲቀርቡ የሚያስችል አሰራር›› ብሎ ይተረጉመዋል። በድርጅቱ ትርጓሜ መሰረት በመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት አሰራር ስርዓት፣ መንግሥት የሚያቀርባቸው አገልግሎቶች በግሉ ዘርፍ ሲቀርቡ የግሉ ዘርፍ የአገልግሎቶቹን የፋይናንስ፣ የግንባታና የአስተዳደር/አመራር ኃላፊነቶችን ይረከባል።

የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት ‹‹የአገልግሎት አቅርቦትንና ተደራሽነትን ዓላማቸው ባደረጉ የመንግሥት ተቋማት እና ትርፍን ታሳቢ ባደረጉ የግል ዘርፍ ተዋንያን መካከል የሚደረግ የአገልግሎት አቅርቦትና አስተዳደር ስምምነት ነው›› የሚል ብያኔ የሚሰጠው ደግሞ የምጣኔ ሀብት ትብብርና ልማት ድርጅት (Organization for Economic Co-Operation and Development - OECD) የተሰኘው በይነ-መንግሥታዊ ተቋም ነው።

ሀገራትም ለመንግስትና የግል ዘርፍ አጋርነት የሚሰጡት ብያኔ እንደየሀገራቱ ነባራዊ ሁኔታዎች ይለያያል። ሀገራት የሚከተሏቸው የምጣኔ ሀብትና የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለሞች በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ አጋርነት በሚደረጉ ስምምነቶችም ሆኑ በአጠቃላይ አስፈላጊነታቸው ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ ይገመታል። ርዕዮተ ዓለሞቹ መንግሥትና የግሉ ዘርፍ በገበያ ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ስለሚወስኑ፣ በሁለቱ አካላት አጋርነት የሚከናወኑ ተግባራት ዓይነትና ወሰን የርዕዮተ ዓለሞቹ ጫና ሰለባ መሆናቸው አይቀርም።

በአጠቃላይ ‹‹የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት›› በሀገር ልማትና እድገት ውስጥ ዋነኛ ተዋንያን በሆኑት በመንግሥትና በግል ዘርፎች መካከል የሚደረግ የአገልግሎት አቅርቦትና የልማት ትብብር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት መገለጫ ከሆኑት ባህርያት አንዱ የግሉ ዘርፍ መንግሥት ለሕዝብ አገልግሎት ማቅረብ በሚገባው ዘርፍ ውስጥ መሳተፉ ነው። ቀጣይ ጊዜን ታሳቢ ያደረጉ የረጅም ጊዜ ስምምነቶች እና የሀብት፣ የክህሎትና የኪሳራ ክፍፍሎችም የአጋርነቱ ሌሎች መገለጫዎች ናቸው። አንዳንድ ሀገራት የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት የውል ጊዜ እስከ 25 ዓመታት ድረስ መዝለቅ እንዳለበት ደንግገዋል። የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን ኪሳራ ለሁለቱ ወገን ያከፋፍላል፤ ሁለቱ ተዋንያን ከኪሳራ በተጨማሪ ሀብትና ክህሎትንም ይጋራሉ።

በርካታ የጥናት ውጤቶች እንደሚያሳዩት፣ የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት ለኢንቨስትመንት ዘርፍ እድገት ትልቅ ሚና አለው። የባባሳሄብ አምቤድካር ዩኒቨርሲቲ (ሕንድ) መምህራኑ ጓራቭ ሲንግ እና መሐመድ ካሃን የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት በማኅበረሰብ ግንባታና በሀገር እድገት ላይ የሚኖረውን ሚና በዳሰሱበት ‹‹The Role of Public Private Partnership (PPP) in Building Society›› በተሰኘው ጥናታቸው፣ ብዙ የዓለም ሀገራት፣ በተለይም ታዳጊዎቹ፣ በመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት በኩል የመሰረተ ልማት ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በርካታ ተግባራትን እንደሚያከናወኑ ጠቁመዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት የመልካም አስተዳደር ስርዓትን ለማስፈን ሁነኛ ግብዓት ሆኖ እያገለገለ እንደሚገኝም አመላክተዋል። ይህ አሰራር በተለይም የማኅበራዊ አገልግሎቶችን ተደራሽነት ለማስፋት ለሚያስፈልገው ፋይናንስ ተጨማሪ ምንጭ በመሆን ለኢንቨስትመንት ዘርፍ ማደግ ከፍተኛ ሚና እንዳለው የባለሙያዎቹ ጥናት ያስረዳል። በአጠቃላይ፣ የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት የአገልግሎቶችን ተደራሽነትና ጥራት በማሳደግ ለኢንቨስትመንት ዘርፍ እድገት ምቹ መደላድሎችን የሚፈጥር ግብዓት ነው።

የዓለም ባንክ፣ ሀገራት የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነትን እንዲተገብሩና አሰራሩ እንዲጠናከር ድጋፍ ከሚያደርጉ ተቋማት መካከል በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል። የባንኩ የጥናት መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ ከ134 በላይ የዓለም ሀገራት የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት አሰራርን በተግባር ላይ አውለዋል። ከ15 እስከ 20 በመቶ የሚሆነው የእነዚህ ሀገራት የመሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት (Infrastructure Investment) የተገነባውም በዚሁ አጋርነት አማካኝነት ነው።

ባንኩም ይህን የአሰራር ስርዓት ለሚተገብሩ ሀገራት በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን (International Finance Corporation - IFC) እና በባለብዙ ወገን የኢንቨስትመንት ዋስትና ድርጅት (Multilateral Investment Guarantee Agency - MIGA) በኩል ከፍተኛ የፋይናንስ ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን፣ የአሰራሩ ትግበራ የሃገራቱን የመሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት ተደራሽነትና ጥራትን ለማሳደግ ላቅ ያለ አስተዋፅዖ እንዳበረከተ ባንኩ በክትትልና ድጋፉ ምስክርነቱን ሰጥቷል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥትም በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ የግል ድርጅቶች ጋር በጥምረት የመሠረተ ልማት አውታሮችን የመገንባት ተግባራትን ሲያከናውን ይታወቃል። እንዲህ ዓይነቱ አሠራር በተለያዩ ጊዜያት በወጡት የኢንቨስትመንት አዋጆች ውስጥም እውቅና ያገኘና የተደነገገ ነው።

የአጋርነቱን ትግበራ የተሻለ ውጤታማ ለማድረግና በትግበራው ሂደት የሚታዩ ክፍተቶችን ቅርፅ ለማስያዝ ያስችላል የተባለው ‹‹የመንግሥትና የግል አጋርነት አዋጅ›› (1076/2010) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መፅደቁ ይታወሳል። የመሠረተ ልማት ሥርዓቱን ጨምሮ የአገሪቱን የልማት ግቦች ከማሳካት አንጻር የግሉ ሴክተር ወሳኝ ስትራቴጂያዊ አጋር መሆኑ በአዋጁ ላይ የተመላከተ ሲሆን፤ አዋጁ ግልጽነትን፣ ፍትሐዊነትን እና ዘላቂነትን ለማስፈን እና በግሉ ዘርፍ የፋይናንስ አቅም የሚገነቡ የመሠረተ-ልማት ፕሮጀክቶችን ለማበረታታት የሚረዳ አመቺ የሕግ ማዕቀፍ እንደሆነም ተጠቁሟል።

የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት እንዲጠነክር ምቹ ሁኔታ ከሚፈጥሩ አሰራሮች መካከል አንዱ በሁለቱ ዘርፎች መካከል የሚደረግ የጋራ ምክክር (Public-Private Dialogue) ነው። የጋራ ምክክሩ የግሉ ዘርፍ ያሉበትን ችግሮች ለመንግሥት በማቅረብ የግሉ ዘርፍ ጠንካራና ተወዳዳሪ ሆኖ በመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት ፕሮጀክቶች ላይ እንዲሳተፍ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

በኢትዮጵያም የግሉ ዘርፍ ከመንግሥት አካላት ጋር ምክክር እንዲያደርግ እድል የፈጠረው ብሔራዊ የመንግሥትና የግል ዘርፍ የምክክር መድረክ (National Public-Private Dialogue)፣ የግሉ ዘርፍ ያሉበት ችግሮች በጥናት ተለይተው ለመንግሥት ሲቀርቡበት ቆይቷል።

የግሉ ዘርፍ ወኪል በሆነው የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሚዘጋጀው ይህ የምክክር መድረክ፣ በወቅቱ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና በምክር ቤቱ መካከል በተደረገ ስምምነት፣ በ2002 ዓ.ም የተመሰረተ ሲሆን፣ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ መካከል ያለውን የልማት ግንኙነትና አጋርነት ለማጎልበት እንዲሁም ለንግድና ኢንቨስትመንት ማነቆ የሆኑ ችግሮች እልባት እንዲያገኙና ለአፈፃፀማቸው ክትትል የሚደረግበት ስርዓት እንዲኖር ታስቦ የተቋቋመ መድረክ ነው።

ይህ መድረክ በ2007 ዓ.ም በዓለም አቀፍ ደረጃ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የምክክር መድረኮችን በሚደግፈውና በየዓመቱም ክንውኖቻቸውን በሚገመግመው ዓለም አቀፉ የግልና የመንግሥት ምክክር መድረክ ኮሚቴ ‹‹ለረዥም ጊዜ ዘላቂ የሆነ የምክክር መድረክ በማካሄድ›› እውቅና እንደተሰጠውም ይታወሳል።

አራተኛው ሀገር አቀፍ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የምክክር መድረክም በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ትብብር የግሉ ዘርፍ ተዋንያንና የመንግሥት አካላት ተወካዮች በተገኙበት በቅርቡ መካሄዱ ይታወሳል። በመድረኩ ላይም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት አቶ ሰብስብ አባፊራ፣ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የምክክር መድረክ መንግሥትና የግሉ ዘርፍ ስለንግዱ ማኅበረሰብ ችግሮች የሚወያዩበትና ቀጣይ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚያስቀምጡበት መድረክ እንደሆነ ይገልጻሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፣ የምክክር መድረኩ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ መካከል ውይይትን፣ ትብብርንና ስትራቴጂካዊ አጋርነትን ለማጎልበት ወሳኝ መድረክ ሆኖ ያገለግላል። በግሉ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲሁም በማክሮ ኢኮኖሚው የለውጥ ሂደት የግሉ ዘርፍ የሚጠበቅበትን እንዳያበረክት እንቅፋት የሆኑ ተግዳሮቶችን በመለየት መፍትሄ ለማበጀት የላቀ ሚና ይኖረዋል።

‹‹የአጋርነት መድረኩ በጥናት የተለዩ የግሉ ዘርፍ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች ይቀርቡበታል። በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ምክክር መደረጉ በንግድ ሥርዓት ውስጥ የሚያጋጥሙትን ክፍተቶች በጋራ ተወያይቶ ለመሙላት ከማገዙም ባሻገር፤ የንግድ ስርዓቱን ለማዘመን፣ በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት፣ የልማት አጋርና አብሮ የመስራት ባህልን ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል›› በማለት ይገልፃሉ።

አቶ ሰብስብ ምክር ቤቱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ እና የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚውን የመሪነት ሚና በአግባቡ እንዲወጣ እየሰራ መሆኑን ጠቁመው፣ በቀጣይም የግል ዘርፍና መንግስት ተቀራርበው እንዲሰሩና ለሚያጋጥሙ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ እንዲያገኙ ለማድረግ የግሉ ዘርፍ ድምጽነቱን ለማጉላት እንደሚሰራም ተናግረዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዶ/ር ካሳሁን ጎፌ፣ የአጋርነት ምክክሩ የግሉ ዘርፍ ተግዳሮቶች የፖሊሲ መፍትሄዎችን እንዲያገኙ፣ የልማት አጋርነት እንዲጎለብትና አብሮ የመስራት ባሕል እንዲዳብር፣ በሀገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ የጋራ ግንዛቤና መግባባት እንዲፈጠር እንዲሁም ባለሃብቶች ጥራት ያላቸውና ተወዳዳሪ ምርቶችን እንዲያመርቱ እና በወጪ ንግድ ዘርፎች ላይ በስፋት እንዲሰማሩ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንደሚያግዝ ያስረዳሉ።

‹‹መድረኩ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ መካከል ድልድይ ሆኖ ያገለግላል። ከተለያዩ ዘርፎች የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት እንዲሰባሰቡና ሃሳብ እንዲለዋወጡ እድል በማመቻቸት ለምጣኔ ሀብት መሰናክል የሆኑ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ ይረዳል፤ የወል አሸናፊነት እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል። በመረጃ ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ ለመቅረፅ የሚያስችሉ ገንቢ አስተያየቶችን ለማግኘትም ያግዛል›› ሲሉ ያብራራሉ።

የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የላቀ ሚና እንዲኖረው በማሰብ መንግሥት የተለያዩ የምጣኔ ሀብት እርምጃዎችን/ማሻሻያዎችን እየወሰደ እንደሚገኝ የተናገሩት ዶ/ር ካሳሁን፣ በእነዚህ ማሻሻያዎች አማካኝነት የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ድርሻ እያደገ እንደመጣም ይገልፃሉ።

ከ2010 ዓ.ም ሀገራዊ ለውጥ ወዲህ፣ ባለፉት አምስት ዓመታት፣ መንግሥት ዘርፈ ብዙ የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብሮችን ተግባራዊ ማድረጉ ይታወቃል። ከእነዚህ መርሃ ግብሮች አንዱ፣ ሀገር በቀል የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብር (Homegrown Economic Reform Program) ነው። የመርሃ ግብሩ ዓላማ አምራች የሆነውን የሠው ኃይል የሚሸከም የሥራ እድል እና የተረጋጋ የማክሮ-ኢኮኖሚ ከባቢ በመፍጠር እንዲሁም የግል ዘርፍ መር (Private Sector-Led) የሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመገንባት ዘላቂና ፈጣን የምጣኔ ሀብት እድገት ማስመዝገብ ነው።

የኢንቨስትመንት አዋጅና የንግድ ሕግ ማሻሻያዎች፣ ብሔራዊ የንግድና ቢዝነስ ስራ አመቺነት ማሻሻያ መርሃ ግብር (National Ease of Doing Business Initiative) እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የግብይት ስርዓት ጋር ዘመናዊ ትስስር ለመፍጠር የፋይናንስ ዘርፉ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆን ተወስኖ ውሳኔውን ለመተግበር እየተደረጉ ያሉ ዝግጅቶች የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ መርሃ ግብሩ አካል ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ በቅርቡ ወደተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር ትግበራ ገብታለች።

እነዚህ ማሻሻያዎች የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ሚና ለማሳደግ ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርጉ ይታመናል። የግሉ ዘርፍ በምጣኔ ሀብት ውስጥ የሚኖረው ሚና ሲያድግ ደግሞ ለኢንቨስትመንት ዘርፍ ማደግ ተጨማሪ አቅም የሚፈጥረው የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት ይጠናከራል።

**የመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት እንዲጠነክር ምቹ ሁኔታ ከሚፈጥሩ አሰራሮች መካከል አንዱ በሁለቱ ዘርፎች መካከል የሚደረግ የጋራ ምክክር (Public-Private Dialogue) ነው። የጋራ ምክክሩ የግሉ ዘርፍ ያሉበትን ችግሮች ለመንግሥት በማቅረብ የግሉ ዘርፍ ጠንካራና ተወዳዳሪ ሆኖ በመንግሥትና የግል ዘርፍ አጋርነት ፕሮጀክቶች ላይ እንዲሳተፍ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል**

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ጎሜ

# ኢትዮጵያን የመክበብ ሴራ እና የሚፈጥረው ስጋት

**አሲ ሴሮ**

> **በአጠቃላይ ግብጽ የመረጠችው መንገድ በኢትዮጵያ ሰራዊት የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ተመናምነው የነበሩት የአልሸባብና የአልቃኢዳ ኃይሎች እንደገና እንዲያንሰራሩና አካባቢውን የሽብር ማዕከል እንዲሆን በር የሚከፍት ነው:: ይህ ደግሞ ስጋቱ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝብ ጭምር ነው**

ሶማሊላንድ እኤአ በሰኔ 26 ቀን 1960 ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነጻ ወጥታ ራሷን ስትችል በደቡብ በኩል የኢጣሊያ ግዛት የነበረችው ሶማሊያም ለአስር ዓመታት ያህል በኢጣሊያ ስር የተባበሩት መንግስታት የሞግዚት አስተዳደር ሆኖ ቆይታ ሐምሌ 1 ቀን 1960 ነጻነቷን አገኘች። ሆኖም የተለያየ የአስተዳደር ብሂልና አካሄድ የነበራቸው ሶማሊላንድና ዋናዋ ሶማሊ ያለምንም ምክክር እና መግባባት እንዲዋሃዱ ተደረገ። ይህም ቅራኔ ፈጠረ። በተለያዩ ጎሳዎች መካከልም የማያባራ ሽኩቻ ተፈጠረ።

በአጠቃላይም ሶማሊ ከምስረታዋ ጀምሮ ያልጸናች በመሆኑም ዘወትር ግጭትና ሁከት አጥቷት አያውቅም። ይህም ሁኔታ ለአሸባሪዎችና ሰርጎ ገቦች ምቹ ሁኔታ ከመፍጠሩም ባሻገር አካባቢው በግጭትና በአለመረጋጋት እንዲታወቅ አድርጎታል።

በተለይም አልሸባብን የመሳሰሉ አሸባሪ ቡድኖች የሚፈነጩባት እና የበርካታ ሶማሊያውያንን ዜጎች ሕይወት የቀጠፈ ጨካኝ ቡድን መፈንጫም ሀገር ነው። በአልሻባብም የተነሳ በየቀኑ የፈንጂ አደጋ፤ የሽብር ጥቃትና ሞት በሶማሊያ የተለመደ ክስተት ነበር። ታዲያ በዚህ ሁሉ ስቃይ ውስጥ ሶማሌያውያንን ያስታወሰ አንድም ሀገር ወይም ዓለም አቀፍም ሆነ አህጉር አቀፍ ተቋም የለም።

ሶማሊያውያንን ዓለም በራሳቸው ወቅት ከጎናቸው የነበረችው ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ኢትዮጵያ ለ17 ዓመታት ያህል ሰላም አስከባሪ ኃይሏን በማሰለፍ ጨካኙን አልሸባብ ቡድን ስትፋለም ቆይታለች። በዚህም በርካታ ውድ ልጆቿ ሕይወታቸውን ጭምር ገብረዋል።

ሆኖም ሶማሊያውያን ሲቸገሩና በየዕለቱም በሽብር ጥቃት ሲሞቱ ግድ ያልነበራቸው ግብጽን የመሳሰሉ ሀገራት ዛሬ ተቆርቋሪ መስለው መጥተዋል። በሰላም አስከባሪ ስም ኢትዮጵያን ለመክበብ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ለዓመታት ሶማሊያውያን የፈንጂ ናዳ ሲዘንብባቸው ቃል ተንፍሳ የማታውቀው ግብጽ ዛሬ የሶማሊያውያን ተቆርቋሪ ሆና ብቅ ብላለች። ሰላምን ለማደፍረስ ሰላም አስከባሪ ሆኜ በሶማሊያ እሰማራለሁ የሚል ጨኸት በማስተጋባት ላይ ትገኛለች።

ሰሞኑን ደግሞ በደቡብ ሱዳን ውስጥ ሰላም አስከባሪ ሆና ለመሰማራት ፍላጎት እንዳላት አስታውቃለች። ለዚህም አሜሪካንን ድጋፍ አግኝታለች። በአሜሪካ ዘንድም ግብጽ የአህጉሩ የጸረ ሽብር አጋር እና የሰላም አስከባሪ ዋነኛ ተዋናይ መሆኗ ማስተማመኛ ተሰጥቷታል።

ሆኖም ግብጽ በየትኛውም የጸረ ሽብር ዘመቻም ሆነ የሰላም ማስከበር ጥረት ውስጥ ውጤታማ ሆና አታውቅም። በሳህል በረሃ እና በሊቢያ አካባቢ እንደ አሸን የሚርመሰመሱትን አሸባሪዎች መግታት ባልቻለችበት ሁኔታ ምስራቅ አፍሪካ ድረስ መጥታ ሰላም አስከብራለሁ ማለት ከጠብ አጫሪነት ውጪ የሚሰጠው ስያሜ የለም። ግብጽ እንደጦስ ዶሮ ኢትዮጵያን የምትዞረው ሰላም ለማስከበር እና ሽብርተኝነትን ለመከላከል ነው የሚል የሞኝ ሀሳብ ማሰብ አይቻልም።

ይልቁንም ግብጽ በሕዳሴው ግድብ ላይ ያጣችውን የበላይነት ለማካካስ በማሰብ ሌላ ካርድ ለመምዘዝ መሞከሯ ነው። ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ግዙፍ ኢኮኖሚ እየገነባች ያለች ሀገር ነች። የሕዝብ ቁጥሯም በአፍሪካ ሁለተኛ ደረጃ የያዘ እና በቀጣይም እያደገ የሚሄድ ነው። ስለዚህም የዚህን ሕዝብ ፍላጎት ለማሟላት መጠነ ሰፊ የልማት እንቅስቃሴ ያስፈልጋታል። ይህንን ለማሳካት ደግሞ በዋነኝነት አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እና የባሕር በር ጥያቄዎቿ ሊመለሱላት ይገባል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በኃይል እጥረት የሚሰቃይ ሕዝብ ነው። 60 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ምንም አይነት የኤሌክትሪክ አገልግሎት አያገኝም። አብዛኞቹ ፋብሪካዎች በኃይል እጥረት ምክንያት በተገቢው መጠን ለማምረት የሚቸገሩ ናቸው።

ስለዚህም ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ ሃብት ተጠቅማ የኃይል ፍላጎቷን ማሟላት ለነገ የማትለው ጥያቄ ነው። ይህን መሰረት በማድረግም ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በአባይ ወንዝ ላይ ታላቁን የሕዳሴ ግድብ በመገንባት ዛሬ ላይ ወደ ማጠናቀቁ ደርሳለች። እስካሁንም ባለው ሁኔታ አራት ተርባይኖች ወደ ኃይል ማምረት የገቡ ሲሆን ቀሪ ስራዎችም እስከ ያዝነው መጨረሻ ድረስ ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይታሰባል።

የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ኃይል ባመነጨበት ቅጽበትም ከሀገር ውስጥ ፍላጎት አልፎ ለጎረቤት ኬንያ እና ሱዳን ጭምር የኃይል አማራጭ መሆን ችሏል። በጎረቤት ሀገራትም ዘንድ የትብብር እና የወዳጅነት ማህተም ተደርጎ ይወሰዳል። በአጠቃላይ የሕዳሴውን ግድብ ጨምሮ ኢትዮጵያ የምታለማቸው ልማቶች ለራሷ አልፎ ለጎረቤት ሀገራትም ጥቅም እየሰጡ ነው። በተለይም የሕዳሴ ግድብ የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና በልማት እንዲተሳሰርና በሀገራት መካከል ትብብር እንዲፈጠር የማይተካ ሚና በመጫወት ላይ የሚገኝ ግዙፍ ፕሮጀክት ነው።

ሆኖም ይህ ግድብ እዚህ ደረጃ ላይ እስኪደርስ ድረስ በርካታ ፈተናዎችን አልፏል። በተለይም በውሃው ላይ የቅኝ ግዛት ውሎችን ጭምር በማንሳት የይገባኛል ጥያቄ የሚያነሱ ሀገራት ግንባታውን ለማስተጓጎል ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። በሀገር ውስጥ ሁከትና ብጥብጥ እንዲነሳ ቅጥረኞችን ከማሰማራት አንስቶ በጸጥታው ምክር ቤት ጭምር በርካታ ጫናዎች ተደርገውበታል።

ሆኖም የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግስት የያዙት ፍትሃዊ የመልማት ጥያቄ በመሆኑ ልማቱን ለማስተጓጎል የቻለ አንዳችም ኃይል የለም።

በተመሳሳይም ኢትዮጵያ ኢፍትሃዊ በሆነ መልኩ የባሕር በር ያጣች ሀገር ነች። በዚህም ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ እና ስነልቦናዊ ጫና ተዳርጋ ቆይታለች። ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነቷም አሽቆልቁሎ ቆይቷል።

ስለዚህም እያደገ የሚሄደውን የሕዝብ ቁጥሯን ለመመገብ እና የኢኮኖሚ ጥያቄዋን ለመመለስ የአማራጭ ወደቦች ባለቤት መሆን አለባት። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ሰላማዊ አማራጮችን እየተጠቀመች ነው።

ሆኖም የኢትዮጵያ ጥያቄ መልስ እንዳያገኝ የሚመኙ እና በሕዳሴው ግድብ የተሸነፉ ሀገራት ጉዳዩን የተለየ መልክ በመስጠት በሰላም አስከባሪ ስም ምስራቅ አፍሪካ ድረስ በመምጣት ቀጠናውን የግጭት ማዕከል ለማድረግ እየጣሩ ነው። በተለይም ላም ባልዋለችበት ኩበት ለቀማ እንደሚባለው ግብጽ ባልተሳተፈችበት የጸረሽብር እና የሰላም ማስከበር እንቅስቃሴ ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ ነኝ ስትል እየተደመጠች ነው። ሆኖም ለዘመናት በጸረ ሽብር እና በሰላም ማስከበሩ ሂደት የተሰጣትን ኃላፊነት በሙሉ በውጤታማነት የፈጸመችውን ኢትዮጵያን ገለል በማድረግ የሚከናወኑ የጸረሽብርም ሆነ የሰላም ማስበር እንቅስቃሴ ውጤት አልባ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው።

ኢትዮጵያ ሽብርተኝነትን በመከላከል ደማቅ ስም ያላት ሀገር ነች። በተለይም አልሸባብን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ የሽብር ቡድኖች አድማሳቸው እንዳይሰፋ እና የከፋ ጉዳት እንዳያስከትሉ ኢትዮጵያ ወታደሮቿን በመላክ ጭምር የሕይወት መስዋዕትነትን ከፍለዋል።

በዚህም የአልሸባብ ዓለም አቀፍ ስጋት እንዲቀንስ እና ሶማሊያም የተረጋጋች ሀገር እንድትሆን ኢትዮጵያ የማይተካ ሚና ተጫውታለች።

በተመሳሳይም ኢትዮጵያ በሰላም ማስከበር ታሪኳ ሁልጊዜ ከፊት የምትሰለፍ ሀገር ነች። በኮርያ እና በኮንጎ በመሰለፍ ታሪክ የማይሽረው የጀግንነት ስራ ሰርታለች። ከጎረቤታችን ሱማሌና ሱዳን ጀምሮ በሩዋንዳ፤ በቡሩንዲ እና ላይቤሪያ በሰላም አስከባሪነት በመሰማራት ሀገራቱ እንዲረጋጉና ወደ ሰላማቸው እንዲመለሱ በማድረግ ደማቅ ታሪክ ጽፋለች። ግጭት ባልቆመባቸው በሱዳን የአብዬ ግዛትና በሶማሊያ የሰላም አስከባሪ ኃይልን በመላክ ኢትዮጵያ ለአባል ሀገራቱ ጥላና ከለላ መሆን ችላለች። በቀውስ ውስጥ የምትገኘውን ሱዳንን ወደ ሰላም ለመመለስም በብቸኝነት የበኩሏን ጥረት በማድረግ ላይ የምትገኝ ሀገር ነች።

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የመጀመሪያው ትኩረት የጎረቤት ሀገራት በመሆናቸው ኢትዮጵያ ከየትኛውም ዓለም አቀፋዊም ሆነ አህጉራዊ ጉዳዮች በበለጠ ለጎረቤት ሀገራት የቅድሚያ ትኩረት ትሰጣለች። ይህንኑ መነሻ በማድረግም ግጭት እና ሁከት ውስጥ የሚገኙትን ሶማሊያ፤ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን በመሪዎች መካከል ተደጋጋሚ ውይይት እንዲደረግ ኃላፊነትን በመውሰድና አልፎ ተርፎም የሰላም አስከባሪ በመላክ ሀገራቱ አንጻራዊ ሰላም እንዲኖራቸው አበክራ በመስራት ላይ ትገኛለች።

ይህ ሁሉ ታሪክ ያላት ሀገር እያለች ዛሬ ግብጽ ብድግ ብላ የጸረ ሽብር እና የሰላም አስከባሪ ዋነኛ አጋር ነኝ ማለቷ ግርምትን የሚያጭር ነው።

በአጠቃላይ ግብጽ የመረጠችው መንገድ በምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ብዙ መዘዝ ይዞ የሚመጣ ነው። በመጀመሪያ ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሕዝብ የከፈለችውን መስዋዕትነት ከንቱ የሚያስቀርና ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት የተከፈለውንም የሕይወት ዋጋ ጭምር ዋጋ የሚያሳጣ ነው። በሌላም በኩል በኢትዮጵያ ሰራዊት የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ተመናምነው የነበሩት የአልሸባብና የአልቃኢዳ ኃይሎች እንደገና እንዲያንሰራሩና አካባቢውን የሽብር ማዕከል እንዲሆን በር የሚከፍት ነው። ይህ ደግሞ ስጋቱ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝብ ጭምር ነው።

በተለይም በአሁኑ ወቅት ሶማሊያን መንግስት እናግዛለን የሚሉ ወገኖች እየላኩት ያለው መሳሪያ ዞሮ ዞሮ በአሸባሪዎች እጅ ውስጥ መውደቁ ስለማይቀር ሁኔታውን እጅግ የከፋ ያደርገዋል። ሰሞኑን የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ታዬ አጽቀ ስላሴ እንደተናገሩት በሶማሊያ ባልተረጋጋ የደህንነት ሁኔታ ውስጥ በውጭ ኃይላት የሚደረግ የጦር መሣሪያ አቅርቦት በመጨረሻ ሀገሪቷ አሸባሪዎች እጅ ላይ እንድትወድቅ በር ሊከፍት የሚችል ነው።

አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ እንደተናገሩትም ኢትዮጵያ ሽብርተኞችን ለመዋጋት የምታደርገውን ጥረት አጠናክራ እንደምትቀጥል አረጋግጠዋል።

በሶማሊያ ድህረ የአፍሪካ ሕብረት ሽግግር ተልዕኮ በሶማሊያ (አትሚስ) የሚኖረው የኃይል ስምሪት ተገቢውን ጊዜ ወስዶ የተልዕኮዎን የኃላፊነትን፣ መጠን፣ የፋይናንስ ምንጭ እና ቅንጅት በአግባቡ መሠራት እንዳለበት አስረድተዋል። ሶማሊያ ባልተረጋጋ የደህንነት ሁኔታ ውስጥ በውጭ ኃይላት የሚደረግላት የጦር መሣሪያ አቅርቦት አሸባሪዎች እጅ ላይ ሊወደቅ እንደሚችል ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል።

አምባሳደሩ እንዳሉት ከሶማሊያ ጎን ቆመናል የሚሉ ወገኖች እየፈጸሙት ያለው ደባ ከቀጠናው አልፎ ለዓለም ስጋት የሚሆን ነው። በተለይም እየተዳከመ ያለውን የሽብር እንቅስቃሴ መልሶ እንዲንሰራራ የሚያደርግና መልሶም ሽብርተኝነት የዓለም ሰላም ስጋት እንዲሆን በር የሚከፍት ነው።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ እየተከተለች ያለውን ፍትሃዊ የመልማት እና የማደግ መስመር ለማደናቀፍ መሞከር እና በሰላም አስከባሪ ስም ወደ ምስራቅ አፍሪካ መዝለቅ መዘዙ ከቀጠናው አልፎ ለቀሪው ዓለም የሚተርፍ ነው።

ከዚያ ይልቅ ኢትዮጵያን መረዳት እና ችግሮችም ካሉ በውይይት መፍታት ዘላቂ ጥቅምን ለሁሉም የሚያጎናጽፍ ነው።

በአጠቃላይ ግብጽ የመረጠችው መንገድ በኢትዮጵያ ሰራዊት የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ተመናምነው የነበሩት የአልሸባብና የአልቃኢዳ ኃይሎች እንደገና እንዲያንሰራሩና አካባቢውን የሽብር ማዕከል እንዲሆን በር የሚከፍት ነው። ይህ ደግሞ ስጋቱ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝብ ጭምር ነው።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## በመስከረም ጉርሻ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

በመስከረም ጥባት፣ በወጋገኑ የሌት ንጋት በአደይ አበባ መሃል ፀዓዳውን ሸማ ተጎናጽፋ ለቆመችው ጥበብ፤ የኪነ ጥበብ የፍቅር ገጸ በረከቶች እልፍ ናቸው። ያረሰረሳትን ክረምት ሸኝታ በልምላሜ እንቡጥ ፍሬን እንደምታበቅለው፣ በፍካት ሳር ቅጠሉን እንደምታወዛው ምድር፤ ጥበብም እንዲሁ ናት። በወርሃ መስከረም እንቁጣጣሽ፣ በወርሃ መስከረም መስቀል ስር ያለች ጥበብ ጥጋብ ሀሴትን እንጂ እጦት ቁዘማን አታውቅም። ሸማው ካይነት ዓይነቱ፣ ከውበት ደምግባቱ ሙሉ ነው። ነብስን ከምታነጻው ውበት ጋር ስጋና አጥንትንም የሚያለመልሙ እልፍ ጉርሻና ቅምሻዎችም በመስከረም ይበረከታሉ። የምድር በረከት፣ የነብስ እርካታ ከጥበብ ጓዳ ውስጥ ይከታተላሉ። ከሞላው ነገር ላይ መርጦ፣ ከመረጡትም ላይ ጨልፎ ማቅረቡ የዓይን አዋጅ እየሆነ ልብን ቢያዋልልም መምረጡም፣ መጭለፉም እያዳገተም ቢሆን ግድ ነውና አስቀድመን ወደ መጽሐፍት ዓለም በረከት ለማምራትና ከተሰጠን ለመጉረስ ልብ ታጥበን እንሰናዳ። መቼም አንዲት ጉርሻ ታጣላለች እንደምንለው ሁለተኛውን ከመስቀል ክብረ በዓል የቤተ ጉራጌዎቹን ደጅ እረግጠን ከእጃቸው ላይ ቀምሰን እንጎርሳዋለን።




**"ጉርሻና ቅምሻ"**

በመጀመሪያው የጉርሻ እጅ የተጠቀለለው የመስከረም ወር አንደኛው ገጸ በረከት "ጉርሻና ቅምሻ" የተሰኘ የግለ ታሪክ መጽሐፍ ነው። የዚህ መጽሐፍ ደራሲና የግለ ታሪኩ ባለቤት የሆነው ደራሲ ማቲያስ ከተማ (ወለላዬ) ከአሁን በፊት የሀገሩን አፈር ለመጨረሻ ጊዜ የረገጠው ከ20 ዓመታት በፊት ነበር። ከሀገሩ ባህልና ወግ ሥርዓት ጋር ተሰነባብቶ የባዕድ ውሀ ቢጠጣም ልቦናና ምናቡ ግን ሀገሩ ላይ ከጠጣው በስተቀር ሌላ የጠማቸው አይመስሉም። ከዚህ ቀደም ደራሲውን በምን ሥራው እናስታውሰው ይሆን ብለን ካልን "የኔ ሸበት" በተሰኘው የግጥም መድብሉ ነው። ይህቺን የግጥም መድብል ሲያሳትማትም ሀገር ውስጥ አልነበረም። በጊዜው የሲውዲን ነዋሪ ነበር። አንድ ጊዜ የወጣውን እግሩን የመለሰውም አዲሱን የግለ ታሪክ መጽሐፍ ይዞ በቅርቡ ሲመለስ ነው። እንግዲህ በግጥም መድብሉ እያስታወስን በድርሰቱ ልናነሳው ነው። መጽሐፉ በሚያጎርሰን የብዕር እጅ ውስጥ ጉርሻ ሙሉ ጥጋብ፣ ቅምሻ ሙሉ ጥፍጥና አለው። እሁድ መስከረም 12 ቀን 2017 ዓ.ም በርካታ የኪነ ጥበብና የስነ ጽሁፍ ጠቢባንን ከወመዘክር አዳራሽ ውስጥ አሳድሞ ለመመረቅ በቅቷል።

ከጠለቀው የልጅነት ጀንበር ከትውስታ ጉድባ ላይ ተቀምጦ የኋልዮሽ ትዝታውን ያወሳበታል። ሙሉ ለሙሉ በእውነተኛ ታሪክ የተሰመሩ ይዘትና ጭብጦች ያሉት ግለታሪክ ሲሆን ታሪኩም ከልጅነት ትውስታ እየፈለቀ፣ ከወጣትነት ቁልቁለት ላይ እየፈሰሰ በስደት ወደ ባሕር ማዶ ይነጉዳል። ዓመታት ላይመለሱ ፊቱን ይዘው ሲገሰግሱ ከሀገሩ ባሕልና ወግ ቢያርቁትም የደራሲውን ትዝታዎች ሊፍቁት ግን አልተቻላቸውም። በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቃለሉት ታሪኮችና መቼቶቹ ከአሁኑ ዕድሜው ጋር ሲስተያይ፤ ከነበረባት ሲውድን የኢትዮጵያን ያህል የተራራቁ ቢሆንም ሲጽፍ ግን በምናብ ትውስታ ሳይሆን በዓይኖቹ እየተመለከተ የነበረ ያህል ነው። አብዛኛዎቹ ሴራዎችና መቼቶች ከዚህቹ የአዲስ አበባ ውጥንቅጥ ውስጥ እየተጋፉና ከሰማይዋ ላይ እየተሸከረከሩ ወደ አንዲት ሸበቶ መንደር ይወስዱናል። ልጅነቱን የቦረቀባት፣ ሕይወትን በፊደላት ያጣጣመባት የቀድሞዋ ውቢት ኮረዳ፤ መርዕድ አዝማች ስብስቴ ነጋሴ ትምህርት ቤት ዙሪያ የትዝታ ክንፉን እየጣለና ከመንደሩ ማኅበረሰብ ጋር ከተጋመደው የኑሮ ዘዬና ወግ ባሕል ጋር ተጣብቆ ትናንትን በዛሬ ይመለከታታል። አይረሴ የትዝታ ማዕድ ጉርሻና ቅምሻዎቹንም የምናገኘው ከዚሁ ነው።

የተለያዩና በርከት ያሉ የታሪክ አቁማዳዎችን ባነገተው "ጉርሻና ቅምሻ" የግለታሪክ መጽሐፍ ውስጥ ይበል የሚያሰኙ አዳዲስ እይታና የአጻጻፍ ስልት ይታይበታል። አዳዲስ ታሪኮችን ለማንበብ የመጀመሪያዎቹን ገጾች በገለጥን ቁጥር በስንኝ ተቋጥረው በጭብጡ አስኳል የተቀመሙ ግጥሞችን እናገኛለን። በሀገራዊ ቃናና በትኩስ ሽታ የታጀበው ጭብጥ፤ የትዝታው የኋልዮሽ ዳራ የደራሲውን ሳይሆን የግላችን የሆነውን የኛን ታሪክ የምናነብ ያህል እንዲሰማን አሳምኖበታል። ቦርቀቅ ያሉና ሰፊ የሚመስሉ ታሪኮችን ቅልብጭ አድርጎ በሁለትና ሦስት ገጾች ብቻ በሚጣፍጥ ለዛ አኑሯቸዋል። በአንድ የግለ ታሪክ መጽሐፍ ውስጥ ገጸ ባህሪያቱ ከእውኑ ማንነታቸው ጋር እንዳይጋጩ በማድረግ መሳጭና ተወዳጅ ማድረጉ ልዩ ብቃትን የሚሻ ነው። ትውስታዊ እንጂ ምናባዊ ባለመሆናቸው ደራሲው እንዳሻው ሊስላቸውና ሊወክላቸው አይችልም። በጉርሻና ቅምሻ ውስጥ የምናገኛቸው አብዛኛዎቹ ገጸ ባህሪያት ደራሲው ኖረው ያለፉትን የጻፈው ሳይሆን የጻፈላቸውን የኖሩ ያህል ማራኪ ናቸው። አንዳንዶቹን ከመጽሐፉ ነጥለን በረዥም ልቦለድ ውስጥ ለማየት የምንቋምጣቸው ዓይነት ሆነው እናገኛቸዋለን።

መጽሐፉ ከተሸከመው የታሪክ ቋጥኞች መካከል አሁንም አንድ ጉርሻ ለጥል ነው እያልን ሁለቱን ብቻ እንቀማምሳቸው። ጉርሻው የሚያንቅ ቢሆንም የመጀመሪያው "ጥላ ወጊ" ነው። ለመሆኑ "ጥላ ወጊ" የምትል አዛውንት ፈሊጥ የሰማንም ሆን የምናውቃት ስንቶች እንሆን...ለማንኛውም በዚህ አርዕስት ስር ባለታሪኩ ደራሲ የሚነግረን ነገር ሁሉ ወደ እንጭጭ ልጅነቱ ይወስደናል። በልጅነቱ ጀምሮም በልጅነቱ ያከትማል። ጥላ ወጊው ግን የመንደሩ ሽማግሌ የነበሩ ባሻ አግዴ የተባሉ ሰው ናቸው። ነጭ ወረቀት በመሰለው የልጅነት አዕምሮው ውስጥ ያስቀመጠላቸው ጥላቻና ቂም ነበር። ጥላ ወጊ ናቸው ሲባል ሰምቷል። እንዲያውም የአባቱን ጥላ ወግተው የገደሉት እሳቸው እንደሆኑ ስለሰማ ከዚያን ከሰማበት ቅጽበት ጀምሮ ለሰውዬው ከጽኑ ጥላቻ በስተቀር ምንም አልነበረውም። "...እናቴ ግን በምታገኛቸው ጊዜ ቆማ ሰላምታ ሰጥታ ስለቤተሰብም ተጠያይቃ መለያየቷ ግርም ይለኛል። እኔ ግን ገና ና! ሳመኝ ማሙሽ ሲሉኝ ብሞት አልስማቸውም። ...የአባቴን ጥላ የወጉ እኔንስ ቢወጉኝ...አንድ ቀን አመሻሽ ላይ ልጫወት ከቤት ስወጣ ባሻ ብቻቸውን ጀርባቸውን ለቤታችን ሰጥተው ቆመው አገኘኋቸው። ብደነግጥም ቀስ ብዬ እቤት ተመልሼ የእናቴን ሸንኩርት መክተፊያ ቢላ ይዤ ወጣሁ። ባሻ እዚያው እንደቆሙ ናቸው። ቀስ ብዬ ተጠጋኋቸው። አላዩኝም። ከኋላቸው የተዘረጋውን ጥቁር ጥላቸውን ሁለት ጊዜ በቢላው ወግቼ ማንም ሳያየኝ እቤት ተመለስኩ..." እያለ የልጅነትን ቂልነት በሚጣፍጥና ድገሙኝ! በሚያስብል መልኩ አቅርቦታል።

**ከሁለተኛው ቅምሻ ትዝታን ብናጣጥም "የስብስቴ ትዝታ" ነው። ከትረካው ጅምር ፊት ይህቺ ግጥም ጉብ! ብላበታለች...**

ይሞታል የሰው ልጅ ሁሉም ቀኑ ሲደርስ፤
ከፉም ደግም ቢሆን መቼም ትዝታ አይፈርስ።
እኔም ይኼን ታሪክ በልቤ ቋጥሬ፤
ጊዜው ፈቀደና ዘረገፍኩት ዛሬ።

ከዘረገፈው ትዝታ የሆነው "የስብስቴ ትዝታ" የደራሲው የልጅነት ትምህርት ቤቱ ጣፋጭ የጉርሻ ሕይወት አጋጣሚዎቹን የሚያወሳ ታሪክ ነው። በዚህ ውስጥ ከእርሱ በላይ የብዙዎችን እውነተኛ ትዝታ የሚቀሰቅሱ አጋጣሚዎችና የተጠቀሱ ስሞች አሉበት። ንፋስ ስልክ መርዕድ አዝማች ስብስቴ ነጋሴ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከማይዘነጋቸው መምህራኖች መንደርደሪያ አድርጎ በመነሳት ከአንደኛው ልዩ መምህሩ ጋር ትረካውን ያጠነጥነዋል። "...ከትምህርት ቤቱ አስተማሪዎች መካከል ቆዳ እያሉ የሚሳደቡት ቲቸር ሐጎስ፣ ትምህርት ቤት ተዘግቶ ሲከፈት አንደኛው ዓይኑ ጠፍቶ ጥቁር መነጽር አድርጎ የመጣው ቲቸር መንግስቴ ጀርጀራ...ሳሙኤል አቤ (ሚስተር ጎት) ...መልኩን አሳምሮ እንደ ወሎ ፈረስ፣ ንግግር አያውቅም ድረስ የሚላት ነገር ነበረችው። እነዚህ ሊረሱ የሚችሉ አስተማሪዎች አይደሉም። ...ወደ ስድስተኛ ክፍል እንዳለፍኩ አንድ የክፍል ኃላፊ መምህር ገጠመኝ። ...ከሁሉም አስተማሪዎች ጎስቆል ብሎ የሚታየው እሱ ነው። ሆኖም መኪና ያለው ደግሞ እሱ ብቻ ነው። ...አንድ አስተማሪ ወይ ይወደዳል ወይ ይጠላል። እሱን ግን እናከብረው እንወደውና እንፈራው ነበር። ምክንያቱም የተማሪ ስም አይጠራም። ...ማስተማር በሚጀምርበት ጊዜ ግን አንዲት ኮሽታ አይፈልግም..." እያለ የሚቀጥለው ግለታሪክ ወስዶ ከአንድ ታሪካዊ ሰው ጋር ያገናኘናል። በደርግ አብዮት ወቅት የመጀመሪያውን ታሪካዊ ጥይት የተኮሰው እሱ ነው የሚባለው የበላይነህ ክንዴ ታሪክ ነው። ትንሹ ማቲያስ ከኢሕአፓው በላይነህ ክንዴ ጋር ቀደም ሲል የነበረው የተማሪና አስተማሪ አጋጣሚ የሚያወሳ ታሪክ ነው።

"ጉርሻና ቅምሻ" ከአርትኦት ሥራው ጀምሮ ጥንቅቅ ያለ ግሩም መጽሐፍ ስለመሆኑ በምረቃው ዕለት ተገኝተው ከሙያቸው ሀሳብ የሰነዘሩ ሁሉ አመስግነውታል። ኃይለ መለኮት መዋል "አበጀህ!" ሲል ስሜቱን በአንዲት ቃል ቋጫት። "ፈረንጅ ሀገር የተቀመጠ ሰው ኢትዮጵያዊ ድርሰት ይዞልን መጣ። እዚህ ያለን እኛ ግን ብዙዎቻችን ይህን ማፍራት አቅቶናል" ያለው ደግሞ ጸሀፊ ተውኔት አያልነህ ሙላት ነበር።

## መስቀልና አዳብና

የመስከረም የጥለት ሸማ ከፍ እያለ ከወገቧ ደረስኩ ደረስኩ ከሚለው የመስቀል ቅላጼ ጋር ይዞን ወደሀገር ቤት መንጎዱ የማይቀር ነው። የተሳለ ትዝታና ስል ትውስታ ያለበት ሁሉ አካላቱ እንጂ ነብስና መንፈሱ ከከተማው ጫጫታ መሀል መሆንን እንደ ኩነኔ ያስጨንቀዋል። መስቀል ሲመጣ ጉራጌ፣ ጉራጌ ሲባል መስቀል ይታወሰናል። ዓመቱን ሙሉ ከቀዬው እርቆ፣ ከሥራ ተጣብቆ የከረመው የጉራጌ ልጅ፤ የመስቀል መዳረሻ ብስራት ከሚበሰርበት የመስከረም ጥባት አንስቶ የቻለ በአካለ ስጋ ያልቻለም በሀሳብ ወደቀዬው ይተማል። የሀገር ቤቱ ጠረን በምናቡ ሸው እያለበት ናፍቆቱ ተቀስቅሶ ሽቅብ እየገነፈለ ልቡ መሄድ መሄድ ያሰኘዋል። እኛም ከሚነጉደው ጋር ነጉደን ከጉራጌዎቹ መስቀል ጥበብ የምትሰጠንን "አዳብና" ተቀብለን ጥቂት ብንጫወት ደስታ ነው። የዘንካታዎቹ ወጣቶችና ጉብል ልጃገረዶች ጨዋታ እንደደራ ሰንጋው ተጥሎ ከክትፎው ጉርሻ በፊት በቅቤና አዋዜ ነዶ የሚቀርበው ቅምሻ አላቸው። በልተን ጠጥተን በጨዋታው አዋዝተንና አወራርደን በአዳብና ሸማ ደምቀን እንመለስ። "አዳብና" ቀደም ሲል አዳምና ሔዋን የሚል የስም ትርጓሜ የነበረው ስለመሆኑ የጉራጌ ነገር አዋቂ ሽማግሌዎች ይናገሩታል። ብዙ የታሪክ ጥናቶች እንዲሚያስረዱት ከሆነ 800 ዓመታትን አልፎ የዘለቀ ድንቅ የባሕል ቱባ ነው። በቤተ ጉራጌ ውስጥ የክስታኔዎች ልዩ መገለጫ ነው። በመስቀል ሰሞን ወጣት ወንዶችና ጉብል ልጃገረዶች በሕብረ ባህላዊ ጥበብ በጋራ የሚያሸበርቁበት ነው። ይህን ሁሉ ዓመታትን አስቆጥሮ ዛሬን ቢደርስም ከእንግዲህ ወዲያ የሚያስቆጥረው ሌላ የዘመን ዕድሜው ጠፍቶ ለመቆረጥ ደርሶ ግን ነበር።

የመስቀል በዓል ጥበባዊ የባሕል ትውፊት ከሆነው የአዳብና ጨዋታ ፈርጁ ብዙ ነው። በዋናነትም ከማይጠገበው የጉራጊኛ ጭፈራ ጋር ይጀምራል። የጭፈራ ስልቱና ዓይነቱም አንድ አይደለም። "የቦላላ" ሞቅ ደመቅ ብሎ ይቆማል። "ጉሮሮ" እና "ማንጎሮም" ከጣፋጮቹ የጭፈራ ገበታዎች መካከል ናቸው። ታዲያ አይጠገቤው ጭፈራ ሲቀርብ የጆሮ ታምቡር በሚበጥስና ልብን በሚያነጥር ዘመን አመጣሽ ስፒከር አይደለም። ድመጸ መረዋ ከሆኑት ወጣቶች መካከል ለግጥምና ዜማ ይሰናዳሉ። በከበሮ ዓመታታቸው ቀልብን ከሚሰውሩት አንድሩን ለማንደር ከአንገት አንግተው ይጠባበቃሉ። የዚያን ሰሞን የክስታኔዎች መንደር ዓለም ዘጠኝ ብቻ አይደለችም። ወጣቶቹ የደስታን ጥግ የሚያጣጥሙበት ነው። ልጃገረዶቹ በነጻነት ዓለም ውስጥ ይንፏለላሉ። ምንም ዓይነት የቤተሰብ ጫና የማኅበረሰቡ ተጽዕኖ አይኖርባቸውም። የታላቋን የቃቄ ውርድዎት ራዕይዎች እውን ሆነው የሚታዩበትም ጭምር ነው። ለአብነትም ሴት ልጅ ውሀ አጣጪን መምረጥ ያለባት ራሷ ናት የሚለውን እሳቤዋን ከፍ የሚያደርጉ ትጭጭጮቶች በክብረ በዓሉ ላይ የአዳብና አካል ናቸው። በዚያን ሰሞን እንኳን ወጣቱንና ጭፈራው ራሱ ብቻውን አይቆምም። በግራና በቀኝ ያጀቡት ማድመቂያዎች ካዳሚ ናቸው። አጋት ዝላይ፣ ሰባ፣ ነጀ አራጀና ብትር ዝላዮች የወንዶቹ ለአቅመ አዳም ደርሻለሁ ማብሰሪያ ናቸው። የጉብሏን ልብ ለማዘለል በተለይ ብትር ዝላዩን በድል መወጣትና ብቁነቱን ማሳየት ይኖርበታል።

ጥንታዊውና 8 መቶ ያህል ዓመታትን የዘለቀውን የአዳብና ሥርዓትን የሞት አፋፍ ላይ ደርሶ ከገደሉ ለጥቂት ተርፏል። ቀደም ካለው ደማቅ ክንውን እየራቀና እየደበዘዘ መጥቶ ደብዛው ሳይጠፋ መትረፉ እድሜ ለአንድ ማኅበር ያሰኛል። የጉራጌ ክስታኔ ዓለም አቀፍ የወጣቶች ማሕበር ለዚህ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል። በ2013 ዓ.ም ማሕበሩ ሲመሠረት በጥቂት የበጎ ፈቃድ ወጣቶች ነበር። ከሀገር ወጭና በሀገር ውስጥ የሚገኙ



ቤተ ጉራጌዎችን በማሰባሰብና በማቀናጀት አባላቱን አብዝቶ ጉልበቱንም አጠንክሯል። ከተነሳበት ዓላማ አንዱ በሆነው የጠፉ የባሕል ትውፊቶችን ዳግም በመቀስቀስ ግብሩ ከአዳብና ጋር ተገናኝቶ ስሩን ደረሰበት። ከአፈር በታች ለቀብር የተሰናዳውን ቱባ የጥበብ ትውፊት እጁን ይዞ አስነሳው። ላለፉት ሦስት ዓመታት አዳብና በክስታኔ መንደሮች ውስጥ በፌስቲቫል ደረጃ ሲከበር ቆይቷል። ባለፈው ዓመት በጢያ ትክል ድንጋይ ዙሪያ በተደረገው ክብረ በዓል ላይ ብዙኀኑን ባስደመመውና በአፍሪካ ድንቃድንቅ ላይ በሰፈረው ግዙፍ የክትፎ ቁልል ላይ የሀሳቡ ፊታውራሪዎች እኚሁ የጉራጌ ክስታኔ ዓለም አቀፍ የወጣቶች ማሕበር አባላት ነበሩ። በዚህ ሳይቆሙ አሁን ደግሞ አዳብናን በዩኔስኮ ለማስፈር ደፋ ቀና እያለሁ ይገኛሉ። ማን ያውቃል በቅርቡ ደግሞ በዩኔስኮ ማሕደር ውስጥ የራሱን ኮታ ይዞ ከሚገኘው የመስቀል በዓል እቅፍ ውስጥ አዳብናን የምናገኘው ይሆን ይሆናል።

ከሞት ጥላ አምልጦ ዳግም ተወዳጅና ተናፋቂ ለመሆን የበቃው የአዳብና ክብረ በዓል ከመስከረም 16 እስከ ጥቅምት 5 ቀን 2017 ዓ.ም በምሥራቅ ጉራጌ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ባማረና በተዋበ መልኩ ይካሄዳል። በድምቀት ከሚከበርባቸው አንዷ የሆነችው የኬላ ከተማ መስከረም 18 ቀን "የተንቢ!" እያለች እጇን ዘርግታ ታላላቆችን ለመቀበል አሰፍስፋለች። መስቀል በጉራጌ፣ ጥበበን በባሕል፣ ክትፎውን በጉርሻ፣ ጨዋታውን በፌሽታና ደስታ ካሉ በመስከረም ከዚህ ወዲያ ጥጋብ ምን ይኖራል...

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ትውልድን ከሱስ የመታደግ ጥረት!

**አስናቀ ፀጋዬ**

ኢትዮጵያ በዓለም የጫት አቅርቦት የመሪነትን ደረጃ እንደመያዟ ከዓለም ከፍተኛ የጫት ተጠቃሚ ከተባሉ ሀገሮችም ከእነየመን፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ መካከል ትመደባለች። በሌላ በኩል በኢትዮጵያ የጫት ሱስ ተቀዳሚውን ሥፍራ ከሚይዙ የሱስ ዓይነቶች አንዱ ነው። የጫት ተጠቃሚዎች ቁጥር በጨመረ መጠን፣ የሱሰኞችም ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይነሳል። በቀደምት ጊዜያት የጫት ተጠቃሚነት በውስን የሀገራችን ክፍሎችና በተወሰኑ አካባቢዎች ይዘወተር የነበረ ቢሆንም፣ አሁን አሁን ግን የተጠቃሚው ቁጥር በተለይም በከተማዎች አካባቢ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃና ባሕል ሳይገድበው በየአካባቢያችን በበርካታ ሰዎች ሲዘወተር ማየት የተለመደ ሆኗል። በተለይ በወጣቱ አካባቢ አሁን አሁን ይህ ሁኔታ ጎልቶ ይታያል። በዚህም ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ዜጎች በጫት ሱሱ ምክንያት ለማኅበራዊ፣ ለኢኮኖሚው ቀውስ እየተዳረጉ ሲሆን በጫት የሚደርሰው የአዕምሮ ጤና ጉዳትም ከፍተኛ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዩኤንኦዲሲ በተደረገ ዳሰሳ ላይ እንደተቀመጠው፣ እ.ኤ.አ. በ1993 በአማኑኤል ሆስፒታል አልጋ ይዘው የአዕምሮ ሕክምና ከሚከታተሉ ታካሚዎች መካከል 43 በመቶው የአዕምሮ ሕመማቸው ከሱስ ጋር የተገናኘ ነበር። የጫት ሱስ ቀዳሚውን ሥፍራ ከሚይዙት መነሻ ምክንያቶችም ይመደባል። ይህም ችግሩ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እያስከተለ መሆኑን አመላካች ይሆናል።

እንደ ሀገር ይህን ችግር ለመከላከል የሁሉንም ማኅበረሰብ የነቃ ተሳትፎ ይጠይቃል። ከዚህ አንጻር ላግዛት የበጎ አድራጎት ድርጅትም በሀገራችን በተለይ አምራቹን የኅብረተሰብ ክፍል እየጎዳ ያለውን የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ በመከላከል የድርሻዬን መወጣት አለብኝ በማለት እንቅስቃሴ ጀምሯል። ከሰሞኑ ድርጅቱ ‘ትውልድን ከአደንዛዥ ዕፅ ሱስ እንታደግ’ በሚል ሀሳብ የሐረሪ ክልል መሠረት አድርጎ የሚተገበር ፕሮጀክት ይፋ አድርጓል። በዚህ ወቅት የላግዛት በጎ አድራጎት ድርጅት መሥራች እና ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ጽዮን አለማየሁ እንደተናገሩት፣ ላግዛት የበጎ አድራጎት ድርጅት በ2014 ዓ.ም የተቋቋመ እና በቦርድ የሚመራ ሀገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው። በድርጅቱ ተግባራዊ የሚደረገው ፕሮጀክቱ በዋነኝነት ቅድመ መከላከል ላይ ትኩረቱን ያደርጋል።

ድርጅቱ መነሻውን ሐረር ላይ አድርጎ የተቋቋመ እንደመሆኑም የፕሮጀክቱ ጅማሮውን በክልሉ ሊያደርግ ችሏል የሚሉት ወይዘሮ ጽዮን፣ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ሱስ አስያዥ ዕፅዋት መካከል አንዱ የሆነው ጫት በስፋት እየተዘወተረ እንደሆነ መረጃዎች ይናገራሉ። በተለይ በከተሞች አካባቢ የጫት ዕፅ ተጠቃሚው ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መሆኑን ጠቅሰው፤ የዚህ ተፅዕኖ ከሚስተዋልባቸው መካከል ሐረር ከተማ ተጠቃሽ መሆኗን ተናግረዋል። በከተማው ችግሩ የሚታይበት የማኅበረሰብ ክፍል በእድሜ የገፋ፣ ጎልማሶች እና ወጣቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በታዳጊ የእድሜ ክልል ላይ በሚገኙት ብሎም በነፍሰጡር ሴቶች ጭምር የሚታይ ነው ብለዋል።

የፕሮጀክቱ ተልዕኮ የማኅበረሰቡን የተለያዩ አካላት በማስተባበር የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ በኅብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰውን አስከፊ ውጤት መቀነስ ብሎም ማጥፋት ነው የሚሉት ወይዘሮ ጽዮን፣ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለማድረግ በክልሉ ከሚገኙ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር የጋራ ስምምነት መፈራረማቸውን ገልጸዋል። በዋነኝነት የክልሉ ጤና ቢሮ፣ የክልሉ ትምህርት ቢሮ፣ የክልሉ ሴቶች እና ሕጻናት ቢሮ፣ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን፣ የክልሉ ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ቢሮን የፕሮጀክቱ ባለድርሻ አካላት አድርጎ በአብሮነት እንደሚሠራም አስታውቀዋል ።

ፕሮጀክቱ ሐረርን መነሻ አድርጎ ይጀምር እንጂ በመላው ኢትዮጵያ ተደራሽ ለማድረግ ይሠራል የሚሉት የላግዛት በጎ አድራጎት ድርጅት የፕሮጀክት አማካሪ አንዱአለም አባተ (ዶ/ር)፣ በድርጅቱ ተግባራዊ የሚደረገው ፕሮጀክቱ በዋነኝነት ቅድመ መከላከል ላይ ትኩረቱን እንደሚደረግ ተናግረዋል። የችግሩ መስፋት አንዱና ዋነኛው ምክንያት ከግንዛቤ ክፍተት የመነጨ እንደሆነ ይታመናል። ስለዚህ በስፋት የሚስተዋለውን ችግር ለመቅረፍ ግንዛቤ መፍጠርን ዋነኛ መሣሪያ አድርጎ ሊነሳ መቻሉን አስረድተዋል።

በክልሉ በሚገኙ የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ መምህራን እና የተማሪ ወላጆች እንዲሁም ከትምህርት ቤቶች ውጪ የሚገኘውን የኅብረተሰብ አደንዛዥ ዕፅ ሱስ ምንነትና አስከፊነት በገጽ ለገጽ የሥልጠና መርሐ ግብሮች ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ይሠራል።

በሌላ በኩል ከትምህርት ቤቶች ውጪ የሚገኘውን አካል በተለያዩ የጽሑፍ፣ የራዲዮ፣ የቴሌቪዥን መገናኛ ብዙኃን ስለ አደንዛዥ ዕፅ ሱስ አስከፊነት ግንዛቤ መፍጠር፤ በአደንዛዥ ዕፅ ሱስ የተያዙ ተማሪዎችን በሥነ ልቦና ባለሙያዎች እገዛ ከሱስ እንዲላቀቁ የሚታገዙ ይሆናል። እንዲሁም ወጣቶች እና በሱስ የተጠቁ ዜጎችን ከሱስ እንዲያገግሙ ማገገሚያ ማዕከል ማቋቋም ከሱስ አገግመው ብዙ ዜጎች እንዲሆኑ የሚያግዝ መሆኑን አብራርተዋል።

በማኅበረሰቡ ልምድ የሆነና ወደ ባሕልነት የተጠጋ ከመሆኑ አንፃር፤ በአንድ ጊዜ የሚቀረፍ ችግር አይሆንም። ለዘመናት የተገነባው አስተሳሰብ ለመቀየር እና ለማረም ዓመታትን እንደሚወስድ አክለው ገልጸዋል። በዚህ ረገድ ሊገጥሙ የሚችሉ ፈተናዎች እንደሚኖሩም የሚጠበቅ ሲሆን፤ ስለዚህ ፕሮጀክቱ ተቀርፆ ወደ ተግባር ሲገባ ይሄንኑ ታሳቢ በማድረግ ነው ሲሉ ዶክተር አንዱዓለም ተናግረዋል ።


በሀገራችን የጫት ተጠቃሚዎች ቁጥር ከዕለት ዕለት እየጨመረ እንደመምጣቱ የጫት ጥገኝነት (ዲፔንዳንሲ) እና ሱስም አብረውት ከፍ እያሉ እንደሆነ ይስተዋላል። በሀገር ደረጃም የችግሩ ስር መስደድ አንጻር ትውልዱን ለማዳን ሰፊ ሥራ መሥራትን ይጠይቃል። ስለዚህ ችግሩን ለመቅረፍ እንደ ላግዛት በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ማበረታታት እና መደገፍ እንዲሁም ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ ማድረግና በጋራ ርብርብ በማድረግ ዓላማው በማሳካት ሀገርን መታደግ ይገባል።

# ዓለም አቀፍ

## በዓለማችን ከሦስት ሕፃናት አንዱ ‘አርቆ የማየት ችግር’ እንዳለባቸው አንድ ጥናት ይፋ አደረገ

በዓለማችን ከሦስት ሕፃናት አንዱ ቅርባቸው ያለ ነገር እንጂ አርቀው ማየት እንደማይችሉ አንድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሠራ ጥናት ይፋ አደረገ። አጥኚዎቹ እንደሚሉት የኮቪድ ወረርሽኝ በሕፃናት ዕይታ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሮ ያለፈ ሲሆን ሕፃናት ወጣ ብለው ከመጫወት ይልቅ ስክሪን ላይ ብዙ ሰዓት ማሳለፋቸው ጎድቷቸዋል።

ራቅ ያለ የማየት ችግር አሊያም በሳይንሳዊ አጠራሩ ማዮፒያ ዓለማችንን የሚያሰጋት ሲሆን በአውሮፓውያኑ 2050 በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናት ይህ ችግር ሊከሰትባቸው ይችላል ሲል ጥናቱ ያስጠነቅቃል። በጃፓን ካሉ ሕፃናት መካከል 85 በመቶ፣ በደቡብ ኮሪያ 73 በመቶው እንዲሁም በቻይና እና ሩሲያ ከ40 በመቶ በላይ የሚሆኑት ማዮፒያ እንዳለባቸው ጥናቱ ይጠቁማል።



ፓራጓይ እና ዑጋንዳ አንድ በመቶ ብቻ ሕፃናት የማዮፒያ ተጠቂ ያላቸው ሀገራት ሲሆኑ ዩናይትድ ኪንግደም፣ አየርላንድ እና ዩናይትድ ስቴትስ ደግሞ 15 በመቶ ላይ ተቀምጠዋል። ብሪቲሽ ጆርናል ኦፍ ኦፕታልሞሎጂ የተሰኘው የሕክምና ሕትመት ላይ የወጣው ሐተታ ከስድስቱም አኅጉራት ከተውጣጡ 50 ሀገራት ያሉ ከ5 ሚሊዮን በላይ ሕፃናትን በጥናቱ ዳሷል።

ከአውሮፓውያኑ 1990 እስከ 2023 ባለው ጊዜ ማዮፒያ በሦስት እጥፍ መጨመሩን ቁጥሮች ያሳዩ ሲሆን ይህ የእይታ እክል ባለፉት 33 ዓመታት 36 በመቶ ጨምሯል። አጥኚዎቹ እንደሚሉት ይህ ቁጥር መጨመሩ በግልፅ መታየት የጀመረው ከኮቪድ ወረርሽኝ በኋላ ነው።

ማዮፒያ ብዙውን ጊዜ የሚጀምረው ሕፃናት ትምህርት መቅሰም ሲጀምሩ ሲሆን በተለይ የዓይን ዕድገት በሚያቆምበት 20ኛው ዕድሜ አካባቢ መባባስ ሊያሳይ ይችላል። በምሥራቅ እስያ ያሉ በርካታ ሰዎች በማዮፒያ ተጠቂ ናቸው። ለዚህ አንደኛው ምክንያቱ በዘረ-መል ሊተላለፍ የሚችል በመሆኑ ሕፃናት ከወላጆቻቸው ስለሚወስዱት ነው።

እንደ ሲንጋፖር እና ሆንግ ኮንግ ባሉ ሀገራት ደግሞ ሕፃናት ገና በልጅነታቸው መጽሐፍት አሊያም ስክሪን ላይ ስለሚያፈጡ የዓይናቸው ጡንቻ መጨማደዱ ለማዮፒያ ሊያጋልጥ እንደሚችል ጥናቱ ያመላክታል። ሕፃናት ከስድስት እስከ ስምንት ዓመት ዕድሜያቸው ትምህርት በሚጀምሩበት አሕጉረ አፍሪካ ማዮፒያ ከእስያ ሲነፃፀር ሰባት እጥፍ ዝቅ ያለ ነው።

ጥናቱ እንደሚገምተው በአውሮፓውያኑ 2050 በዓለማችን ከሚኖሩ ታዳጊዎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ማዮፒያ ሊኖርባቸው ይችላል። ታዳጊ እና ወጣት ሴቶች ከታዳጊ እና ወጣት ወንዶች የበለጠ ለማዮፒያ ሊጋለጡ ይችላሉ፤ ምክንያቱም ወደ ውጭ ወጥቶ የመጫወት ዕድላቸው የጠበበ ነው ይላል ጥናቱ።


ምንም እንኳ በ2050 እስያ በማዮፒያ ከሌሎች አህጉራት በ69 በመቶ ልትበልጥ ብትችልም እያደጉ ናቸው የሚባሉ አሕጉራትም 40 በመቶ ሊደርሱ ይችላሉ ይላል። ሕፃናት በተለይ ደግሞ ዕድሜያቸው ከ7-9 በሚደርስበት ወቅት በየቀኑ ቢያንስ ለሁለት ሰዓታት ወጣ ብለው ቢጫወቱ በማዮፒያ የመያዝ ዕድላቸው ይጠባል ይላሉ የዩኬ ባለሙያዎች።

ነገር ግን ልዩነት የሚፈጥረው የተፈጥሮ የፀሐይ ብርሃን ይሁን አሊያም ሕፃናት ራቅ ያለ ቁስ ለማየት የሚጠቀሙት የትኩረት መጠን ገና አልታወቀም። “ያም ሆነ ይህ ሕፃናት ወጣ ብለው መጫወታቸው ጠቀሜታው እጅግ የጎላ ነው” ይላሉ የዩኬ ኦፕቶሜትሪስትስ ኮሌጅ ክሊኒካል አማካሪ ዳንኤል ሀርዲማን ማካርትኒ።

እንዲሁም ምንም እንኳ ቀድመው ቢመረመሩም ዕድሜያቸው ከ7-10 ያሉ ሕፃናት የዓይን ምርመራ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ሲሉ ይመክራሉ። ቤተሰብ መርሳት የሌለበት ነገር ማዮፒያ የሚተላለፍ መሆኑን ነው። እናት ወይም አባት ማዮፒያ ካለባቸው ሕፃናት የማዮፒያ ተጠቂ የመሆን ዕድላቸው በሦስት እጥፍ ይጨምራል።

ምንም እንኳ ማዮፒያ ሕክምና ባይኖረውም በመነፅር አሊያም በኮንታክት ሌንስ ሊስተካከል ይችላል። ማዮፒያ ያለባቸው ሰዎችን ዕይታ የሚያስተካክል ልዩ ሌንስ ቢኖርም ዋጋው ከፍተኛ ነው። ራቅ ያሉ ጽሑፎችን ለማንበብ መቸገር ለምሳሌ መማሪያ ክፍል ውስጥ ሰሌዳ ለማየት መቸገር፤ የኮምፒውተር ስክሪን አሊያም ተንቀሳቃሽ ስልክ በጣም ቀረብ አድርጎ መመልከት፤ ራስ ምታት እና ዓይንን ቶሎ ቶሎ ማሸት የማዮፒያ ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት



## "የኢዳዋይ" ፍሬዎች ከዱባዩ ክለብ እስከ ወጣት ብሔራዊ ቡድን

**ቦጋለ አበበ**

ባለፈው የአፍሪካ ዋንጫ ከ24 አገራት 630 ያህል ተጫዋቾች ብሔራዊ ቡድኖቻቸውን ሲወክሉ ከነዚያ ተጫዋቾች መካከል 200 ያህሉ የተወለዱት ወይም የእግር ኳስ ክህሎታቸውን ያጎለበቱት ከአፍሪካ ውጪ ነው። 104ቱ በፈረንሳይ የተወለዱ ወይም በሀገሪቱ የሥልጠና መንገድ የተገሩ ናቸው። 24 ተጫዋቾች በስፔን፣ 15 በእንግሊዝ፣ 13 በኔዘርላንድስ፣ 10 ደግሞ በፖርቹጋል።

በ2022 የዓለም ዋንጫ ግማሽ ፍፃሜ በመድረስ የመጀመሪያዋ አፍሪካዊት አገር የሆነችው ሞሮኮ መሠረታቸው አውሮፓና ሌሎች ሀገራት ያደረጉ 18 ያህል ተጫዋቾች በስብስባ መካተታቸው ትልቅ አስተዋፅዖ ነበረው። ጠንካራ ብሔራዊ ቡድን ያላቸው እንደ አልጄሪያ፣ ሴኔጋል፣ ናይጄሪያ፣ ኮትዲቯርና ሌሎችም በርካታ ሀገራት ወሳኝ የሆኑ በርካታ ተጫዋቾቻቸው የእግር ኳስ መሠረታቸው ከአፍሪካ ውጪ ነው። በዚህም ውጤታማ እየሆኑ ይገኛሉ። ተጫዋቾች ከታዳጊነት አንስቶ የዳበረ የእግር ኳስ ባሕል፣ በዘመናዊ ሥልጠናና ሳይንሳዊ መንገድ መገራታቸው ለየቡድኖቻቸው የተሻለ ነገር እንዲያበረክቱ ማድረጉ አያከራክርም።

ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ዕድለኛ አይደለችም። የእግር ካስ ሥርዓቷ ከመሠረተ ልማትና ከሥልጠናው ጀምሮ ወይ አልዘመነ ወይም ሌሎቹ የአፍሪካ አገራት የሚጠቀሙትን ዕድል አልተጠቀመች በተለመደው መንገድ መጓዟን ቀጥላለች። ለዚህም ነው ለመጨረሻ ጊዜ በተሳተፈችበት አፍሪካ ዋንጫ ከ24 ሀገራት መካከል አንድም ተጫዋች ከሀገር ውጪ የተወለደ ወይም ውጪ ቀመስ ያላካተተች ብቸኛዋ ሀገር የነበረችው። ለዚህም ሕገ መንግሥቱ ጥምር ዜግነት አለመፍቀዱ ዋነኛው ምክንያት ነው። ለዚህ ግን አንድ መፍትሔ አለ፣ ተሰጥዖ ያላቸው ታዳጊ ኢትዮጵያውያንን መልምሎ የተሻለ መሠረተ ልማትና የእግር ካስ ሲስተም ባላቸው የውጪ ሀገራት እንዲጎለብቱ ማድረግ። ግን እንዴት?



**ቢንያም ደስታው፣**



**ናትናኤል አረጋዊ፣**

ይህን ጥያቄ ለመመለስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያውያን ባለተሰጥዖ ታዳጊዎች ዓለም አቀፍ ተፈላጊነት እንዲያገኙ መንገድ የሚጠርጉ ፕሮጀክቶች ብቅ ማለት ጀምረዋል። በቀድሞው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንና የኢትዮጵያ የቡና ተጫዋች አሠልጣኝ ዕድሉ ደረጄ የሚመራው ዕድሉ አካዳሚ (ኢዲዋይ አካዳሚ) አንዱ ነው።

አካዳሚው ታዳጊዎችን በመመልመል ሥልጠና መስጠት ከጀመረ ሁለት ዓመት አስቆጥሯል። ከዛ በፊት ግን በተቆራረጠ መልኩም ቢሆን ሥልጠና ይሰጥ እንደነበር መሥራቹ አሠልጣኝ ዕድሉ ደረጄ ይናገራል። ባለፈው ዓመት በሀገር ውስጥ በምድብ አንድ ወደ ኢትዮጵያ ቡናና ኢትዮ ኤሌክትሪክ ያቀኑ ተጫዋቾችን አፍርቷል። በቀጣይም ፕሮፌሽናል ተጫዋች ለማፍራት ጠንካራ የውጪ ግንኙነት መሥርቷል። በዚህም መሠረት ኢዲዋይ አካዳሚ ከወራት በፊት አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት አድርጓል። ይህ ስምምነት ቲኤፍ ኤ ኢሊት ከሚባል በዱባይ የሚገኝ ፕሮፌሽናል የእግር ኳስ ክለብ ጋር ነው። ቲኤፍ ኤ በዱባይ ሊግ በሦስተኛ ዲቪዚዮን ይወዳደራል። ከዚህ በተጨማሪ ተጫዋቾችን እየመለመለ ሥልጠናም እየሰጠ ወደ አውሮፓ መላክ ላይ ትኩረት አድርጎ ይሠራል። ይህ አካሄድ ለተስፈኛ ኢትዮጵያውያን ተጫዋቾች መልካም ዕድል ሆኗል።

ቲኤፍ ኤ ኢሊት ምስራቅ አፍሪካን ጨምሮ በመላው ዓለም ላይ ልዩ ችሎታ /talent/ ያላቸው ታዳጊ ተማሪዎች ከመመልመል ባሻገር የአካዳሚውን ደረጃ /standard/ እንዲያሟሉ ሥልጠናዎችን በመስጠት ወደ አውሮፓ ክለቦች ይልካል። የኢዲዋይ አካዳሚ መሥራች አሠልጣኝ ዕድሉ ከቲኤፍ ኤ ኢሊት ጋር ባደረገው ዓለም አቀፍ የታዳጊዎች ምልመላ ስምምነት የ18 ዓመት ወጣት የሆኑት ናትናኤል አረጋዊና ቢንያም ደስታው ዕድል የተፈጠረላቸው ተጫዋች ናቸው። ናትናኤል ከዓመት በፊት ወደ ቲኤፍ ኤ አካዳሚ ገብቶ ከሠለጠነ በኋላ ከመላው ዓለም ከ10 አገራት ከመጡ ተጫዋቾች አንደኛ በመሆን ነበር ለመፈራረም የበቃው። ቢንያምም በተመሳሳይ። አሁን ላይ የሁለቱ ወጣቶች ፍሬ በአጭር ጊዜ መታየት ጀምራል።

የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን በቅርቡ በሚያደርገው የአፍሪካ ዋንጫ የሴካፋ ዞን ማጣሪያ ላይ በአሠልጣኝ ሥዩም ከበደ ጥሪ ከተደረገላቸው ተጫዋቾች መካከል ሁለቱ የኢዲዋይ አካዳሚ ፍሬዎች ይገኙበታል።

‹‹ወደ ዱባይ ያቀናሁት በአሠልጣኝ ዕድሉ አማካኝነት ነው›› የሚለው ናትናኤል እዚያ ካቀና በኋላ ከኢትዮጵያ የተለየ ነገር ያገኘው በዋናነት በሥልጠና አሰጣጡ ላይ መሆኑን ይናገራል። ‹‹እዚያ ሁሉም ነገር ፕሮፌሽናል ነው፣ ከሜዳ ጀምሮ እስከ አመጋገብ ምንም የሚጓደል ነገር የለም፣ ከእኛ የሚጠበቀው አቅማችንን አውጥተን ማሳየት ነው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አንዱ ችግር የሜዳ ነው፣ ታዳጊዎች ደግሞ የተሻለ ደረጃ እንዲደርሱ ምቹ ሜዳ የግድ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ታዳጊዎች ላይ ትኩረት አይደረግም›› ያለው ናትናኤል፣ እሱ ያገኘውን አይነት ዕድል ቢያገኙ አቅሙና ብቃቱ ያላቸው በርካታ ኢትዮጵያውያን ታዳጊዎች በእድሜያቸው መሠረት ተመልምለው የኢትዮጵያን እግር ኳስ መቀየር እንደሚችሉ እምነት አለው። ቢንያምም በዚህ ረገድ ከናትናኤል የተለየ ሀሳብ የለውም።

ኢዲዋይ አካዳሚ የፈጠረለትን ትልቅ ዕድል ተጠቅሞ በዱባዩ ክለብ የሙከራ ጊዜውን በስኬት በማጠናቀቅ ከስምንት ወር በፊት መፈረሙን የሚያስታውሰው ቢንያም፣ የኢትዮጵያን እግር ኳስ ወደ ኋላ እየጎተተው የሚገኘው ከመሠረተ ልማት ጀምሮ እስከ ሥልጠና ያለው ችግር በዱባዩ ቆይታው አልገጠመውም። እንደ ኢዲዋይ አካዳሚ ሌሎችም ለታዳጊዎች የእሱ አይነት ዕድል በስፋት መፍጠር ከቻሉ የኢትዮጵያን እግር ኳስ የመለወጥ አቅሙ እንዳላቸው ጥርጥር የለውም።

አሠልጣኝ ዕድሉ እነዚህ ወጣቶች በዱባይ ባገኙት ዕድል ከአካል ብቃት ጀምሮ ብዙ እድገት ማሳየታቸውን ይናገራል። ኢትዮጵያ ውስጥ ከመሠረተ ልማት ጀምሮ ታዳጊዎቹ ወጥ በሆነ መንገድ አቅማቸውን ለማሳደግ ብዙ ፈተናዎች እንዳሉባቸው በማስታወስም፣ በዱባይ ቆይታቸው በዋናነት የፕሮፌሽናል አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ ከማድረጉ በተጨማሪ ፉክክር በበዛበት ሂደት ውስጥ ጎልተው ለመውጣት ጠንክረው እንዲሠሩ ማድረጉን አስረድተል። በዚህ ሂደት አልፈው ለወጣት ብሔራዊ ቡድን መጠራታቸውም ለሌሎች ተነሳሽነትን ይፈጥራል ባይ ነው።

---

## ከኢትዮጵያ ባዮና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በየ15 ቀን የሚታተም

BETin
BIO & EMERGING TECHNOLOGY INSTITUTE

## የአየር ንብረት ለውጥን በአረንጓዴ ዐሻራ

**በፍሬው ደረጀ**

የአየር ንብረት ለውጥ ከተፈጥሮ ዑደት ውጭ በሰው ልጅ የተለያዩ እንቅስቃሴ ሳቢያ በሚጨምር የሙቀት አማቂ ጋዞች ምክንያት የተከሰተ እና በዚህ ዘመን ለሰው ልጅ ትልቅ ፈተና የሆነ ክስተት ነው። የመሬት የሙቀት መጠን መጨመር እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች የሙቀት መጠን ከሚጠበቀው በታች መውረድ፣ የዝናብ ስርጭት መዛባት፣ ድርቅ እና ርሃብ መከሰት የሚያስከትል ነው።

የአየር ንብረት ለውጥ በሁሉም የልማት ዘርፎች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ የሚያደርስ ነው። ለአብነትም በግብርናው ዘርፍ ዙሪያ የምርት መቀነስ እና ሰብሎች ለተለያዩ በሽታዎች መጋለጥ፤ በሽታ አምጪ በሆኑ ሕዋሳት መጠቃት፤ በጤናው ዘርፍ ላይ የሰዎችን ጤና በማዛባት ከፍተኛ ተፅዕኖ ማስተል ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በትራንስፖርት ዘርፍ፣ በኃይል ምንጭ፣ በኢንዱስትሪው፣ በተፈጥሮ ሀብት ላይ በአጠቃላይ በዓለም ዙሪያ እየተከሰቱ ላሉ የተለያዩ አደጋዎች ምንጭ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች ናቸው። ስለሆነም የአየር ንብረት ለውጥ በሀገራት ኢኮኖሚ ላይ፣ በሰው፣ በእንስሳት እንዲሁም በአካባቢ እና በተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ በመገንዘብ መሥራት ለነገ የሚባል ተግባር መሆን የለበትም።

ችግሩ በአንድ ሀገር ወይም አሕጉር የማይፈታ ዓለም አቀፋዊ ትብብርን የሚጠይቅ በመሆኑም ሃገራት በመረዳዳት ትኩረት ሰጥተው ሊሠሩበት ግድ ነው፤ ከዚህ አንጻርም ይመስላል እኤአ በ1990 የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሀገራት ተደራዳሪ ኮሚቴ በአየር ንብረት ለውጥ (Intergovernmental Negotiating Committee for a Framework Convention on Climate Change (INCFCCC) ) ላይ እንዲቋቋም የተደረገው።

ሀገራት ወደዚህ ማዕቀፍ ከመጡ በኋላ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ድርድር ያደረጉ ሲሆን፤ አሁን ላይ ከ196 ሃገራት በላይ አባል በማድረግ እኤአ በ21 March 1994 የተባበሩት መንግሥታት ኮንቬንሽንን በአየር ንብረት ለውጥ (United Nations Framework Convention on Climate Change (UNFCCC) ተፈራርመዋል። የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ስምምነት ሀገራት የሙቀት አማቂ ጋዝ እኤአ በ2008 እስከ 2012 በ5ነጥብ2 በመቶ ለመቀነስ እኤአ በ1997 ሲሆን፤ የኩዮቶ ፕሮቶኮል በመባል ይታወቃል። እኤአ በ2001 በጀርመን ቦን ላይ ሃገራት አጽድቀውታልም።

እኤአ በ2009 የኪፒንሀገን ፕሮቶኮል እንዲሁም እኤአ በ2015 የፓሪስ ስምምነት ሃገራት በትብብር እንዲሠሩ ስምምነት ላይ የደረሰባቸው ፕሮቶኮሎች ናቸው። ሃገራትም የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ በትብብር እንዲሠሩባቸው ሆነዋል።

ኢትዮጵያ በዓለማችን የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ ከሆኑት 10 ሃገራት መካከል አንዷ መሆኗን የመንግሥታቱ ድርጅት የአካባቢ ጥበቃ ድርጅት (UNEP) ጥናት ያመለክታል። በአማካይ የሙቀት መጠን መጨመርና የዝናብ ስርጭት መዛባት የመሰሉ ቀጥተኛ የሆኑ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች ተጠቂ ስትሆን በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢ በተደጋጋሚ ለሚከሰቱት ድርቅ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች የጎርፍ አደጋ የአየር ንብረቱ እያስከተላቸው ካሉት አደጋዎች መካከል ይጠቀሳሉ።

የሀገሪቱ 80 በመቶ ዜጎች መተዳደሪያ የሆነው እና 40 በመቶ ሃገራዊ ምርት የተመሠረተበት የግብርናው ዘርፍ ደግሞ 90 በመቶ የሀገሪቱ የኃይል ምንጭ ከውሃ የተመሠረተ በመሆኑም ለአየር ንብረት ለውጥ ቀጥተኛ ተጠቂ ከመሆናቸው አንጻር ሀገራዊ ተጋላጭነቱን ከፍተኛ ያደርገዋል። ስለሆነም መንግሥት የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ከፍተኛ አደጋ በመቋቋም በኢኮኖሚው እና በተለያዩ ዘርፎች ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት የተለያዩ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል።

ኢትዮጵያ እኤአ በ2011 ከሁሉም ዘርፎች ወደ 150 ‹‹MtCO2e›› ያህል የሙቀት አማቂ ጋዞች ወደ ከባቢ አየር የለቀቀች ሲሆን፤ በዚሁ ከቀጠለ እኤአ በ2030 400 ‹‹MtCO2e›› እንደሚደርስ ይገመታል። ይህን አካሂድ ለማስተካከል እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በዓለም አቀፍ የሚሠሩ ሥራዎች አካል ለመሆን እና ግዴታዎችን ለመወጣት እኤአ በ2011 ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ (ስልት) ቀርጻ ወደ ትግበራ ገብታለች።

የስትራቴጂው ዋና ዓላማ ቀጣይነት ያለውን ልማት እና ዕድገትን ማረጋገጥ ሲሆን፤ እኤአ በ2030 በአማካኝ ዜሮ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት በማድረስ ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካሏቸው ሃገራት ተርታ ማሰለፍ ነው። በዚህም በሁሉም ዘርፎች ከ60 በላይ ቴክኖሎጂዎች ተለይተው ወደ ትግበራ የተገባ ሲሆን፤ ሁሉም ዘርፎች ይህን ስልት የዕቅዳቸው አካል (mainstream) በማድረግ ሥራዎችን እያከናወኑ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እና ለማጣጣም ለአፍራካ ብሎም ለዓለም ምሳሌ የሚሆኑ ሰፊ ሥራዎች ሠርታለች፣ እየሠራችም ትገኛለች። ለምሳሌ፡- አረንጓዴ ዐሻራን ከማሳረፍ አንጻር ባለፉት ዓመታት እየተተከሉ ያሉ ችግኞች ልናይ እንችላለን። ለዘርፉ በተሰጠው ትኩረት እና በኅብረተሰብ ላይ ከፍተኛ የአመለካከት ለውጥ በማምጣት ኢትዮጵያ እኤአ በ29 July 2019 በአንድ ቀን ብቻ ከ350 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል የዓለምን ሪከርድ ልትይዝ ችላለች። ዘንድሮም ‹‹ኢትዮጵያን እናልብስ›› በሚል መሪ ቃል የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር አካል የችግኝ ተከላ የተጀመረ ሲሆን፤ ካለፉት ዓመታት ተሞክሮ በመውሰድ በቂ የሆነ ዝግጅት በማድረግ የተሻለ ሥራ እና ውጤት እንደሚገኝ ተስፋ ተጥሏል።

በመሆኑም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ሀገራችንን አረንጓዴ ለማልበስ ላደረጉት ጥሪ ሁሉም ዜጋ የድርሻውን በመወጣት ኢትዮጵያን ለመጪው ትውልድ ምቹ እና አረንጓዴ ለማድረግ መረባረብ ይኖርብናል። ሠላም!